ፍኖተ
# ነፃነት
ፍኖተ ነፃነት ማክሰኞ ጥር 29 ቀን 2004 ዓ.ም.
ዋጋ 6:00
2ኛ ዓመት ቅጽ.2 ቁ.28
የኢትዮጵያ ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን እንታገል!



## እያንዳንዱ ዜጋ የከተማ ቦታን በነፃ እንዲያገኝና የመሬት ባለቤት እንዲሆን እንሰራለን

አቶ ሽመልስ ሀብቴ

6

# የጋምቤላ ነዋሪዎች የሚሸሹት ከልማት vs ከጥፋት?



ነዋሪዎቹ የተፈናቀሉ፤ ሰዉ አልባ ጎጆዎች በጋምቤላ

2




በስደት ያሉ የጋምቤላ ነዋሪዎች በዳዳብ ኬኒያ ስደተኞች ካምፕ
(ከHRW የተገኘ) ስደተኞች ካምፕ (ከHRW የተገኘ)

## በጋሞ ጎፋ ዞን በተፈጠረ ግጭት አንድ ቤተክርስቲያን ተቃጠለ

ብስራት ወ/ሚካኤል

ደቡብ ክልል በሚገኘው ጋሞ ጎፋ ዞን ዲታ ወረዳ በሚገኘው ዛራ ከተማ ከጥር 10 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ በተፈጠረ ግጭት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክርስቲያን አካል የሆነው የቅዱስ ሩፋኤል ቤ/ክርስቲያን መቃጠሉ ተገለፀ፡ ፡ በቃጠሎውም የቤ/ክርስቲያኗ ንብረቶች መውደማቸው የተገለፀ ሲሆን በግጭቱም ከዞኑ እስከ ወረዳው ያሉ የመንግስት አመራሮች እጅ እንዳለበት ነዋሪዎቹ ያላቸውን ጥርጣሬ እየገለፁ እንደሆነ የዜና ምንጮቻችን ጠቁመዋል፡፡

ለግጭቱም መንስኤ ነው የተባለው አሁን ያሉት የዞኑ እና የወረዳዎቹ አመራሮች የፕሮቴስታንት ኃይማኖት ተከታዮች በመሆናቸውና የአመራር ለውጥ ይደረጋል አሁን

ወደ 11 ዞሯል

## በአገሪቱ ውስጥ ከፍተኛ ወንጀል እየተፈፀመ መሆኑን ሰመጉ አስታወቀ

ብዙአየሁ ወንድሙ

በመላው አገሪቱ ውስጥ ከፍተኛ ወንጀል እየተፈፀመ መሆኑን የቀድሞ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ጉባኤ /ኢሰመጉ በአሁኑ አጠራር የሰብአዊ መብት ጉባኤ /ሰመጉ/ አስታወቀ፡፡ ሰመጉ ይህንን ያስታወቀው ሰሞኑን ባወጣው "የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ በወጣው 35ኛ መደበኛ መግለጫ ነው፡፡

በኢትዮጵያ የመጀመሪያው መንግሥታዊ ያልሆነ የሰብአዊ መብቶች ተሟጋች ተቋም የሆነው ሰመጉ ባወጣው መግለጫ በአሁኑ ጊዜ በአገራችን "ህገወጥ ግድያ፣ ከይዞታ ማፈናቀል፣ ህገ መንግስታዊ ሀሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት መከልከል፣ በነፃነት የመኖር መብት ጥሰት፣ ህገወጥ እስር፣ ማሰቃየት፣ ህገ ወጥ እስር እና ኢ-ሰብአዊ አያያዝ የስራ እና የመኖር ዋስትና ማጣት፣ ፍትህ ማጣት፣ የደረሰበት አለመታወቅ፣ ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ አለመመለስ" እየተፈፀመ መሆኑን በማስረጃ በማስደገፍ ዘርዝሯል፡፡

ሰመጉ ባወጣው ባለ 32 ገጽ መግለጫው እንደዘረዘረው "በደቡብ ክልል ሲዳማ ዞን በቆንሴ አርኬ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ነዋሪ የሆኑ ወ/ሮ ወርቄ አሩሳ በፖሊስ በሁለት ጥይት በግፍ ተገለዋል፡፡ በርካታ ሰዎች በህገ ወጥ መንገድ ከይዞታ ተፈናቅለዋል፡፡ ኢትዮጵያ ፊርማ የተቀበለችውን እያንዳንዱ ግለሰብ የመረጃ የማግኘት መብት እንዲሁም ሀሳብንና አመለካከትን በነፃነት የመግለትጽ መብት የሚደነግገውን እና እንዲሁም የህገ መንግስቱን አንቀጽና የፕሬስ አዋጅን በመጣስ የምናጣራው አለ በማለት የህትመት ፍቃድ ተከልክሏል፡፡" በማለት ይዘረዝራል፡፡

መግለጫው በነፃነት የመኖር መብት ጥሰትን ሲዘረዝር "እንዳልካቸው ወሰኑ ደምሴ አማራ ክልል ሰሜን ወሎ ዞን መቄት ወረዳ 01 ቀበሌ ፍላቂት የሆነው ወጣት በወረዳው ከባቢዎች ከመንግስት ሥራውና ከአካባቢው እንዳይኖር ተገዶ መሰደዱን፡፡ አቶ ዳኜ አበራ ለማ አዲስ አበባ ጉለሌ ክ/ከ ሽሮ ሜዳ በደረሰበት ማስፈራራት እንግልት ደርሶበት አካባቢውን ቢለቅም ክትትል እየተደረገበት በነፃነት መኖር አለመቻሉን፤ አቶ ንጋቴ መላኩ የአዲስ አበባ ነዋሪ ሲሆን የመከላከያ ሠራዊት ሆኖ አገልግሎ ከሠራዊቱ ከወጣ በኋላ ሐሳቡን በነፃነት በመግለጹ ምክንያት ድብደባ እስራትና ማሰፈራሪያ እንደተፈፀመበት፤ አቶ በአካል ተሾመ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ 3ኛ ዓመት ተማሪ የሆነ በሁለት የደህንነት

ወደ 11 ዞሯል

## በውስጥ ገፅ

የትምህርት ደረጃቸውን ያሻሻሉ ባለሙያዎች የደረጃ ዕድገት መከልከላቸውን ገለፁ 10
"አሁን መሬት የሌለው ሁሌም የለውም" 11
የከተማ ቦታ የሊዝ "መነሻ ዋጋ ስንት ነው?" 9
የኦሮሚያ ትራፊክ ፖሊስ ለሌሎቹ ምሳሌ ሊሆን እንደሚገባ ተገለፀ 10
"ፈረዱባቸው" 3

**ኢትዮጵያውያን መሬትን በተመለከተ በሁለት መልኩ ተዋግተዋል የውጭ ወራሪዎችን እና የውስጥ አጋባሾችን፡፡ በተለይም አብዮተኞቹ የዘመናዊ ትምህርት “መሬት ለአራሹን” በማቀንቀን ብዙ ከፍለዋል፡፡ ደርግን ያለ ፈቃድ በማስፈር ሲያብጠለጥል የነበረው ኢህአዴግ ደግሞ ለዚያውም ሰፋሪዎቹን ቀጥተኛ ተጠቃሚ ለማያደርግ ፕሮግራም ከፍተኛ የአካል እና የመንፈስ መፅዋዕት እንዲከፍሉ “ጋምቤላዎችን” እያስገደደ ነው የሚለው ሰለሞን ስዩም ተከታዩን አጠናቅሯል፡፡**



ሰለሞን ስዩም
era4st@yahoo.com

# የጋምቤላ ነዋሪዎች የሚሸሹት ከልማት vs ከጥፋት?

ኢህአዴግ የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎችን “አቋመ ቢሶች” ሲል ይወቅሳቸዋል፡፡ በሌላ መልኩ አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ታዛቢዎች የኢህአዴግ ፕሮግራሞችን “ንፋስ አመጣሽ” ሲሉ ይተቻሉ፡፡ የልማታዊ መንግሥት ትንተናን ከጀመረ ወዲህ ቁሳዊ ዕድገት የሚያመጣ የትኛውም መንገድ ብልፅግና መሆኑን ከማመኑም በላይ የመጣለትን ሁሉ ዜጎች የግድ ሊተገብሩት እንደሚገባቸው አድርጎ እንደሚወስድ ይስማማሉ፡፡

ነገር ግን በ1994 ዓ.ም በኢፌዴሪ የታተመ የገጠር ልማት ፖሊሲዎች ስትራቴጅዎችና ስልቶች የሚል ሰነድ የመንግሥት አቋም ለማንፀባረቅ ሞክሮ ነበር፡፡ ሰነዱ በሰፈራ እና መንደር ምስረታ ፕሮግራሞች አስፈላጊነት ቢያምንም ለውጤታማነቱ ግን ጥንቃቄ እንደሚያሻው ያትታል፡፡ መንግሥት የደርግ ስሜትን ከማጥፋት ዘመን ባልወጣበት /Dedergaization/ በዚያን ወቅት “የደርግ የሰፈራ ፕሮግራም ዋነኛ ጉድለት የሰፈራው ፕሮግራም በሰፋሪው ፈቃድና ፍላጎት ላይ ያልተመሠረተ የነበረ መሆኑ ነው” ሲል ይገመግማል፡፡ ከታሪክ የተማረ የሚመስለው የኢህአዴግ መንግሥት ለምግብ ዋስትና ከሚቀመጡ መፍትሄዎች ዋነኛው የሰፈራ ፕሮግራም መሆኑን ቢደመድምም “የሰፋሪውን ፈቃድ ያላካተተ ነገር ፈፅሞ ግቡን አይመታም” ሲል ያስጠነቅቃል፡፡

በሌላ መልኩ መንግሥት ከሚለው በተቃራኒ በተያዘው የፈረንጆች አመት ገበሬዎች በቆሎ ለማምረት በተዘጋጁበት ከህዳር-ታህሳስ ባለው ጊዜ ውስጥ አስገዳጅ የሰፈራ ፕሮግራም መከወኑን Human Rights watch ያብራራል፡፡ መንግሥት “የህዝብ ተሳትፎ በምንልበት ወቅት በእምነትና በፍላጎት ላይ የተመሠረተ ተሳትፎ ማለታችን ብቻ ነው ሊሆን የሚችለው” ቢልም Human Rights watch በበኩሉ ፕሮግራሙ “በማስፈራሪያ፣ በድብደባና፣ በዘፈቀደ ቅጣቶች የታጀበ ነበር” ይላል፡፡

ሁኔታውን ሸሽተው በኬኒያ ዳዳብ የስደተኞች ካምፕ የሚገኙ የጋምቤላ ተወላጆች እንደሚሉት ለሰፈራ በሄዱባቸው ቦታዎች ጎጆ ቤቶችን እንዲገነቡ በወታደሮች የሚገደዱ ሲሆን ለአፍታ እንኳ እረፍት መውሰድ አሊያም ከስራ አጋር ጋር እያወሩ መስራት ለጥቃት እንደሚያጋልጣቸው መስክረዋል፡፡ በውጤቱም በህብረተሰቡ ዘንድ ሽብር መንገሱን ሪፖርቱ ጠቅሷል፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት ባለሥልጣናት የመንደር ምስረታን (ሠፈራን) አስፈላጊነት ሲያስረዱ “ምክንያታዊ የመሬት አጠቃቀም፣ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና፣ ደህንነትን ማጠናከርና ለንፁህ ውሃ አቅርቦት፣ ጤናና ትምህርት መሠረተ ልማቶች ተደራሽነት ነው” በማለት ነው፡፡ የሰነድ ማስረጃዎች እንደሚያሳዩት በ4ቱ ታዳጊ ክልሎች የታቀደው የሰፈራ ፕሮግራም አፋር እና ሶማሌ ክልልን ለአንድ አመት ብቻ ያቀፈ ሲሆን በሁለቱ ለም ክልሎች ቤንሻንጉልና ጋምቤላ ለሦስት አመታት መያዙን ያወሳሉ፡፡

የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ዶ/ር ሽፈራው ተክለ ማሪያም የአፋር እና የሶማሌ ክልሎችን ሰፈራ “ሰዎቹን ከበረሃ ወደ ከፊል በረሃ ለማምጣት” ነው ያሉ ሲሆን የቤኒሻንጉል ጉምዝና ጋምቤላ ግን “ለተሻለ አገልግሎት ቅርብ እንዲሆኑ” ብለዋል፡፡ በብሉምበርግ የዜና ድህረ ገፅ ላይ በወጣው ደብዳቤ ሚኒስትሩ “በጋምቤላ የሚካሄደው ሰፈራ ድህነትን እና ድንቁርናን ለማስቀረት” ያለመ ሆኖ ከቁሳዊ እስከ መንፈስ ብልፅግና ያሉ ጉዳዮችን በዝርዝር አቅርቧል፡፡ ቀደምት የመንግሥት ሰነዶችም ለሰፈራ የተለዩ ቦታዎች ምንም አይነት መሠረተ ልማት በሌለባቸው፣ ከፍተኛ የጤና ችግር በሚስተዋልባቸው ቆላማ አካባቢዎች መሆናቸውን ያምናሉ፡፡ በመሆኑም “እነዚህን ችግሮች የሚፈታ የመንገድ፣ የጤና አገልግሎቶች፣ የመጠጥ ውሃ፣ የትምህርት መሠረተ ልማት ዝግጅት ሳይጠናቀቅ የሰፈራ ስራን ማስጀመርም የማይታሰብ መሆን አለበት” ይላሉ፡፡ ለውጤታማነቱም “. . . ሰፈራ በሚካሄድባቸው አካባቢዎች የመሠረተ ልማት



ስራዎችን አስቀድሞ ማካሄድ ነው” ሲሉ መላ ይላሉ፡፡

በሌላ በኩል፣ አንድ ምስክርነት የሰጡ የአቦቦ ወረዳ የአኙዋክ ቤሄረሰብ አዛውንት “ግልፅ ሊሆንላችሁ የሚገባው መንግሥት እዚህ ያመጣን እዚሁ እንሞት ዘንድ ነው፣ . . . አለም እንዲሰማን የምፈልገው ነገር መንግሥት አኙዋኮችን እዚህ እንዲሞቱ ነው ያመጣቸው፡፡ ምግብ አልቀረበልንም፡፡ መልሰን እንኳ እንዳንሄድ መሬታችንን ለባዕዳን ሰጥቷል” ብለዋል፡፡

መላኩ ውብነህ የተባሉ አጥኚ “Resettlement and villagization” በተባለ ጥናታቸው “ውሳኔው ምቹ አይደለም፡፡ ሺዎች ተሰደዋል፡፡ ሌሎች ተገደው ከሰፈሩ በኋላ በነፍስ ግቢ ነፍስ ውጪ ሁኔታ አልያም በሞት ተለይተዋል፡፡” በሌላ መልኩ ዋነኛ የመልሶ ሰፈራ አላማ ነው የተባሉት “የመጠጥ ውሃ፣ መብራት፣ ጤና ተቋማት፣ ት/ት ቤቶች፣ ትራንስፖርት፣ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት” የመሣሰሉት መንግሥት አቅም የለውም በሚል ምክንያት አልቀረቡም፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ መንግሥት በፖሊሲ ደረጃ የያዘውን አባወራዎችን ደረጃ በደረጃ በመጀመሪያው አመት ስልጠና በመስጠትና ቦታው ድረስ በመውሰድ ለቀጣዩ አመት ሁኔታ እንዲያመቻቹ የማድረግ ዕቅድ ገሸሽ አድርጎ “ሱሪ በአንገት” አይነት መከተሉን ታዛቢዎች ያወሳሉ፡፡ በዚህም የተነሳ የሰፈሩባቸው አካባቢዎች ደረቅ እና ጠፍ መሬት እንዲሁም ምንጣሮ የሚጠይቁ በመሆ ናቸው ቅድመ ዝግጅት እና ጊዜ በተሰጣቸው ነበር፡፡ በተጨማሪም ዘር፣ ማዳበሪያ፣ የእርሻ መሳሪያና ስልጠና ባልተዘጋጀበት ሁኔታ በወጡበት እንዲቀሩ ማስገደድ “በሞት ድግስ እንደ መታደም ነው” ይላሉ በደቡብ ኬኒያ የስደተኞች ካምፕ ቃላቸውን የሰጡ አንድ የአኙዋክ ብሄረሰብ፡፡ ምንም በሌለበት ሁኔታ ከሞት ጋር መፋጠጥ ቢሆንም ቅሉ በአዲሱ የሰፈራ መንደር መቆየት ግድ የሚል ነገር ነው፡፡ ከወታደሮች አይን አምልጠው ወደ ቀድሞ መንደራቸው የተመለሱ ሰዎች ሰብላቸው ወይ በዝንጀሮ አሊያም በአይጠ መጎጥ ወድሞ እንደሚያገኙት ይናገራሉ፡፡

“በህዝብ ፈቃደኝነት” vs በሰቆቃ?

“የቀሩኝን ንብረቶች ለመቃረም ወደ ቀድሞ ቀዬዬ ስመለስ አንዱ ወታደር `እዚህ የመጣህው ለምንድነው? ሌባ መሆን አለብህ` ሲል በዱላ ደበደበኝ፡፡ አሁን ድረስ ደረቴ ላይ ስቃይ አለኝ፡፡ ከዚህ ቀን በፊት ጓደኛዬ በወታደሮች ተገድሏል፡፡ በዱላና በጥይት ተደብድቦ ደም አስታወከ፣ ሳናስታምመው አረፈ፡፡ የ19 አመት ለግላጋ ነበር፡፡ እየተደበደበ ሳለ ብዙ አኙዋኮች በዙሪያው ተኮልኩለው አምርረው ቢያለቅሱም፣ ለመገላገል /ለማስጣል አልቻሉም፡፡ ብዙ ወታደሮች ነበሩና፡፡” ይህን ያለው አንድ የአኙዋክ ብሄረሰብ ወጣት ነው፡፡

ጠቅላይ ሚ/ር መለስ ዜናዊ በህዳር ወር የብሔር ብሔረሰቦችን ቀን በማስመልከት በራዲዮና በቴሌቭዥን ቤታችን ድረስ እየገቡ “ኢትዮጵያ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩባት ሀገረ ናት” ብለው ነበር፡፡ ቀደሞ የገጠር ልማት ሰነዱም ሌላኛው የሰፈራ ፕሮግራም አላማ ለመልካም አስተዳደር እና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ያመች ዘንድ እንደሆነ ያመለክታል፡፡ HRW በዳዳብ ኬኒያ ያናገራት የቀድሞ ጎጅ ዴፓቼ ሴት ነዋሪ “አንድ ቀን ጥላ ስር ሆነን ጎመን እየበላን ነበር፡፡ ወታደሮች መጡና አምስት ልጆቻችንን ጠርተው ክፉኛ ደበደቧቸው፡፡ ወደ ሆስፒታል ቢወሰዱም ሁለታቸው ሞተዋል፡፡ ቀሪዎቹም በከባድ ስቃይ ነው ያሉት፡፡ . . .የሰውን ሬሳ በየመንገዱ ዳር ማግኘት ብርቅ አይደለም፡፡ ጉሮሮያቸው ተቆርጦ የሚገደሉ አሉ፡፡ እነዚህ ሰዎችን የቀሰቀሱ ሰዎች ግድያ ምልክት መሆኑ ነው” በማለት ከመጋረጃ ጀርባ ያለውን ተውኔት ተናግራለች፡፡

የሰፈራ ሂደቱን አስገራሚ የሚያደርገው በመንግሥት አቋም እና በተግባር በሚታየው መካከል ሰፊ ልዩነት መታየቱ ነው፡፡ መንግሥት ምንም ነገር ያለ ህብረተሰቡ ቀጥተኛ ምክክር እና ፈቃደኝነት እንደማይሳኩ በገጠር ልማት ሰነዶቹ ይወተውታል፡፡ በተቃራኒው በወታደር ጭምር እየተጠበቁ የሚገኙት ሰፋሪዎች ተገደው ያሉ ስለመሆናቸው ከሚቀርቡ ምክንያቶች አንዱ የኑዌር ሰፋሪ የብሄረሰብ አባላት አዲሱን ጣቢያ ሙሉ በሙሉ ጥለው መሄዳቸው ነው፡፡

ስንድራ ስቴይንገራባር የተባለች አጥኚ “Resettlement and villagation” በተባለ ጥናቷ የጋምቤላ ህዝብ ነፃ አውጭ ንቅናቄ የተመሠረተው የደርግን የሰፈራና መንደር ምስረታን ፕሮግራም በመቃወም መሆኑን

ወደ 5 ዞሯል

# "ፈረዱባቸው"



ክፍል አንድ

<u>ብዙአየሁ ወንድሙ</u>

- እኔ ወንጀል አልፈፀምኩም፡፡ ጥፋተኛም አይደለሁም፡፡ ታሪክ ነፃ ያወጣኛል፡፡ አቶ ዘሪሁን ገ/እግዚሐብሄር
- ማስረጃ ባልቀረበበት ክስ ፈርዳችሁብኛል፡፡ ጋዜጠኛ ውብሺት ታዬ
- ይህ የሰው ፍርድ እንጂ የእግዚሐብሄር ፍርድ አይደለም፡፡ ወ/ሮ ሂሩት ክፍሌ

ባለፉት 20 ዓመት ከአገራችን በርካታ ክስተቶችን አስተናግዳለች፡፡ በተለይ በፍ/ቤት ዙሪያ ብዙ አሳዛኝም፤ አስገራሚም የሚባሉ ነገሮች ተፈጽመዋል፡፡ በወቅቱ አንድ ግዙፍና ጠንካራ ተቃዋሚ ፓርቲ በመመስረት፣ በህክምና ሞያቸውና በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህርነታቸው እንዲሁም በግል ስብዕናቸው ስመጥርና አንቱ የተባሉት የፕ/ር አስራት ወልደየስ የፍርድ ሂደት ዘላለም ይታወሳል፡፡ እሳቸው ፍ/ቤት በሚቀርቡበት ወቅት ፍ/ቤት የሚሰበሰበው ህዝብ አስገራሚ ነበር፡፡ በአንድ ወቅት በዚሁ በፍ/ቤት ዙሪያ በተሰበሰቡ ሰዎች ላይ የጅምላ አፈሳ ተደርጐ ለሦስት ወር ኮልፌ ፖሊስ ካምፕ ታስረው ነበር፡፡

ተይዘው ሲታሰሩ ትልቅ የለ ትንሽ ፀጉራቸውን በጠቅላላ እንዲላጩ ተደረጉ፡፡ አዛውንቷ አምባሳደር ዮዲት እምሩም አንዷ ሰለባ ነበሩ፡፡ ፕ/ር አስራት በተከሰሱበት ወንጀል ለጊዜው ለመከራከር ቢሞክሩም የዳኝነቱ ሂደት እምነት አሳጥቷቸው ነበር፡፡ "ፍትሐዊ ዳኝነት በሌለበት አልከራከርም" ብለው ጠበቆቻቸውን ማሰናበታቸው ይታወሳል፡፡ ተፈረደባቸውና እስር ቤት ገቡ፡፡ ከዚያም የሆነው ሁሉ ሆነ፤ ሞቱ፡፡ ተቀበሩ፡፡ ከመሞታቸው በፊት ግን አንድ ነገር ተናግረው ነበር፡፡ "ሻማውን ለኩሰነዋል፡፡ ከእንግዲህ ማንም አያጠፋውም፡፡" ነበር ያሉት፤ ፕ/ር አስራት ወልደየስ፡፡

የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር /ኢመማ/ ፕሬዝዳንት የነበሩት ዶ/ር ታዬ ወ/ሰማያት ተከሰሱና ፍ/ቤት ቀረቡ፡፡ በአገሪቱ ውስጥ አመጽ ለመቀስቀስ ፓርቲ እንዳቋቋመ፤ ጦር እንዳደራጁ፤ ተመሰከረባቸውና ተፈረዳባቸው፡፡ የፍርዱ ዕለት በጉጉት ተጠብቆ ነበርና በርካታ ታዳሚዮች ችሎቱን ሞልተው ይከታተሉ ነበር፡፡ "15 ዓመት እንዲታሰሩ ተወስኖበዎታል፤ በፍርዱ ቅሬታ ካልዎት ይግባኝ ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡" ተባሉ፡፡ ዶ/ር ታዬ "ከእንግዲህ እናንተ 15 ዓመት የምትቆዩ ከሆነ ውጪ ከምሆን እስር ቤቱ ይሻለኛል፡፡" ብለው ተናግረው እስር ቤት ገቡ፡፡ ፓርቲያቸውንም ጦራቸውንም ማንም ሳያውቀው በወረቀት ላይ ቀረ፡፡ ቀን ፈታቸውና ተፈቱ፡፡ እና ተሰደዱ፡፡ ሌሎች በርካታ ገጠመኞችን ማንሳት ይቻላል፡፡ በቅርቡ የወጣው የፀረ-ሽብር አዋጅ መነጋገሪያ ሆኖ መቆየቱ ይታወቃል፡፡ አዋጁ ገና ከረቂቁ ጀምሮ ከፍተኛ ተቃውሞ ቀርቦበታል፡፡ አዋጅ ሆኖ እንዳይወጣ ከአገር ውስጥም፣ ከዓለም አቀፍ ማህበረሰብም፤ ጥረት ተደርጐ ነበር፡፡

ረቂቅ አዋጁን አጥብቀው ካወገዙት ድርጅቶች ውስጥ አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍተህ ፓርቲ/አንድነት/ ይገኝበታል፡፡ ሰኔ 18 ቀን 2001 ዓ.ም "የፀረ-ሽብርተኝነት ረቂቅ አዋጅ በዜጐች ላይ ሽብር ፈጣሪ ነው!!" በማለት መግለጫ ማውጣቱ ይታወቃል፡፡ በወቅቱ በፓርላማው ውስጥ የነበሩ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት አጥብቀው አውግዘውታል፡፡ ዓለም አቀፍ ማህበረሰቡም ረቂቁ እንዳይፀድቅ አሳስበዋል፡፡ "አዋጁ ተቃዋሚዎችንና ጋዜጠኞችን ለማጥቃት የታለመ ነው" በማለት ሥጋታቸውን ገልፀዋል፡፡ "አዋጁ አገርንና ህዝብን ለመጠበቅ ታስቦ የተዘጋጀ ሳይሆን ኢህአዴግን በሥልጣን ላይ ለማቆየትና ኢህአዴግ እየፈፀመ ላለው አፈናና ወንጀል ህጋዊ ሽፋን ለመስጠት የታሰበ ነው" ሲሉ አብጠልጥለውታል፡፡

ፓርላማው በረቂቅ አዋጁ ላይ ሲወያይ በወቅቱ የፓርላማው አባል የነበሩት አቶ ወንድሙ ኢብሳ "ረቂቅ አዋጁ በራሱ ሽብር ነው" ሲሉ ረቂቅ አዋጁን አጣጥለውት ነበር፡፡ ሁሉም ቢያወግዘውም፣ ቢፈራውና ቢጠላውም አዋጁ አዋጅ ሆኖ ወጣ፡፡

በዚህ ክስ የተመዘገቡት የኢትዮጵያ ሪቪው ድህረ ገጽ ባለቤት አቶ ኤልያስ ክፍሌ በሌሉበት ክሳቸው ታይቶ የእድሜ ልክ እስራት ተፈርዶባቸዋል፡፡ 2ኛ ተከሳሽ የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ፓርቲ /ኢብአፓ/ ፕሬዝዳንት አቶ ዘሪሁን ገ/እግዚሐብሔር ናቸው፡፡ ከመከሰሳቸው በፊት አቶ ዘሪሁንና ፓርቲያቸውን እስቲ በጥቂቱ እንመልከት፡፡ ይህ ፓርቲ 2002 ምርጫ ንቁ ተሳትፎ ያደርጉ ከነበሩ ፓርቲዎች ውስጥ አንዱ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ጠንካራ የተቃውሞ አቋሞችን ይወስድ የነበረ ቢሆንም ብዙ የሚዲያ ሽፋን ባለ ማግኘቱ በህብረተሰቡ ዘንድ በስፋት ይታወቃል ተብሎ አይታሰብም፡፡ ፓርቲው የምርጫ ሥነ ምግባር ደንብ ሲፀድቅ በቅድሚያ ያወገዘና ራሱን ያገለለ ፓርቲ ነው፡፡ የምርጫ ሥነ ምግባሩን ካልፈረሙት ጥቂት ፓርቲዎች ውስጥም አንዱ ነው፡፡ በምርጫውም ላይ ከ60 በላይ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤትና በመቶዎች የሚቆጠሩ ለክልል ም/ቤት እጩዎችን አስመዝግቦ ተወዳድሮአል፡፡ የምርጫውን ውጤት አንቀበልም፤ ብሎ መግለጫ ካወጡት ፓርቲዎች ውስጥም አንዱ ነው፡፡ ከምርጫው በኃላ ፓርቲውን ወክለው የተወዳደሩ ከሥራ ተባረሩብኝ፣ ታሰሩብኝ፣ እርዳታ ተከለከሉ፣ ተሰወሩብኝም፣ በማለት በተደጋጋሚ መግለጫ አውጥቶ ነበር፡፡ ግንቦት 20 ቀንን በማውገዝ ህዝባዊ ሰለማዊ ሠልፍ ለማድረግ ባለፈው ዓመት ግንቦት 20 ቀን 2003 ዓ.ም ፍቃድ ጠይቀው ተከልክለዋል፡፡ በዚሁ የተነሳ ከፍተኛ ማስጠንቀቂያና ዛቻ እንደተፈፀመባቸው ክትትል ይደረግባቸው እንደነበረም ለፍ/ቤቱ ሲያስረዱ ተደምጧል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ሰኔ 12 ቀን 2004 ዓ.ም "በሽብርተኝነት ተጠርጥረሃል" ተብለው ታሰሩ፡፡ አቶ ዘሪሁን ከማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ ወደ ቃሊቲ ማረሚያ ቤት በወረዱበት ወቅት ለዝግጅት ክፍላችን አንድ ደብዳቤ ልከው ነበር፡፡ ጉዳዩ በፍ/ቤት የተያዘ ስለሆነ በወቅቱ አላወጣነውም ነበር፡፡

በዚህ ደብዳቤ ላይ እንደገለፁት እና ፍ/ቤት ሲያስረዱ እንደተደመጠው "በታሰርኩ በማግስቱ ምርመራ ቢሮ ተጠራሁ፡፡ ከዚያም መቼም አንተ የአራዳ ልጅ ነህ፡፡ እንደ ገጠር ልጅ አትገግምም፡፡ እኛ በምንነግርህ መሠረት የመድረክ መሪዎች፣ የአንድነት ፓርቲ አመራሮች ላይ በኤልያስ ክፍሌ ላይ ትመሰክራለህ፡፡ ከዚያም ትለቀቃለህ አሉኝ፡፡ ምንድነው የምመሰክረው ብዬ ስጠይቃቸው ሽብርተኞች ናቸው፡፡ ወንጀለኞች ናቸው፡፡ ይህን ይህን አድርገዋል፡፡ እኔንም እንዲህ እንዲህ አድርግ ብለውኛል ብለህ አሉኝ፡፡ በእርግጥ መርካቶ ተወልጄ አድጌአለሁ፡፡ የአራዳ ልጅ ወይም የመርካቶ ልጅ አብሮ ይሰራል፡፡ አብሮ ተሸምቶና ተቀማምቶ ይበላል፡፡ ለጓደኛውና ለእውነት ይሞታል እንጂ በማያውቀው ነገር የሐሰት ምስክር አይሆንም፡፡ የአራዳ ልጅ በእምነቱ ይሞታል እንጂ ግብዝ አይሆንም፡፡ እየሰማሁ ያደኩት ይህንን ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ እኔ በሐሰት አልመሰክርም፡፡ የያዛችሁኝ ማስረጃ አለን ብላችሁ ነው፡፡ ከያዛችሁኝ በኋላ እንዴት እንዲህ ትሉኛላችሁ? አልኳቸው፡፡ ፍ/ቤቱን የምናዘው እኛ ነን፡፡ እንቢ ካልክ የ20 ዓመት እስር ይጠብቅሀል፡፡ የሚደርስብህን ሁሉ ታያለህ አሉኝ፡፡ የፈለጋችሁትን አምጡ እንጂ በሐሰት ምስክር ሆኜ አልቀርብም አልኳቸው፡፡" ይላል፡፡ ቤተሰቦቻቸው እንደሚሉት ደግሞ "መርማሪው ፖሊስ ጠርቶ ምከሩት፡፡ ለሰው ብሎ ራሱንና ቤተሰቡን እየጐዳ ነው፡፡ እሱ እንዴት የቤተሰብ ኃላፊነት አይሰማውም? እኛ እሱን ለመርዳት ከፍተኛ ጥረት እያደረግን እሱ ግን እንቢ እያለ ነው፡፡ ቀላሉን ጉዳይ ከባድ እያደረገው ነው፡፡ ብትመክሩት ይሻላል አለን፡፡ እኛም በየዋህነት ሄደን መርማሪው ፖሊስ እንዳለው መርማሪው ባለበት ለምን የሚሉህን እሺ አትላቸውም? ይኸው መርማሪው ፖሊስ ምከሩት እያለን ነው፡፡ መፈታት አትፈልግም ወይ ለእኛስ ለምን አታስብልንም በማለት ነገር ነው፡፡ እዚያው መርማሪ ፖሊስ ባለበት ተናዶ ምኑን ነው እሺ የምለው? ብሎ ንዴቱን መቆጣጠር አቅቶት ባለቤቱን ሊያንቃት ሲይዛት ልጁ አባብላ አስለቀቀቺው፡፡ እኛ እሱ ስለአለን ነው፡፡ የምናውቀው ሚስጥር የለም፡፡ ሁሉንም የምታውቀው አንተ ነህ፡፡ አንተን እንደመሰለህ ብለን ትተነው ሄድን፡፡ ከዚያ በኋላ አንስተንበትም አናውቅም" ይላሉ፡፡ አቶ ዘሪሁን በመቀጠል "ለሁለት ወር ጨለማ ቤት አስገብተው ለብቻዬ አሰሩኝ፡፡ ሁለት ቀን ሙሉ ሰቅለው ሲቀጠቅጡኝ ውለው አደሩ፡፡ ጠባሳውን አሁንም ማሳየት እችላለሁ፡፡ ህክምናም እንዳላገኝ ተከለከልኩ" በማለት አቶ ዘሪሁን በጊዜ ቀጠሮ ይመላለሱ ለነበሩት ፍ/ቤት ገልፀዋል ነበር፡፡ አቶ ዘሪሁን ከማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ ወደ ቃሊቲ ማረሚያ ቤት ሲወርዱ ለዝግጅት ክፍላችን የላኩትን ደብዳቤ ሙሉ ጽሑፉን በሚቀጥለው ሳምንት ለአንባቢያን እናቀርበዋለን፡፡

በአሁኑ ጊዜ በዚህ አዋጅ በርካታ ሰዎች ተከሰው ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ መዝገቦች ውስጥ በቅርቡ የፍርድ ውሳኔ የተሰጠበትን የእነ ኤልያስ ክፍሌ የክስ መዝገብን እንመልከት፡፡ ጥር 17 ቀን 2004 ዓ.ም በ8፡30 የተሰየመው የፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት 3ኛ ወንጀል ችሎት ዳኞች እንዳሻው አዳነ፣ ሙሉ ጌታ ኪዳኔ፣ በሪሁን አራጋው ተሰየሙ፡፡ አቃቤ ሕግ ብርሃኑ ወንድማገኝ አንተነህ ጌታቸው ተከላካይ ጠበቆች የ2ኛ፣ የ3ኛና የ4ኛ ተከሳሽ ጠበቃ ደርበው ተመስጌን የ5ኛ ተከሳሽ ጠበቃ ሞላ ዘገየ ቦታ ቦታቸውን ይዘዋል፡፡ መዝገቡ የተቀጠረው የፍርድ ውሳኔ ለመስጠት ነበር፡፡

ይህንን ያሉት አቶ ዘሪሁን በ2ኛ ተከሳሽነት ተከሰሱና "በቃ" የሚል ጽሑፍ ማጻፋቸው ተረጋገጠ ተባለ፡፡ በሽብር ወንጀል አስተባባሪነትና ፈጻሚነት በተከሰሱበት ሦስት ክሶች "ጥፋተኛ ሆነው በመገኘታቸው 17 ዓመት እስራትና 50 ሺ ብር" ተፈረደባቸው፡፡ ከፍርድ በኋላ ወደ ዳኞች ጣታቸውን ቀስረው "እኔ ወንጀል አልፈፀምኩም፡፡ ጥፋተኛም አይደለሁም፡፡ ታሪክ ነፃ ያወጣኛል፡፡" በማለት ችሎቱን ለቀው ወደ ቃሊቲ ማረሚያ ቤት ሄዱ፡፡

ከተፈረደባቸው አምስት ቀን በኋላ አቶ ዘሪሁንን ማረሚያ ቤት ሄጄ አነጋግሬአቸው ነበር፡፡ በተፈረደባቸው ጉዳይ ምን ተሰማዎት? አልኳቸው፡፡ ፍርድ ቤት በፍርዱ ዕለት የተናገሩትን በመድገም ጀመሩልኝ፡፡ "እኔ ወንጀል አልሠራሁም፡፡ ጥፋተኛም አይደለሁም፡፡ ፍቃድ ያወጣነው ለመቃወም እንጂ ሸንኩርት ልንቸረችርበት አይደለም፡፡ የአቶ መለስ አገዛዝ መቀየር አለበት ብለን ስለአመንን "መለስ በቃ" እያልን ነው፡፡ "መለስ በቃ" ማለት ሽብርተኝነት አይደለም፡፡ ሥርዓቱ በዘረኝነት፣ በሙስና፣ በሰብአዊ መብት ጥሰትና በዴሞክራሲያዊ መብት አፈና ይታወቃል፡፡ የሥርዓቱ ፖለቲካ ከሰሯል፡፡ የሚያራምዱት የከሰረ ፖለቲካ ነው፡፡ የእኛን የክስ ሂደትና ፍርድ ስትመለከትም የከሰረ ፖለቲካ ውጤት መሆኑን ያሳያል፡፡ የፍርድ ሥርዓቱ በህግ አስፈጻሚው ሥር ወድቋል፡፡ ህግ አውጪውም በህግ አስፈጻሚው ሥር ነው፡፡ ህግ አስፈጻሚው በአምባገነንነት በትዕዛዝ ያሻውን ሲያስወስንና ሲያስፈጽም ይታያል፡፡ የምንታገለው የምናወግዘው ይህንን ነው፡፡ በቃ ያልነውም ይህንኑ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ራሳቸውም ያወጡት ህገ መንግስት ይፈቅዳል፡፡ ላወጡት ህገ መንግስትም አይገዙም፡፡ ፀረ- ህገመንግስት የሆነ አዋጅ አውጥተው ይንቀሳቀሳሉ፡፡ ምንም የሠራሁት ወንጀል የለም፡፡ ፍርዱ ፍርደገምድል ነው፡፡" ብለዋል፡፡ የፍትህ ሥርዓቱ በህግ አስፈጻሚው ሥር ወደቋል ብለዋል፡፡ ይግባኝ አትጠይቁም ማለት ነው? በማለት ጥያቄ አቅርቤላቸው ነበር፡፡ "ስለይግባኙ እያሰብንበት ነው፡፡ ከጠበቆቻችንና ከቤተሰብ እንዲሁም ከትግል አጋሮቼ ጋር ተመካክሬ እወስናለሁ፡፡ የፍትህ ሥርዓቱ ያለበትን ደረጃ ማሳየቱ ተገቢ ይመስለኛል፡፡ ውሳኔው ምንም ይሁን ምን ሥርዓቱን ለትውልድ ማሳየት ያስፈሊጋል፡፡" በማለት መልስ ሰጥተውኛል፡፡ በሚቀጥለው ሳምንት የጋዜጠኛ ውብሼት ታዬን እና መምህርት ጋዜጠኛ ርዕዮት ዓለሙን የፍርድ ሂደት እንዲሁም ከፍርዱ በኋላ ጠበቆች ቤተሰብና የህግ ባለሞያዎችን አስተያየት እንዳስሳለን፡፡

ፍኖተ -ነፃነት ጋዜጣ ሐምሌ 2003 ዓ.ም ተመሠረተ፡፡ ፍኖተ ነፃነት በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ሥር የሚታተም በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ፣ በወቅታዊ ጉዳዮችና በመዝናኛ ላይ የሚያተኩር የፓርቲው ጋዜጣ ነው፡፡

**ጋዜጣችን እንደ ፓርቲ ልሳን ብቻ ሳይሆን እንደ አንድ ሚዛናዊ የግል ጋዜጣ ሆኖ ማገልገል ይፈልጋል የማንኛዉም ሰዉ ሀሳብና አመለካከት የሚስተናገድበትና የሚንሸራሸርበት እንዲሆን እንሻለን ሰፊ የሚዲያ ሽፋን ያለዉ ኢህአዴግም በዚህ ሚዲያ አቋሙንና ፖሊሲዉን ለማቅረብ ቢፈልግ ክፍት ነዉ**

ዋና አዘጋጅ፡-
አንዳርጌ መሥፍን
አድራሻ፡-
የካ ክ/ከተማ ወረዳ 12
የቤ.ቁ አዲስ

አዘጋጆች፡-
ብዙአየሁ ወንድሙ
ብስራት ወ/ሚካኤል

አምደኞች፡- ዶ/ር ኃይሉ አርዓያ
ኢ/ር ዘለቀ ረዲ
ወንድሙ ኢብሳ
ስለሞን ስዩም
ግርማ ሞገስ
ደረጀ መላኩ
ቀለሙ ሁነኛው
በለጠ ጎሹ

ኮምፒውተር ጽሑፍ፡-
የሺ ሃብቴ
ብርቱካን መንገሻ

አከፋፋይ፡-
ነብዩ ሞገስ

አሣታሚው፡-
አንድነት ለዴሞክሲና ለፍትህ ፓርቲ(አንድነት)

አድራሻ፡- አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 07 የቤ.ቁ አዲስ

አታሚ፡- ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
አራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 07 የቤ.ቁ 984

የዝግጅት ክፍሉ

ስልክ +251 922 11 17 62
+251 913 05 69 42
+251 118-44 08 40
+251 923 11 93 74

ፖ.ሳ.ቁ፡ 4222

ኢሜይል፡- fnotenetsanet@yahoo.com
udjparty@gmail.com
andinet@andinet.org

ፋክስ ቁጥር፡- +251-111226288

# ርዕሰ አንቀፅ

## የመምህራኑ ጥያቄ መልስ ያሻዋል ! !

ሠላም ላንዲት አገር ሁለንተናዊ እድገት ሰፊ ድርሻ አለው፡፡ ያለ ሠላም ምንም ነገር የለም፡፡ ሠላም እንዲሰፍን ደግሞ የተረጋጋና ሠላማዊ አመራር ወይንም አሥተዳደር ያሻል፡፡ ሠላም ከደፈረሰ ግን የተሠራው ይፈርሳል፤የተገነባው ይናዳል፡፡

ሠላም የግእዝ ቃል ሲሆን “አማን፣ፍቅር፣መልካም፣ጥሩ ማለት ነው” ስለዚህ ሠላም የሁሉም ዋስትና የፍቅር ቁልፍ ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ እፅዋትና አዝርእት እንኳን ሠላም ያስፈልጋቸዋል፡፡ አዝርእት የተመጣጠነ ርጥበትና ያየር ፀባይ የሚያስፈልጋቸውን ያህል ሠላምም ያስፈልጋቸዋል፡፡ በእንክርዳድና በአረም ከተዋጡ የሚጠበቅባቸውን ጥራት ያለው ምርት መሥጠት አይችሉም፡፡ በቂ የሆነና ጥራት ያለው ምርት እንዲሰጡ ማረም ተገቢ ነው፡፡

ሠላም ስንልም ካንድ ወገን ብቻ ስለተፈለገ የሚገኝ አይደለም፡፡ ሁለት የተፋጠጡ ኃይሎች /ባላንጣዎች/ በመቻቻል፣በመተሳሰብ፣ ሰጥቶ በመቀበል፣አርቆ በማሰብ፣ነገና ከነገ ወዲያ ሊመጣ የሚችለውን መዘዝ በመገንዘብ በተፈጠረው አገራዊ ችግር ዙሪያ በመወያየት ለሠላም በርን መክፈት ሲቻል ነው፡፡ አቅም አለኝ፣ጉልበት አለኝ ብሎ የሠላም በርን ክርችም አድርጐ በመዝጋት የተፈጠረውን ችግር በኃይል ደፍጥጦ ለመፍታት መሞከር ውጤቱ የማይበርድ እሳት እንደ መለኮስ ይቆጠራል፡፡ ርግጥ ነው የኃይል ርምጃው ለጊዜው እፎይታ ሊያስገኝ ይችል ይሆናል፡፡ እሳቱን ግን ጨርሶ ማዳፈን አይቻልም፡፡ ዛሬ በሀገራችን በየቦታው ሲጨሱ የምናያቸው ጭሶች ኢህአዴግ በወቅቱ በሠላም ሊፈታቸው የሚገቡ ነገር ግን በኃይል ለማጥፋት የሞከራቸው ለመሆናቸው ማስረጃ አያቋጥረንም፡፡

ችግሮቻችንን በኀይል እንጂ በሠላም የመፍታት ተሞክሮ የለንም፡፡ ከታሪካችን የወረስነው በኃይል ሌሎችን መድፈቅና ጨርሶ ማጥፋትን ነው፡፡ ብዙ ርቀን ሳንሄድ የቀዳማዊ ኃ/ሥላሴና የደርግ ሥልጣን አያያዝና አወዳደቅ በቂ ማረጋገጫችን ነው፡፡ መሪዎቻችን ካንዱ ውድቀት ሌላው አይማርም፡፡ “ጉልቻ ቢቀያየር” እንዲሉ የፊተኛው በቀደደው የከፋት መንገድ የኋለኛው ከመጓዝ በስተቀር የሰላምን መንገድ የመምረጡ ጉዳይ አልሆነልንም፡፡ ለምን ቢባል በክፋት ተኮትኩተን፣ቂምና በቀልን ቋጥረን ያደግን በመሆናችን የበጎ ነገር ሥንቅ የለንም፡፡ በደርግና በኢህአዴግ ሥርዓት ውስጥ ተወልደው ያደጉ ሕፃናትና ወጣቶች ምን በጎ ነገር እንዲኖራቸው ይጠበቃል? የነጭና የቀይ ሽብር ቁስል ገና ሳይጠግግ /ሳይሽር/ በ85 ዓ.ም፣በ93 ዓ.ም፣ በ97 ዓ.ምና በ98 ዓ.ም የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው በተሰለፉ ወጣቶች ላይ በመትረየስ የሚያጭዱ በዙፋኑ ሲተኩ ወጣቶች ቢደነዝዝና ራእይ አልባ ቢሆኑ ምን የሚያስገርም ነገር ይኖራል?

እንደሚታወቀው ለቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ሥልጣን መናጋትና በመጨረሻም መውደቅ ትልቁን ድርሻ የተጫወቱት መምህራን ነበሩ፡፡ ወሩም የካቲት ወር 1966 ዓ.ም ነበር፡፡ ዳሩ ግን መምህራኑ ያቀረቧቸው ጥያቄዎችም ሆኑ የሕዝቡ መሠረታዊ የለውጥ ፍላጎት ደርግ ባቋራጭ ሥልጣን ላይ በመቀመጡ ተጨናግፈው ቀርተዋል፡፡

ደርግ “ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም” የሚል አማላይ መፈክር የዞ ቢነሳም የአገሪቱን መሠረታዊ ችግር ሊፈታ ባለመቻሉ” የሕዝብ ብሶት ወለደን” በሚሉ ከሥልጣኑ ተገፈትሮ ሊወድቅ ችሏል፡፡ ከመውደቁ በፊት ግን ብዙ የሠላም በሮች ተንኳኩተውለት ሳይጠቀመባቸው ቀርቷል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ኢሕአዴግም ለ20 ዓመታት ከሕዝብም ሆነ ከተቃዋሚዎች ለቀረቡለት የሠላም ጥያቄዎች ላንዳቸውም መልስ ሰጥቶ አያውቅም፡፡ ለሠላም እጅን መዘርጋትና በርን መክፈት በሱ ቋንቋ “ተንበርካኪነት ነው፡፡”

አንጋፋው የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ከ60 ዓመታት በላይ እድሜ ያለው ቢሆንም በየጊዜው ከሥልጣን ላይ የሚወጡ አምባ ገነን መሪዎች በሚያደርሱበት ጫና የአባላቱን መብት ሳያስከብር ቆይቷል፡፡

አንጋፋው የኢትዮጵያ መምህራን ማሕበር የኢሕአደግ ጡጫ ካረፈባቸው የመጀመሪያዎቹ የሲቪል ማህበራት መሀከል አንዱ ነው፡፡ ከመርጫ 97 ዓ.ም በፊት በዶ/ር ታዬ ወ/ሰማያት ይመራ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ንብረቱንና በባንክ ያስቀመጠውን ገንዘቡን ተማርኮ በኢሕአዴግ ሠራሽ አመራር መተካቱ የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡

መምህራን የተማረ የሰው ኃይል አፍሪዎች ወይንም የቀለም አባት መሆናቸው ተዘንግቶ ባለፉት 20 ዓመታት ውስጥ ለከፉ አደጋዎች ተጋልጠው መቆየታቸው የሚታወቅ ነው፡፡ ከሥራ ተፈናቅለዋል፤ አገር ጥለው ተሰደዋል፤ከደረጃ ዝቅ ብለዋል፤ የጎሣ ሥርዓት በፈጠረባቸው ምክንያት ተወልደው ካደጉበት ቀየ ተሰደዋል፤ ቀሪዎቹም አንድ ላምስት ተጠርንፈው ለሥርዓቱ ቢያጎበድዱም ጠብ የሚልላቸው ነገር አላገኙም፡፡ ሰብአዊ ክብራቸው ተገፎ በጋጠወጥ ካድሬዎች ግልምጫ ነጋ ጠባ እየተሸማቀቁ ለተማሪዎቻቸው ሊያበረክቱ የሚችሉትን ያህል እውቀታቸውን ማበርከት አልቻሉም፡፡ ነገሮች ሁሉ ጡዘውባቸዋል፤ በሥርዓቱ ብልሹነት ተንገሽግሸዋል፤ በመሆኑም መብታቸውን ለማስከበር ሲሉ “ታሪክ ራሱን ይደግማል” እንዲሉ ባሁኑ ወቅት የመብት ጥያቄ ይዘው ተነስተዋል፡፡

የኢትዮጵያ መምህራን የደመወዝ ስኬል ከሌሎቹ የሲቪል ሠራተኞች ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ ነው፡፡ ማህበሩ እንደ ሌሎች የሲቪል ሠራተኞች ደመወዙ እንዲስተካከልለት ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ሲወተውት ቆይቷል፡፡ በ2002 ዓ.ም የምርጫ ዋዜማ ጠ/ሚንስትሩ በመላ ሀገሪቱ የተውጣጡ መምህራንን አዲስ አበባ ላይ ሰብስበው ባነጋገሩበት ወቅት ይኸው የደመውዝ ጥያቄ ተነስቶ ነበር፡፡ ጠ/ሚኒስትሩ ጉዳዩን ወደ ሚመለከተው እንደሚመሩት ቃለ ገብተው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በ2003 ዓ.ም የሌሎች ሠራተኞች የደመወዝ ማሻሻያ ሲደረግ የመምህራን ግን በዝምታ መታለፉ የብዙዎችን ቆሽት አድብኗል፡፡ በዚህ ምክንያትም ጥቅምት 5 ቀን 2004 ዓ.ም ድሬዳዋ ላይ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባዔ አካሂዶ ነበር፡፡ በጉባዔው ፍፃሜ ወቅትም ባለአሥር ነጥብ የአቋም መግለጫ ያወጣ ሲሆን በተራ ቁጥር ሦስት የተጠቀሰው የደመወዝ ማሻሻያ ስኬልን የተመለከተ ነው፡፡ እንዲህ የሚል ይገኝበታል፡-

“የመምህራንን የሥራ ሞራል ለመጠበቅና የሥራ ተነሳሽነታቸውን ከፍ ለማድረግ - - - የደመወዝ ስኬል እንደ ሌሎቹ ተመሳሳይ የትምህርት ደረጃና አገልግሎት ካላቸው የሲቪል ሠራተኞች ጋር እኩል መሻሻል እንዳለበት አናምናለን፡፡ በመሆኑም እስከ ጠር 30 ቀን 2004 ዓ.ም ድረስ ምላሽ የሚሰጠበት ሁኔታ እንዲመቻችልን እንጠይቃለን- - - ” ይላል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን በየካቲት ወር 2004 ዓ.ም አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔው በሚወስነው ውሳኔ ሕጉ በሚፈቅድላቸው መሠረት ሥራ የማቆም አድማ እስከ መጥራት እንደሚደርስ ማሕበሩ አስጠንቅቋል፡፡ ይኸው ሥጋት አድሮባቸው ይመስላል፡፡ የኢሕአዴግ ታማኝ ካድሬዎች ሰሞኑን በየ ት/ቤቶች በመገኘት አባል መምህራንን በምስጢር በመሰብሰብ “ፀረ-ሕዝቦች መምህራንን የሥራ ማቆም አድማ እንዲያደርጉ እየቀሰቀሷቸው ነው፡፡ ነቅታችሁ ጠብቋቸው፤ ተከታተሏቸው - - -” በማለት አንዱን በሌላው ለማስተናነቅ የሞከሩት ሴራ ከሽፎባቸዋል፡፡ አብዛኞቹ መምህራን፡-

“አሁንስ በዛ፤እኛ የኢህአዴግ አባል የሆነው ጥቅምቻችን ለማስጠበቅ እንጂ ጥቅሞቻችንን አስነጥቀን የሙያ አጋሮቻችንን በጠላትነት ልንመለከት አይደለም!” በማለት መሟገታቸውን ከተጨባጭ መረጃ ለማወቅ ችለናል፡፡ ዋናው ነገር ማን ሀቅ ተናገረ፣ማን አታለለ የሚለው አይደለም፡፡ እነማናቸው “ፀረ-ሕዝቦች?እነማንስ ናቸው ለሕዝብና ለመምህሩ ጥቅም የቆሙት?” የሚለው ጥያቄ ግን መልስ ማግኘት አለበት፡፡

ደርግ ያሁኖቹን ባለጊዜ ባለሥልጣናት “ፀረ-ሕዝቦች፣ፀረ አብዮተኞች፣ገንጣይ፣ አስገንጣይ” ይለን ነበር፡፡ ኢሕአዴግ በፈንታው ሥልጣን በጨበጠ ማግሥት “ነፍጠኞች ትምክህተኞች፣ጠባቦች፣የአድሃሪያን ርዝራዦች” እያለ ዛሬም ድረስ በማያባራ ፕሮፖጋንዳ መጠመዱና ከእንዲህ አይነቱ አዙሪት አለመውጣቱ አሳፋሪ ነው፡፡ የሆነ ሆኖ የመምህራኑ የደመወዝ የማሻሻያ ጥያቄ “በፀረ-ሕዝቦች” መስፈራርቾ ተዳፍኖ መቅረት እንደሌለበትና በቂ መልስ ሊሰጣቸው እንደሚገባ እናምናለን፡፡ መምህራን የቀለም አባቶች ብቻ ሳይሆኑ የሠላም አባቶችም በመሆናቸው ከቾክ በስተቀር በእጃቸው ምንም ነገር የለም፡፡ ስለዚህ የነሱን ጥያቄ ባግባቡ አለማስተናገድ እንደ አንድነት ያሳስበናል፡፡ በሠላማዊመንግድ ያቀረቧቸው ጥያቄዎች በቀናነትና በአክብሮት ሊመለስላቸው ይገባል እንላለን፡፡ ይህ ሳይሆን ቀርቶ የሰላሙ በር ተዘግቶ ነገሮች መልካቸውን ቀይረው ለሚፈጠረው ችግር ኢሕአዴግራሱ ተጠያቂ እንደሚሆን ከወዲሁ ለማስገንዘብ እንወዳለን!!

*ጋዜጣችን “ፍኖተ-ነፃነት” ብለናታል፡፡ “ፍኖት” ማለት መንገድ ማለት ሲሆን ከነፃነት ጋር ሲጣመር “የነፃነት መንገድ” ማለት ነው!!*

# ነፃ አስተየት

## መሬት የሕዝብ ነው

ከበርናሱ በዛብህ

አዲስ የወጣው የከተማ ቦታ ሊዝ አዋጅ ችግር መነሻ በሕገ-መንግሥቱ ላይ የተደነገገው መሬት የመንግሥትና የሕዝብ ነው የሚለው ይመስለኛል፡፡ በመጀመሪያ፣በዓረፍተ ነገሩ ቅደም ተከተል “መንግሥት” በቅድሚያ መጠቀሱ አወዛጋቢ ነው፡፡ “መንግሥት” የሚመሠረተው በነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ከሕዝብ መሆኑ እየታወቀ፣”ሕዝብ” መቅደም ሲገባው፣”መንግሥት” ለምን ቅድሚያ እንደተሰጠው ግለፅ አይደለም፡፡

እንግዲያውስ “መንግሥት” በነፃና ፍትሐዊ መርጫ በሕዝብ የሚመረጥ የሕዝብ ወኪል እንደመሆኑ፣ ወካዩ ሕዝብ እያለ፣ወኪሉ “መንግሥት” ለምንስ በአንቀፁ ውስጥ ይጠቀሳል? በዚህ አስተሳሰብ መሠረት፣ “መሬት የሕዝብ ነው” የሚለው ብቻ በቂ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ይህን ስል ሕገመንግሥቱን ለማጣጣል መሞከሬ እንዳልሆነ እንደታወቅልኝ አፈለጋለሁ፡፡ ምክንያቱም ሕገ-መንግሥቱ አሁን ባለበት ሁኔታ እንኳን በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊና ፍትሐዊ ሥርዓት ለመገንባት ከበቂ በላይ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ ችግሩ ሕገ መንግሥቱን የፃፈው ኢህአዴግ ራሱ አያከብረውም፡፡ በመሆኑም፣የኢህአዴግ ዋና ጠላት መድረክ ወይም አንድነት ፓርቲ ሳይሆኑ፣ራሱ አርቅቆ ራሱ በየቀኑ የሚጥሰው ሕገ-መንግሥቱ ነው፡፡ ለማንኛውም፣ ሕገ-መንግሥቱ ራሱን ማሻሻያ አንቀፅ ስላለው፣ይህ ወደፊት ሕዝባዊ መንግሥት ሲቋቋም የሚነሣ ጉዳይ ይሆናል፡፡ እንደሚታወቀው፣ሕገ-መንግሥቱ የእግዚአብሔር ቃል ስላልሆነ ሊሻሻል ይችላል፡፡ የኃ/ሥላሴ ሕገ-መንግሥት ተሻሽሏል፤ የአሜሪካም ሕገ-መንግሥት ተሻሽሏል

ለአሁኑ ግን፣መሬትን በተመለከተ፣ሕገ-መንግሥቱ እና ለሕዝብ ቢያንስ እኩል መብት ሰጥቷል፡፡ አዲሱ የሊዝ አዋጅ ግን የህንን የእኩልመብት አንቀፅ በመጣል፣የመሬት ባለቤትነትን ለመንግሥት ብቻ የሰጠ ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡ በዚህም ምክንያት አዋጁ ሕገመንግሥቱን ይፃረራል እላለሁ፡፡

ከመሠረታዊ የኢኮኖሚ ንድፈ ሐሳብ አኳያ ደግሞ፣መሬት እግዜር ለሰው ልጅ በነፃ የሰጠው የተፈጥሮ ሀብት እንደመሆኑ፣በፅንሰ ሐሳብ ደረጃ በአንድ ሀገር ላለ ሕዝብ በመነሻው ላይ መሬት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ መከፋፈል እንደሚገባው ብዙ ምርምርና ጥናት የሚያስፈልገው አይመስለኝም፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በረጅም የጊዜ ሂደት መሬት እሴት (value) ብሎም ዋጋ (price) ያለው ሀብት እየሆነ በመምጣቱ፣ገበያ እንዲኖረው የግድ ይላል፡፡ እሴት ካለው ዋጋ የኖረዋል፤ዋጋ ካለው ገበያና የገበያ ዋጋ (Market price) ይኖረዋል፡፡ ከዚህ በመነሳት፣መሬት ሸቀጥ ነው፤ ይሸጣልም፣ይለወጣልም፡፡

የመሬት ባለቤትነትን በተመለከተ፣ሕዝብ ማለት ግለሰቦች ወይም የግለሰቦች ስብስብ እንደመሆኑ፣መሬት በግለሰቦች ወይም በወል /በማኅበር/ ባለቤትነት ሊያዝ እንደሚችል ግልፅ ይመስለኛል፡፡ በሌላ በኩል፣በሕዝብ ወኪልነት፣መሬት በመንግሥትም ይዞታ ሥር ሊሆን እንደሚችል ለመገንዘብ አስቸጋሪ አይደለም፡፡ በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ፣ “መሬት አይሸጥም፣አይለወጥም” የሚለው ዝርዝር ጉዳይ ስለሆነ፣በዚህ ዓይነት አጠቃላይ ሕግ ላይ መሥፈሩ ትክክል አይመስለኝም፤ ምክንያቱም መሬት የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑ ከተደነገገ ሕዝቡ መሬቱን እንዴት እንደሚይዘው በሕዝቡ ምርጫ የሚወሰን ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል፣ሕገ-መንግሥቱ መሬት አይሸጥም አይለወጥም” ይበል እንጂ ከላይ በተጠቀሰው መሠረታዊ የኢኮኖሚ ሕግ አስገዳጅነት እስከአሁን መሬት በግለሰቦችም፣በማኅበሮችም፣በመንግሥትም ሲሸጥ፣ሲለወጥ ቆይቷል፡፡ አዲሱ የሊዝ አዋጅ ግን የመሸጥ፣ የመለወጡን መብት ለመንግሥት ብቻ ለመስጠት የሚሞክር ነው፡፡ እርግጥ፣ግለሰቦች መሬት ሲሸጡ በቦታው ላይ በቆመው ቤት ላይ የመሬቱን ዋጋ በውስጡ ታዋቂነት እየደመሩ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ፣ “ሊዝ” የሚለው የእንግሊዘኛ ቃል በአማርኛ “ኪራይ” የሚለውን የሚተረጉም በመሆኑ የኢህአዴግ መንግሥት “ሊዝ” ኪራይ እንጂ ሽያጭ አይደለም ብሎ ይከራከራል፡፡ ነገሩ አልሸሹም ዞር አሉ ዓይነት ነው፤ምክንያቱም ለ99 ዓመት የተሰጠ ሊዝ የጊዜ ገደብ ያለው ሽያጭ ተብሎ ሊተረጐም ይችላል!

“መሬት አይለወጥም” የሚለውንም በተጨባጭ ተግባራዊ ለማድረግ እጅግ አስቸጋሪ ነው፡፡ ኢህአዴግ መሬትን የሚለውጠው በእጅ ለሚቆጠር የገንዘብ ረብጣ ሳይሆን፣በጆንያ ተሸክሸኮ ለሚቀርብ የብር ኖት ነው! ማለትም፣በካሬ ሜትር እስከ 20,000 ብር ስለዚህ መሬት ይሸጣልም፣ይለወጣልም!

ኢህአዴግ “አዲሱን የሊዝ አዋጅ ያወጣሁት ልማትን

ወደ 7 ዞሯል

# የጋምቤላ ነዋሪዎች . .




ትተርካለች፡፡ በወቅቱ መንግሥት ጋህነን ይደግፋሉ ያላቸውን ሰዎችና የገጠር ህዝብ ሲጨፈጭፍ በተመሣሣይ ጋህነንም ከመንግሥት ጋር ንክኪ አላቸው የሚላቸውን ሁሉ ይገድል እንደ ነበር ምሁሯ ታትታለች፡፡

ከደርግ ስህተት ማምለጥ ያልቻለው ኢህአዴግም በ2003 እ.ኤ.አ 7 ደገኞችና አንድ አኙዋክ በሞቱባት የመኪና ጥቃት አደጋ የተነሳ ብዙ መቶ አኙዋኮችን ለመጨፍጨፍ በቃ፡፡ በአቦቦ እና ጋምቤላ ከተሞች ቀጥሎ የነበረው የወቅቱ ጭፍጨፋ በተለይም አኙዋኮች ላይ በማነጣጠሩ የዘር ማጥፋት ወንጀል እንደነበር `international displacement monitoring center" በሰራው ጥናት አረጋግጧል፡፡

ፕ/ር ገብሩ ታረቀ "The Ethiopian revolution: war in the horn of Africa " በተባለ መፅሐፋቸው እ.ኤ.አ ከ1984-86 በነበረው የደርግ ሰፈራ ፕሮግራም ውስጥ ከተካተቱት 33,000 (ከአጠቃላዩ 5%) ሰዎች ከረሃብ እና የቆላ በሽታ / tropical disease) የተነሳ መሞታቸውን ፅፈዋል፡፡ 84,000 ወይም 14% ደግሞ የሰፈሩባቸውን አዲስ ቦታ ጥለው መሄዳቸውን አብራርተዋል፡፡

`ከመልካም ነገር መሸሽ`

የተዘረዘሩት የመንግሥት የሰፈራ ጣቢያ ዕቅዶች ህብረተሰቡን ከማሳመንም የዘለለ መሄድ እንደሚችሉ ይገመታል፡፡ በሌላ ገፁ በተለይ ሁለቱ የክልሉ ብሔረሰቦች -ኑዌር 46% እንዲሁም አኙዋክ 26% የስደት ሲሳይ መሆናቸው የፖሊሲውን አግባብ ጥያቄ ውስጥ የሚከት ነው፡፡ በጉዳዩ መንግሥትን በመከላከል የተጠመደው የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ሚኒስትር የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮምሽንን ሪፖርት ለኢትዮጵያ ያለመድረስ ተገን በማድረግ "መሠረተ ቢስ ክስና ሙሉ በሙሉ የፈጠራ ወሬ ነው" በማለት የኢቲቪን ቋንቋ ተውሰዋል፡፡ ሚኒስትሩ ሽፈራው ተክለማሪያም "በጭላንጭል እንኳ እውነታነት ቢይዝ ኖሮ የUNHCR ኦፌሰላዊ ደብዳቤ በደረሰን ነበር፡፡ እንዲህ የሚል ሪፖርት የለም፡፡ እንዲህ የሚባሉ ሰደተኞች ስለሌሉ" ሲሉ ደምድመዋል፡፡ ነገር ግን ጁን 17,2011 HRW ከ UNHCR ጋር ባደረገው የመረጃ ልውውጥ 1,474 የጋምቤላ ክልል ተወላጅ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች በኬኒያ እንደነበሩ አረጋግጠዋል፡፡ በቀጣዮቹ 7 ወራት 681 ስደተኞችን በማከል 2,155 የደረሱ ሲሆን በዚህ ወር ኬኒያ የስደተኞች ጣቢያ ከደረሱት እንኳ 5ቱ በ HRW ቃለ መጠይቅ ተደርጎላቸዋል፡፡ የ HRW ሪፖርት ያካተተው የአኙዋክ ብሄረሰብ አባላት ፎቶ ባህላዊ ዳንስ ሲከውኑ የሚያሳይ ሲሆን የሚታየው የሰው ቁጥር በሀገሩ ያለ እንጂ የስደተኛ ቁጥር እንኳ አይመስልም፡፡

የመጀመሪያው አመት የሦስት አመታት የጋምቤላ የሰፈራ ፕሮግራም፣ በኃይል መፈናቀል የተስተዋለበትን የቀድሞ ጊዜ አሰራር ያንፀባረቀ ነው፡፡ ለመመለስ ያለሙ ሠፈርተኞች ቤታቸው ተቀጥሏል፤ እህላቸው ወድሟል. . .፡፡ የኢፌዴሪ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ማንም ሰው ወደ ቀድሞ ቀዬው መመለስ ይችላል" ይላሉ፡፡ ነገር ግን ወደ ኋላ ለቀሩ ንብረቶች እንኳ መሄድ ለድብደባ እንደሚደረግ ይነገራል፡፡ በሰፈራ ጣቢያው ግንባታ የተሳተፈ አንድ የጋምቤላ ተወላጅ "ሽፍቶች ናችሁ ይሉናል፤ እናንተ ጥቁር ህዝቦች የኛ ባሪ ናችሁ ይሉናል፡፡" ሲል ተናግሯል፡፡

ልማት V5 ጥፋት

የኢፌዴሪ የገጠር ልማት ፖሊሲዎችን ያየ ሰው አቶ መለስ በአካባቢ ጥበቃ ጉዳይ ብቅ ቢሉ አይገርመውም፡፡ ምክንያቱም የተፃፈን ማወቅ ፊደላዊነት ነውና፡፡ ሰነዱ የሰፈራ ቦታዎች ልቅ ከሆኑና በነባር የተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ውድመት በሚያደርስ መልኩ ከተተገበሩ ከጥቅሙ ጉዳቱ እንደሚያመዝን ያብራራል፡፡ በተጨማሪም "መሬታችንን በአግባቡ መጠቀም ካልቻልን በሚፈለገው መጠን ፍጥነትና ቀጣይነት ያለው የግብርና ልማት ማረጋገጥ የማይቻል" መሆኑን ያብራራል፡፡ መንግሥት በአቋሙ ሲገፋ በተለይ የለም መሬቶች አጠቃቀም ትኩረት እንደሚሻው ይጠቅሳል፡፡

አፍሪካን በአለም ደረጃ በመወከል ስለ የከባቢ አየር ለውጥና ካሳው የሚወተውቱት አቶ መለስ ገንዘቡን ለልማታዊ መንግሥት ማስፈፀሚያነት ክፉኛ በመፈለጋቸው እንጂ የተፈጥሮ ተቆርቋሪነት ኖሯቸው አይደለም፡፡ አንድም ቀን በሀገር ውስጥ ቴሌቭዥን ቀርበው "ዛፍ ትከሉ" ካለማለታቸውም በላይ በአካባቢ ተቆርቋርዎች በሚነሱ ትችቶች ላይ የሚያቀርቡት ግብረ መልስ ስድብ መሆኑ ነገሮችን በእጅጉ ጥርጣሬ ውስጥ እንዲወድቁ አድርጓቸዋል፡፡

ማኦኢዝም?

በዚህ የመንግሥት ፕሮግራም ሌላው የቀውስ ምንጭ የሆነው ጉዳይ ማህበረሰቦቹ ለብዙ ዘመናት ከለመዱት የኑሮ ዘይቤ `ባንዲት ጀንበር` እንዲወጡ ለማድረግ የሚደረገው ጫና ነው፡፡ በተለይም ለዘመናት ከብቶቻቸውን ከቦታ ቦታ በማንቀሳቀስ ግጦሽ ባለበት ሁላ የሚከሰቱት አርብቶ አደሮች ወደ እርሻ ሙያ እንዲሸጋገሩ ሰፊ ጊዜ እና ስልጠና ያስፈልጋቸዋል፡፡ በሌላ መልኩ የኑሮ ዘይቤያቸውን ለመቀየር አይገደዱም ቢባል ስለሚሰጣቸው ተለዋጭ የግጦሽ መሬት፣ ደኖች እና አነስተኛ ማሳ ሳያግባቡ የቀድሞ መሬታቸውን መቀማት ከመንግሥት ጋር ሆድና ጀርባ ቢያደርጋቸው ተፈጥሮአዊ ነው፡፡ ነገር ግን መንግሥት ይህንንም መፍታት የሚፈልገው የማኦ አካሄድ በመከተል "ጉልበት ያለው ርትዕ አለው" በሚል ሆኗል፡፡

በተለይ ተገቢ ካሳ ማግኘት ሲገባቸው የቃል ማፅናኛ እንኳ ማጣታቸው ብዙዎች "የኢህአዴግ መንግሥት ለራሱ ሲሆን በተመቸው ሁሉ ህገ መንግሥቱን ይሸነቁራል" በማለት በአንቀፅ 44/2 መሠረት የነበሯቸውን የመካስ መብት ጠቅሰዋል፡፡ ሰሙጉም በዚሁ ሰሞን በዋጣው 35ኛ መደበኛ መግለጫው የዚህ አንቀፅ ያለመከበር ያስቆጣው ይመስላል፡፡

"ሳታመኃኝ ብላኝ"

ከአፋር እና ሶማሌ ክልል የሰፈራ ፕሮግራምም አንድ ደረጃ ከፍ በማለት "ለተሻለ አገልግሎት እና መሠረተ ልማት ተደራሽ እንዲሆኑ ነው" የተባለው የጋምቤላ ጉዳይ መሠረታዊ የተባሉት እንደ ት/ቤት፣ የእርሻ መሣሪያ፣ መሬትና ውሃ ባለመኖራቸው ልጆች ት/ቤት እንደማይሄዱ፣ ሴቶች ውሃ ፍለጋ ረዥም መንገድ በማቋረጣቸው በወታደሮች መደፈር እንደገጠማቸው የሙላቱ ውብኔ ጥናት ያሳያል፡፡ HRW በባለፈው አመት ብቻ 20 ሴቶች በመንግሥት የደህንነት ሀይሎች መደፈራቸውን ይገልፃል፡፡

ብዙዎች ታዛቢዎች መንግሥት ያለውን ሀቅ ለመናገር ባይደፍርም "በሰፈራ ፕሮግራሙ የተያዙት ህዝቦች የያዙት መሬት መንግሥት ለማከራየት በሰፊው ያቀደባቸው ናቸው" ሲሉ ይሞግታሉ፡፡ ከ2008 እ.ኤ.አ ጀምሮ የኢትዮጵያ መንግሥት 3.6 ሚሊዮን ሄክታር መሬት አከራይቷል፡፡ ይህ ማለት ኔዘርላንድ/ሆላንድ ከምትባለው ሀገር ጋር እኩል የሆነ መሬት ማለት ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት 2.1 ሚሊየን ተጨማሪ መሬት በፌዴራል መንግሥት የመሬት ባንክ በኩል ለግብርና ኢንቨስትመንት ተዘጋጅቷል፡፡ ጋምቤላን በተመለከተ የክልሉ 42% የክልሉ መሬት ወይ ለኢንቨስተሮች ተላልፏል አሊያም ለገበያ ቀርቧል፡፡ የዚህ ሰፈራ ፕሮግራም ለተነሺዎቹ ጥቅም ያለመሆኑን ለመናገር አብዛኛዎቹ ተነሺዎች ወደ ግል ባለሀብቶች ከተላለፈው ወይም ለገበያ ከቀረበው መሬት መሆኑን በማየት መገመት አይከብድም፡፡

አብዛኛውን ጋምቤላ እንደ ኮርፖሬት ፊውዳሊዝም ስርዓት የገዛው ካራቱሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የኢሌ (Ilea) ነዋሪዎችን ወደ ፈለገው አካባቢ አስፍሮ የሚነሱበትን ቦታ መውሰድ እንደሚችል ከክልል መንግሥቱ ፍቃድ እንደሰጠው የHRW ጥናት ያጋልጣል፡፡

መንግሥት በስራ ላይ የሚገኙት አርሶአደሮች ትምህርት ቤት ያልሄዱ መሆናቸውን ያብራራል፡፡ በሌላ በኩል ካራቱሪ የተባለው የዘመኑ `Corporate feudal` የህንድ ኩባንያ "የሩዝ አመራረትን ከጋንቤላ ገበሬዎች ለመማር ተዘጋጅቻለሁ" ሲል ቀልድመሰል አሳብ ሰጥቷል፡፡ የHRW ሪፖርት የሰፈራ ፕሮግራም እና የመንደር ምስረታ ለኢትዮጵያ አዲስ እንዳልሆነ ገልፆ ደርግ ለፖለቲካ ፍጆታ ኢህአዴግ ደግሞ ከማኦኢዝም የተቀዳ ይመስል ከማህበረ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ትራንስፎርሜሽን ስም በጋምቤላ ክልል እንደ ፋሽን ተያይዟታል ብሏል፡፡

መንግሥት በክልሉ ጉዳይ የተሻለ ነገር ፍለጋ እጁን እንደሰደደ ቢናገርም HRW ያገኘሁት የጥናት ውጤት ከዚህ የተለየ ነው ይላል፡፡ እንዲያውም በተቃራኒው መሆኑን ትኩረት ሰጥቶ ያወሳል፡፡ HRW ለኢትዮጵያ መንግሥት ባቀረበው ጥሪ "ዳግም ሰፈራ የህብረተሰቡን ትክክለኛ ፍቃደኝነትና ካሳ ማካተት ግድ የሚለው መሆኑን እና ትክክለኛ የሕግ አሰራር በሌለበት ለገበያ ተኮር ግብርና ተብሎ በጅምላ ማፈናቀል የኢትዮጵያን ህገ መንግሥት የሚጣረስ እንዲሁም የባላገሩን ህዝብ መብት ከዓለም ህዝብ አንፃር መጣስ ነው" ሲል አስፍሯል፡፡

የኢህአዴግ መንግሥት ትኩረት በብጥስጣሽ መሬት ያለውን ገበሬ ወደ ምርታማነት ማሸጋገር መሆኑን ከ1985 ዓ.ም ጀምሮ የሚወጡ የገጠር ልማት ሰነዶች ያረጋግጣሉ፡፡ የዐፄው መንግሥት በግብርና ልማት ትኩረት ማጣት ተወቅሶል፡፡ በኋላም በሦስተኛው ዙር የአምስት አመት ፕላኑ (1961-1973) ትኩረቱን ወደ እርሻ ሲያዞርም ቅድሚያ የተሰጠው አብዛኛው ሰው ለሚይተዳደርበት የግብርና መስክ ሳይሆን በውጭ ንግድ ላይ ላተኮረው የንግድ እርሻ ነበር፡፡ የልማታዊ መንግስት ስኬት ተቀባይነታቸው መሠረት ያደረጉት አቶ መለስም ገንዘብ ከተገኘ የማይሸጥ ያለ አይመስላቸውም፡፡ በ1994 ሰነድ መንግስት ጤንነቱ ያልተረጋገጠ ገበሬ የእርሻ ምርታማነትን በምንም መልኩ ማረጋገጥ እንደማይችል ይገልፃል፡፡ ፕሮግራሙ እንዲያውም ቅድመ መከላከል ላይ ማተኮር እንዳለበት ያሰምርበታል፡፡ ሆኖም HRW የጋምቤላ ሰዎችን መፈናቀል በተመለከተ ምንም የጤና፣ የትምህርት፣ የግብርና፣ የውሃ ተቋማት እንዳልተሟሉላቸው በመግለጽ ነው፡፡

# እናንተ ይህንን . . .

ከገፅ 15 የዞረ

አይችልም" በሚል ዘይቤ ብቻ ያላዩትን ቢፈርዱ ከኢህአዴግ የሚለያቸው ነጥብ ይጠፋል፡፡

አንድ ህፃን ከተወለደ ጀምሮ በአንድ ክፍል ውስጥ እንዲያድግ ቢደረግ፣ እናቱም ከጡት ውጭ ምንም ባታወራው የቱንም ያህል ዕድሜው ቢሄድ ቋንቋን መናገር አይችልም፡፡ ምክንያቱም አልተለማመደውምና ነው፡፡ ይህን ልጅ ቋንቋ እንዲማር ሳይደረግ አይችልም ማለት እንዴት ይቻላል፡፡ ይህን ልጅ ቋንቋን አለማምዶ መናገር ባይችል የአዕምሮ ዝግመት አለበት ሊባል ይቻላል፡፡ ነገር ግን ልጁ ቋንቋ እንዳይለማመድ በማድረግ ማውራት እንዳይችል ያደረጉት ቤተሰቦቹ ስለሆኑ ተወቃሾቹ እነርሱ ናቸው፡፡

ከግብፅ፣ ከቱንዚያና ከሊቢያ አለቆች መማር ያለበት ኢህአዴግ ብቻ ሳይሆን የተቃዋሚ መሪዎች ጭምር መሆን አለባቸው፡፡ በግብፅ የተካሄደውን አብዮት ስንመለከት ተሳታፊዎች በአብዛኛው ከ30ዎቹ ያልዘለሉ ወጣቶች ናቸው፡፡ የ30 ዓመት ወጣቶች ሆሲኒ ሙባረክ ስልጣን ሲይዙ ያልተወለዱ ናቸው፡፡ አንድ የ40 ዓመት ጎልማሳንም እንደ ምሳሌ ብናነሳ ሆሲኒ ሙባረክ ስልጣን ሲይዝ የ9 ዓመት ልጅ የነበረ ነው፡፡ ግን እነዚህ ወጣቶች የራሳቸውን የተለያየ ምልከታ ተጠቅመው አባቶቻቸው በነፍጥ ለበርካታ ዓመታት የታገሉትን በ18 ቀን ያለነፍጥ ከጫንቃቸው ላይ አሽቀንጥረው ጣሉ፡፡ የለውጡ ተጠቃሚ የሚሆኑት ግን ወጣቶቹ ብቻ ሳይሆኑ ሁሉም የህብረተሰቡ ክፍል ናቸው፡፡ ውስጠ ወይራ ፍላጎቷን አንግባ የምትንቀሳቀሰው አሜሪካና ሙባረክ ከሌሉ ግብፅ እንደማትኖር የሚሉ ጠንቋዮች እንዲሉት ሳይሆን ግብፅ እስካሁን አለች፤ ሀገሪቱ አሁንም ያልተረጋጋችው የወታደራዊ ሃይሉ አዘናግቶ ስልጣኑን ሊቆናጠጥ ሲል ህዝቡ "18 ቀን ላንቃችን እስቲሰነጠቅ የሌሊት ብርድ፣ የቀኑ ሐሩር ሳይበግረን የታገልነው ለዴሞክራሲ እንጂ የወታደራዊውን ሀይል ወንበር ለማስጨበጥ አይደለም" በሚል ነው፡፡ ሳይቃጠል በቅጠል ብለው እየታገሉ ያሉት፡፡ ከተቃጠሉ እንኳን በቅጠል በእሳት አዳጋም አይጠፋምና ገና በእንጭጩ ለመቆጣጠር መሞከራቸው አበጃችሁ ያሰኛል፡፡

ከዚህ አንፃር ወጣቱ በራሱ ጊዜ ሃላፊነት መሞከራቸው አበጃችሁ ያሰኛል፡፡ ይመታዋል፤ እየተባለ ፀሐይ ብርሃን ሳያገኝ ያደገ ህፃን አጥንት አጣሜ/ሪኬትስ/ እንደሚይዘው ሁሉ፣ አይችልም በሚል ሰበብ ሀላፊነትን እንዳይለማመድ ተደርጎ ያደገ ትውልድ ሽብር በሚባለው /ወኔ አጣሜ/ በሽታ ይለከፍና በአንዳንድ አፍሪካ ሀገራት እንደሚታየው ደንታ ቢስ ወጣት እንደ አሸን እንዲፈላ ያደርጋል፡፡ በዚህ ረገድ ኢህአዴግ "መተካካት" ብሎ በሰየመው አካሄድ አዛውንቶቹን በወጣቶች ይተካል ሲባል በወጣቶች ያለማመን አባዜው ተነስቶ ሽማግሌዎችን በሽማግሌዎች ለመተካት ከማውራት ያለፈ አዲስ ፊት አላመጣም፡፡ ተቃዋሚዎች ጡረታ ወይም ሞት ያሉ ይመስላሉ፡፡

በወጣት መሪዎች መተካት ቢችል ኖሮ ደሞክራሲያዊነቱና ነፃ ምርጫ በሀገራችን ሊሰፍን ይችል ይሆናል፡፡ በተቃዋሚውም በኩል ወጣቱ ኃላፊነት ቢሰጠው 20 ዓመታት እድሜ የፈጀባችሁን የትግል ጊዜ ከምትገምቱት ጊዜ ባነሰ ሊያሳካ ይችላል፡፡ ሁል ጊዜ "ይህን አትችሉም" አትበሉ፤ እናንተ የቻላችሁትን እንደመለኮታዊ ፀጋ የተሰጣችሁ ከሆነ እኛም ፀጋውንና ፅናቱን እንደእናንተ እንድናገኝ እንድንፀልይ ያለበለዚያ አባቶች አስተምረዋችሁም ከሆነ አስተምሩን፡፡ ለማንኛውም የአሁኑ ወጣት የተሻለ መሸከም የሚችል ጠንካራ ትውልድ መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡

ሳምንት ይቀጥላል፡፡



**አቶ ሽመልስ ሀብቴ ይባላሉ፡፡ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የተከታተሉት በተወለዱበት አርሲ ክፍለ ሀገር አርባጉጉ በሚባል ቦታ ሲሆን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ በአዲስ አበባ ተከታትለዋል፡፡ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በታሪክ፣ የሁለተኛ ዲግሪያቸውን (MA) በትምህርት ሥራ አመራር ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተመርቀዋል፡፡ በተጨማሪም በአስተዳደር ዘርፍ (በማኔጅመንት) የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ሲሆን በመምህርነትና በተለያዩ የአስተዳደር ጉዳዮች የመንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ አገልግለዋ እያገለገሉም ይገኛሉ፡፡ ከባልደረባችን ብስራት ወ/ሚካኤል አጭር ቆይታ ስላደረጉ እንድታነቡ በአክብሮት ጋብዘናል፡፡**

# እያንዳንዱ ዜጋ የከተማ ቦታን በነፃ እንዲያገኝና የመሬት ባለቤት እንዲሆን እንሰራለን

➢ አቶ ሽመልስ ወደ ፖለቲካው ህይወት መቼ ገቡ? እንዴት?

ወደ ፖለቲካው ህይወት ከገባሁ የቆየሁ ቢሆንም ወደ ተደራጀ ፖለቲካ የገባሁት ግን በ1993 ዓ.ም በወቅቱ ጥሩ ይንቀሳቀስ በነበረው ኤዴፓ ውስጥ ነው የጀመርኩት፡፡ ወደ ፖለቲካው እንድገባ የተገደድኩት የሀገሪቱና የማኅበረሰቡ ነባራዊ ሁኔታና የመንግስት ኢ-ፍትሐዊና ብልሹ አሰራሮችን ስታይ እንደ ዜጋ ከእኔ ምን ይጠበቃል በሚል ቁጭት የተባለሹ ነገሮች ከሌሎች ወገኖቻችን ጋር በጋራ በመሆን ለማስተካከል ወደ ፖለቲካ ትግሉ ገብቻለሁ፡፡ የአንድነት መስራች አባልነት ጀምሮ የብሔራዊ ምክር ቤት አባል በመሆን እያገለገልኩ ሲሆን ፓርቲው ከሌሎች በተሻለ መልኩ ጥሩ ፕሮግራም ስላለው አብሬ የድርሻዬን እየተወጣሁ እገኛለሁ፡፡

➢ በአንድነት ፓርቲ ውስጥ ያለዎት የስራ ድርሻ ምንድነው?

በፓርቲ ውስጥ ከዚህ በፊት የውጭ ጉዳይ ምክትል ኃላፊ በመሆን፤ ከዚያም የህግና ሰብዓዊ መብት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ በመሆን አገልግያለሁ፡፡ በአሁን ወቅት የአንድነት ፓርቲ ሥራ አስፈፃሚ አባል እና የማኅበራዊ ጉዳዮች ሰብሳቢ በመሆን እያገለገልኩ እገኛለሁ፡፡

➢ በእርስዎ የሚመራው ክፍል በዋነኝነት የሚያከናውነውን ተግባር ቢጠቅሱልኝ

የማህበራዊ ዘርፍ በአብዛኛው የሚያተኩረው ጥናትና ምርምር ዘርፍ ላይ ነው፡፡ በተለይ በሀገሪቱ ያሉ ማኅበራዊ ችግሮችን ለይቶ ማጥናት፣ የመፍትሄ አቅጣጫ መጠቆምና ፓርቲው በማህበራዊ ዘርፍ ሊከተለው የሚገባውን ፖሊሲ በመፈተሽ ተጨማሪ ያስፈልጋሉ የሚባሉ ካሉ ከፕሮግራሙ በመነሳት በፖሊሲ ውስጥ እንዲካተቱ ማድረግ፡፡ በተጨማሪም ፓርቲው በሚያካሂደው የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ በማህበራዊ ዘርፍ አዳዲስ ካሉ በፕሮግራሙ መካተት የሚገባቸውን በመጠቆም ንድፍ የሚያወጣና የሚሰራ ክፍል ነው፡፡

➢ በእናንተ እይታ የማኅበረሰቡ የኑሮ ሁኔታን እንዴት አያችሁት?

በኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ ማህበራዊ ችግሮች አሉ፡፡ በሀገሪቱ ከፍተኛ የማህበራዊ ቀውስ ይታያል፤ ከፍተኛ የኑሮ ውድነት፣ በጣም ከፍተኛ የሆነ ስራ አጥነት አለ፣ የሀገሪቱ ዜጐች በሀገራቸው መኖር የማይፈልጉበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል፡፡ በማህበረሰቡ ስደት ተበራክቷል፤ በትምህርት፣ በጤና፣ በመጠለያ (በቤት)፣ በምግብ አቅርቦት፣ በዋጋ ንረት እና በመሳሰሉት ከፍተኛ ችግሮች ላይ ወድቋል፡፡ በዚህም ምክንያት የኢትዮጵያ ህዝብ በአሁን ወቅት የተሻለ ማህበራዊ ኑሮ ለማግኘት ለውጥ እንደሚፈልግ ነው የተገነዘብነው፡፡

➢ ይሄ የሆነው ለምን ይመስላችኋል?

ግልፅ ነው፡፡ ይህ የማህበራዊ ችግር የተፈጠረው የገዥው ፓርቲ የሚከተለው የተሳሳተ የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ያላገናዘበ ፖሊሲና የብልሹ አስተዳደር ጫና ነው፡፡ አንደኛ ገዥው ፓርቲ የሚከተላቸው ፖሊሲዎች ህዝብን ያሳተፈና ያማከረ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ገዥው ፓርቲ ለራሱ ሰዎች የሚጠቅመውን ፕሮግራም ነው ህዝቡ ላይ እየጫነ ያለው፡፡ በአብዛኛው የሚነደፉ ፖሊሲዎች የተጠኑ አይደሉም፡፡ የወጡ የተሳሳቱ ፖሊሲዎች ተግባር ላይ ሲውሉ ችግሮች ሲፈጠሩ እንኳ ኢህአዴግ ለማሻሻል ፈቃደኛ አይደለም፡፡ ስለዚህ ሁሉን ነገር የሚያየው ከራሱ የስልጣን ቆይታ አንፃር በመሆኑ በሀገሪቱ ያሉ ማህበራዊ ችግሮች ከዕለት ወደ ዕለት እየተባባሱ መጥተዋል፡፡ በአጠቃላይ እነዚህ የተወሳሰቡ ችግሮች የተፈጠሩት የገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ በሚከተለው የተሳሳተ ፖሊሲ መሆኑን ነው የተገነዘብነው፡፡

➢ የጠቀሷቸው ችግሮች እንዲስተካከሉ ምን መደረግ አለበት ብላችሁ ታምናላችሁ?

ኢህአዴግ ህዝብን ማዳመጥ መቻል አለበት፡፡ የህዝብን ችግር በጥልቀት ማየትና መመርመር፣ ከሁሉም ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በሀገሪቱ እና በህዝቡ ጉዳይ በጋራ መወያየት፣ መነጋገር እና መስራት አለበት፡፡ ኢህአዴግ ራሱን ለለውጥ ማዘጋጀትና ራሱ ብቻውን የሀገሪቱ ፈላጭ ቆራጭ እንቅስቃሴን ገታ በማድረግ ዞሪያ ገባውን ማየትና የሀገሪቱ ችግሮች የሚፈቱበትን ሁኔታ መቀየስ ይኖርበታል ብለን እናምናለን፡፡

➢ እናንተ ወይም ፓርቲያችሁ ሥልጣን ቢይዝ የኢትዮጵያ ህዝብ ማኅበራዊ ኑሮ እንዲሻሻል

**የሴቶች እኩልነት በተግባር ማረጋገጥ፤ የህፃናት የተሻለና ምቹ የአስተዳደግ ሁኔታ እንዲያገኙ መስራት፡፡ ትምህርትን ከልማት ጋር በማስተሳሰር ከፖለቲካ ተፅዕኖ ነፃ ማድረግ እና ዜጐች በነፃነት ሐሳቦቻቸውን በመግለፅ በራስ የመተማመን ስሜታቸው እንዲጨምር በማድረግ መስራት፤ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ከፖለቲካ ተፅዕኖ ነፃ ሆነው ሰርተው ሀብት እንዲያፈሩ፣ ገበያ መር የሆነ ኢኮኖሚን ተጠቅመው ወገኖቻችንን በመጥቀም አለኝታነታቸውን እንዲያረጋግጡና በሀገሪቱ ልማት የራሳቸውን ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማበረታታት ጥቂቶቹ ማኅበራዊ ኑሮን የሚመለከቱ ፖሊሲዎቻችን ናቸው**

## ቆይታ

ምን ለማድረግ አስባችኋል?

በአሁን ወቅት በርካታ የተወሳሰቡ ችግሮች አሉ፡፡ እነዚህንም ችግሮች ለመፍታት ፓርቲው ወደ ስልጣን ሲመጣ ከፍተኛ ኃላፊነት ይጠበቅበታል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ፓርቲው በፕሮግራሙ ያስቀመጣቸው በርካታ ጉዳዮች ያሉ ሲሆን አንዱ ማኅበራዊ ኑሮን የማሻሻል ጉዳይ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ፓርቲያችን የመድረክ አንድ አባል ድርጅት ነው፤ የመድረክም ፕሮግራም አለ፡፡ ፕሮግራሙ ላይ ያሉት ተፈፃሚ የሚሆኑትም ህዝብን ባሳተፈ መልኩ እንዲሆን በግልፅ ተቀምጧል፡፡ ፖሊሲዎቹም በአግባቡ ማኅበረሰቡንና የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ተጠንተው እንደወጡ ሁሉ ተግባራዊነታቸውም እንዲሁ ሀገሪቱንና ማህበረሰቡን ያገናዘበ እንዲሆን አስቀምጠናል፡፡ ፖሊሲዎቹ ሲተገበሩ እንኳ ችግር የሚፈጠርባቸው ካሉ ወዲያውኑ ጥልቀት ያለው ጥናት በብቁ ባለሙያዎች ተጠንቶ ህዝብን ባሳተፈ መልኩ እንዲሻሻል ይደረጋል፡፡ ምክንያቱም የወቅቶች እና ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያላቸው ለውጦች ሲመጡ የእኛም ህዝብ እንዳይጐዳ አስፈላጊ ማስተካከያ እንዲወስድ ይደረጋል፡፡ ይሄ ደግሞ አንድ መንግስት ለሀገሩና ለህዝቡ የቆመ ሲሆንና ወገኑን ለመጥቀም የሚወስደው እርምጃ ነው፡፡ ፓርቲያችንም በህዝብ ፈቃድ ሥልጣን ቢይዝ የሚያደርገው ይህንኑ ነው፡፡ የዜጐች ኑሮም እንዲሻሻል፣ አረጋውያን ተከብረው እንዲጦሩ፣ ህፃናት ብሩህ ተስፋ ኖራቸው ጤናማና ደስተኛ ሆነው እንዲያድጉ እና እንዲማሩ፣ ዜጐች ሁሉ በሀገራችን እኩል ሆነው በሀገራቸው ተከብረው በዓለም አቀፍም እጅግ ተቀባይነት ያላቸው ኩሩ ዜጋ እንዲሆኑ እንሰራለን፡፡

- አሁን ከኢህአዴግ የተለየ እና ለሕዝብ በተለይም ማኅበራዊ ህይወትን ለማሻሻል ይጠቅማል ብላችሁ ከምትከተሉት ፖሊሲ መካከል ጥቂቱን ቢገልፁልኝ

አንድነት/መድረክ የሕዝብ ድጋፍ አግኝቶ ስልጣን ቢይዝ እያንዳንዱ ዜጋ የመኖሪያ ቤት የመስራት አቅም ካለው የከተማ ቦታ በነፃ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡ ቤት የመስራት አቅም ለሌላቸው ደግሞ በመንግስት ወጪ ይሰራና በዝቅተኛ ዋጋ በረጅም ዓመታት ክፍያ ለነዋሪዎች እንዲዳረስ ይደረጋል፡፡ ምክንያቱም አንድ ዜጋ ዜግነቱ የሚረጋገጠው በሀገሩ መሬትና ሀብት የባለቤትነት መብት ሲረጋገጥ ነውና፡፡

የወጣቶችን የስራ ተነሳሽነት በማበረታታት ከየትኛውም የፖለቲካ ተፅዕኖ ነፃ በሆነ መልኩ ብድርና ስልጠና እንዲያገኙ ማመቻቸት፣ በሀገራቸው ሰርተው እንዲከብሩና የስራ ዕድል እንዲፈጥሩ ድጋፍ ማድረግ፡፡

የወጣቶችን የስራ ፍላጐት በማየት መንግስት ከሚሰጠው በተጨማሪ ያስፈልገናል ያሉትን ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፡፡

አርሶ አደሮች (በገጠር የሚኖሩ ወገኖቻችን) በቂ የእርሻ መሬት የቴክኖሎጂ ግብዓቶች እንዲያገኙ መስራት፣ መስኖ ማስፋፋት፣ በትምህርት እንዲታገዙ ማድረግ፡፡ በቂ መሠረተ ልማት በአቅራቢያቸው እንዲያገኙ የእነሱን ፈቃድና ፍላጐት መሠረት በማድረግ ማዘጋጀት እና ከውጭ የሚመጡ ግብዓቶች (ትራክተር፣ ማዳበሪያ፣ ምርጥ ዘር) በሀገር ውስጥ እንዲመረቱና አርሶ አደሩ በዝቅተኛ ዋጋ እንዲያገኙና የመሬት ባለቤትነቱን ማረጋገጥ፤

አርብቶ አደሮችን የአሰፋፈር ሁኔታ በማጥናት በቂ የግጦሽ መሬት እንዲያገኙ መሬቱም እንዲለማ የመስኖ ውሃ፣ የህክምና እና የትምህርት ተቋማትን ከነመጠለያ ማስፋፋት



የመከላከያ፣ የደህንነት እ የፍትህ ተቋማት ከየትኛው የፖለቲካ ድርጅት ነፃ ሆነው ለሀገሪቱ የቆሙ ሆነው መንግሥት ሲቀያየር የማይቀያየሩ ጠንካራ ገለልተኛ ተቋም እንዲሆኑና የዜግነት መብቶቻቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማረጋገጥ እና ማስቻል

የትምህርት ጥራትን በማስጠበቅ ተማሪዎቹ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሀገሪቱን ባለሙያዎች ዕውቀትና አቅም የሙያ ነፃነትን በጠበቀ መልኩ ጥናት አቅርበው ከሀገሪቱ ተጫባጭ ሁኔታ ጋር እንዲተገበሩ ማበረታታትና ማስቻል፤ የጐልማሶችን ትምህርት በማስፋፋት ሁሉም ዜጋ ትምህርት የሚያገኝበትን ዕድል መፍጠርና ማረጋጥ፡፡ የሀገራችንን ተፈጥሯዊ ሀብት፣ ታሪክ፣ ቅርሶች እና ባህሎችን (እሴቶችን) በመጠበቅ ለቀጣዩ ትውልድ ሳይበከሉ እንዲተላለፉ ጠንክሮ በመስራት ማረጋገጥ

የኃይማኖት ተቋማት ከማንኛውም የመንግስት እና የፖለቲካ ተፅዕኖ ነፃ ሆነው ዜጐች በነፃነት አምልኮአቸውን እንዲፈፅሙ በተግባር ማረጋገጥ፤

የሴቶች እኩልነት በተግባር ማረጋገጥ፤ የህፃናት የተሻለና ምቹ የአስተዳደግ ሁኔታ እንዲያገኙ መስራት፡፡ ትምህርትን ከልማት ጋር በማስተሳሰር ከፖለቲካ ተፅዕኖ ነፃ ማድረግ እና ዜጐች በነፃነት ሐሳቦቻቸውን በመግለፅ በራስ የመተማመን ስሜታቸው እንዲጨምር በማድረግ መስራት፤ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ከፖለቲካ ተፅዕኖ ነፃ ሆነው ሰርተው ሀብት እንዲያፈሩ፣ ገበያ መር የሆነ ኢኮኖሚን ተጠቅመው ወገኖቻችንን በመጥቀም አለኝታነታቸውን እንዲያረጋግጡና በሀገሪቱ ልማት የራሳቸውን ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማበረታታት ጥቂቶቹ ማኅበራዊ ኑሮን የሚመለከቱ ፖሊሲዎቻችን ናቸው፡፡

- ከላይ የጠቀሳችኋቸውን ለመተግበር አቅሙንስ ከየት ታመጣላችሁ?

በመጀመሪያ ደረጃ አቅማችን ህዝባችንና የተፈጥሮ ሀብታችን ነው፡፡ ምክንያቱም ህዝብን መሠረት ያደረገና ያሳተፈ ፖሊሲ ካለ የሀገር ህዝብ እውቀትም፣ ገንዘብም፣ ጉልበትም ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ የሀገሪቷን የተፈጥሮ ሀብትም በህዝቡ ፈቃድና አቅም በአግባቡ በመጠቀም ተነሳሽነትንና ፍትሃዊ የሀገር ሀብት ክፍፍል በማረጋገጥ እውን ማድረግ ይቻላል፤ የምንሰራው ከህዝብ ጋር ነውና፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከሌሎች ሀገሮች የሚገኝ ትብብርም ይሁን እርዳታ ተጠያቂነት በተሞላበት መልኩ በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ ምክንያቱም ከአበዳሪም ይሁን ከለጋሽ ሀገራት የሚመጣው ገንዘብ በህዝብ ስም ነውና በአግባቡ ተጠቅመን ከዕርዳታ ተቀባይነት ነፃ በመውጣት የዜጐቻችን ዕድገት በማረጋገጥ ያሰብነውን ማሳካት እንችላለን፡፡ ሌላው የድርጅት አቅምን በዕውቀትና በመልካም ስነ ምግባር ማጠንከርና ከሌሎች ተፎካካሪ ኃይሎች ጋራ በመስራት የታሰበውን ማሳካት ይቻላል፡፡

- ህብረተሰቡ በአሁን ወቅት ኑሮው እንዲሻሻል ምን ማድረግ አለበት? ከመንግስትስ ምን ይጠበቃል ይላል?

የማህበራዊ ችግሮቹ መጀመሪያ ተጠቂ ህዝቡ ራሱ ስለሆነ ይህ እንዲሻሻልና የተሻለ ለውጥ እንዲመጣ፣ የዜጐች ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ ህዝቡ ሊጠይቅና መንግስት ላይም ግፊት ማድረግ መቻል ይኖርበታል፡፡ የአንዲት ሀገር ችግሮች ሊፈቱ የሚችሉት በህዝብ የሚደገፍና የተመረጠ መንግስት ሲኖር ነው፡፡ ስለዚህ ኢህአዴግ የህዝብን ብሶትና የልብ ትርታ እና ጥያቄዎች እንዲያዳምጥ ግፊት ማድረግ ይኖርበታል፡፡ መንግስትም በተራው የህዝብን ብሶት ማዳመጥ ይኖርበታል፤ የግድ ሁልጊዜ በሥልጣን እቆያለሁ በማለት እኔ ያልኩት ብቻ ይሁን ከማለት መቆጠብ ይኖርበታል፡፡ ለተፈጠሩት ማህበራዊ ችግሮች ተጠያቂው ራሱ ኢህአዴግ በመሆኑ፤ ከዚህ ችግር ለመውጣትና ነገም ከታሪክ ተጠያቂነት ለመዳን የህዝቡን ብሶት ማዳመጥና ከሁሉም ተፎካካሪ ፓርቲዎች እና ከህዝብ ጋር በግልፅ መነጋገር ይኖርበታል፡፡

- አሁን ከህብረተሰቡ ጋር ምን እያደረጋችሁ ነው? ወደፊትስ ምን ለማድረግ አስባችኋል?

አሁን ህብረተሰቡን አሳታፊ የሆነ ተጨማሪ ጥናት ለማድረግ አዲሱ አመራር በእንቅስቃሴ ላይ ነው፡፡ የተጠኑ ጥናቶችንም የመቀመርና ወደ ፖሊሲ ሰነዶች በማሸጋገር ወደ ህዝብ በመውረድ ማስተዋወቅ ነው፡፡ በዚህ ላይ ተመስርተን ደግሞ የፖለቲካ ምህዳሩ ከተስተካከለ ወደ ምርጫ በመግባት አሸንፈን ሥልጣን በመያዝ ዕቅዶቹንና ፖሊሲዎቹን ህዝብን በቀጥታ በማሳተፍ በጥናቱ መሠረት ለመተግበር ጥረት እናደርጋለን፡፡

- በመጨረሻ ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ካለ

ዴሞክራሲ በአንድ ሀገር ላይ ሲሰፍን ነው ህዝብ መደማመጥ የሚችለው፡፡ መንግስትም ህዝብን ማዳመጥ አለበት፡፡ ዕድገትና ልማትም መምጣት የሚችለው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሲሰፍን ነው፡፡ ይህም እውን እንዲሆን ህዝቡ ድምፁን ከፍ አድርጐ በመጮህ፣ መብቱ እንዲከበርና እንዲረጋገጥ መንግስትን ሰላማዊ በሆነ መንገድ መጠየቅ አለበት፡፡ አሁን የሚታዩት ሁኔታዎች አስከፊ ቢሆኑም ሰላማዊ ትግል እልህ አስጨራሽ ስለሆነ ውጤቱ ጣፋጭና መልካም በመሆኑ ህዝቡ በቁርጠኝነት ለመብቱ መታገል አለበት እላለሁ፡፡

## መሬት...

ከገፅ 4 የዞረ

ለማፋጠን ነው፡፡” ይለናል፡፡ ልማት በመንግሥት ብቻ ነው እንዴ የሚካሄደው? ለምሳሌ አንድ በአዲስ አበባ 500 ካሬ ሜትር ግቢ ውስጥ መኖሪያ ቤት ያለው ዜጋ ቦታውንና ቤቱን በጊዜው ዋጋ ሸጦ ራቅ ብሎ ሌላ ቦታ ገዝቶ ቤት ከሠራ በኋላ በሚተርፈው ገንዘብ “ቢዝነስ” በማቋቋም ለኢኮኖሚ ልማትና ዕድገት አስተዋፅኦ ማድረግ አይችልም? ያውም፣በራሱ ገንዘብ ላይ ሙስና ማካሄድ ስለማይችል ከሙስና በፀዳ ሁኔታ፡፡ የኢህአዴግ ካድሬአዊ ቢሮክራሲ ግን ከሊዝ ከሚገኘው ገንዘብ ጭምር የሚዘርፈው ሀብት በራሱ ሚዲያ ጭምር እየተጋለጠ ነው፡፡

መቼም በጉዳዩ ብዙ ነገር ማለት እንደሚቻል ይታወቃል፤ግን ለማጠቃለል፣ኢህአዴግ በአሁኑ ጊዜ ማድረግ የሚገባው ለሕጋዊ የቦታ የዞታዎች ሕጋዊ ካርታ መስጠትና ተገቢውን የቦታ ግብር የቤት ግብር እና የቦታ ሽያጭ ታክስ መሰብሰብ ብቻ ነው እላለሁ፡፡

ይሁንና የኢህአዴግ መንግሥት የሰው ምክርና የሕዝብ ብሶት የሚያዳምጥ ጆሮ እንደሌለው ሁላችንም እናውቃለን፡፡ ከአሁን በፊት ላለፉት ሃያ አንድ ዓመታት የኢህአዴግ መንግሥት ፀረ-ሕገ-መንግሥት የሆኑ አያሌ አዋጆች፣ሕጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች አውጥቶ ተግባራዊ ስለአደረገ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሠረታዊ ችግር ዛሬ ደግሞ ኢህአዴግ አንድ ተጨማሪ ፀረ-ሕገ-መንግሥት የሆነ አዲስ የከተማ ቦታ ሊዝ አዋጅ ማውጣቱ አይደለም፡፡ መሠረታዊ ችግራችን ኢህአዴግ እነዚህን ኢ-ሕገ-መንግሥታዊ አዋጆችን የሚያወጣበትን ሥልጣን ያገኘው ከጠብመንጃ አፈሙዝ እንጂ በሕዝብ ይሁንታ ተመርጦ አለመሆኑን በሚገባ አለማወቃችን ነው ወይንም ብናውቅም ሕዝባዊ ትግል ለማካሄድ አለመቻላችን ነው፡፡ አሁንም ቢሆን የተቀናጀና መጠነ ሰፊ ሠላማዊ ትግል ለማካሄድ ካልቻልን በርካታ ኢ-ሕገ-መንግሥታዊ አዋጆች እየወጡ ተግባራዊ እንደሚሆኑና የኢትዮጵያ ሕዝብ እና ሐቀኛ ወኪሎቹ ሥቃይና መከራ እንደሚቀጠል ጥርጥር የለውም፡፡

# በቁርሾና በቂም አንገቱን ለደፋ ህዝብ ስለልማት ማውራት ከፈረሱ ጋሪ እንደ ማስቀደም መሆኑን ኢራፓ አስታወቀ

ብዙአየሁ ወንድሙ

"በመሠረቱ የሰው ልጆችና ልማት ተደጋጋፊዎችና ተመጋጋቢዎች ናቸው፤ ቢባልም ልማት ከውጥን እስከተግባር የሚከናወነው በፍቅር በመተማመንና በመከባበር በታነጸና በተገነባ የቤተሰባዊነት መንፈስ በዳበረ ጤናማና ሠላማዊ ሕብረተሰብ እንጂ በቁርሾና በቂም አንገቱን ለደፋውና ዝምታን ለመረጠው ሕዝብ ልማት ከፈረሱ ጋሪውን እንደማስቀደም ያህል ነው፤" ሲል የኢትዮጵያ ራዕይ ፓርቲ / ኢራፓ/ አስታወቀ፡፡ ኢራፓ ይህንን ያስታወቀው "ሕዝባችን እንዳይናገር እኛ እንነጋገር" በሚል ርዕስ በትላንትናው ዕለት ባወጣው መግለጫ ነው፡፡ መግለጫው ሲዘረዝርም፡- "ስለሆነም በሀገራችን የዜጎቻችን መሠረታዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በትክክል መተግበር፣ የሰብአዊ መብቶችና የግል የህሊና ነፃነት፣ የፕሬስ የመናገርና የመፃፍ፣ የመሰብሰብና የሠላማዊ ሠልፍ ሕገ-መንግስታዊ መብት መረጋገጥ ጉዳይ ከእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር ቢያንስ ጎን ለጎን ማስኬድ በተገባ ነበር በሀገራችን ታሪክ በምርጫ ካርድ ሳይሆን በትጥቅ ትግልና በጠመንጃ የመንግስት ሥልጣን ቅብብሎሽ የተነሳ በየሥርዓቶቹ አራማጆችና ደጋፊዎቻቸው እንዲሁም በአብዛኛው የሕብረተሰብ ክፍሎችና ቡድኖች መካከል በተለያዩ ወቅቶቹና ምክንያቶች የተፀነሰው የፍትህ እጦት፣ ፖለቲካዊ ቁርሾና ቂም በቀል "ሳል ይዞ ስርቆት ቂም ይዞ ፀሎት" እንዳይሆንብን በሀገር አቀፍ ደረጃ ለወሳኙ "ብሔራዊ መግባባት ቅድመ ሁኔታዎችን የሚያመቻቹ የመወያያና የመነጋገሪያ መድረኮች መከፈት እንዳለባቸው ይህም ለአብሮነታችንና ለአስተማማኝ ሰላማችን ለእድገታችንና ለብሔራዊ አንድነታችን፣ ለጥንካሬአችንና ለክብራችን ብቸኛ መንገድ ተብሎ በብዙዎቻችን ዘንድ የታመነበት በመሆኑ" ይላል በመቀጠልም የፓርቲውን አቋም ሲዘረዝር ኢህአዴግን ጨምሮ በተቃዋሚ (ተፎካካሪ) የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ቅንነትንና ግልፅነትን የተላበሰ ከፀበኛነትና ባላንጣነት መንፈስ የፀዳ የመልካም ግንኙነትም ምዕራፍ እንዲከፈት፣ ከዚህ ቀደም ግንቦት 17 ቀን 2002 ዓ.ም ጠ/ሚንስትር መለስ ዜናዊ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችንም በም/ቤት ወንበር ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም በሁሉም ወሳኝ በሀገር ጉዳዮች ላይ ለማማከር፣ ለማሳተፍና ቃል በመግባት የገለፁበት ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ የኢትዮጵያ ሕዝብ የጭፍን ጥላቻ ፖለቲካ ማራመድ እንደማይፈልግ ቂም በቀልና ቁርሾን ማየት እንደሌለበት የሠጡት መሪ ቃል ሕይወት አግኝቶና ነፍስ ዘርቶ ሥራ ላይ እንዲውል እንዲደረግ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ አገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ዜጎቻችን በሙሉ በፖለቲካ መስመሮቻቸው በኃይማኖታቸውና በእምነቶቻቸው በዘር፣ በጎሳና በክልላዊነት፣ በጾታና በቋንቋ ... ወዘተ መከፋፈልን አጥብበው ለብሄራዊ ጥቅማችንና ለኢትዮጵያዊነታችን ልዕልና ሲባል ሠላማዊ፣ ነገር ግን ወሳኝ የተባበረ ጫና በመንግስትና በፖለቲካ ፓርቲዎች ላይ እንዲያሳርፉ፡፡ ማንኛውም ሠላም ወዳድ ዴሞክራትና ቅን አሳቢ ዜጋ፣ ታዋቂ ግለሰቦች የኃይማኖት አባቶች (መሪዎች)፣ የሀገሪቱ ምሁራን፣ የግል ባለሀብቶችና የንግድ ተቋማት፣ የመንግስትና የግል ድርጅቶች ሠራተኞች፣ መምህራንና ተማሪዎች የግልና የመንግስት የሚዲያ ተቋማት፣ የሙያና የሲቪክ ማህበራት፣ አርሶ አደሩ፣ አርብቶ አደሩና . . . ወዘተ ሁሉም ያለልዩነት ለብሔራዊ መግባባት መሳካት ሁለንተናዊ የዜግነት ግዴታቸውን እንዲወጡ፣ ሌሎች ተራማጅና ዲሞክራት የውጭ ሀገር መንግስታት፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ የግጭት አስወጋጅ ድርጅቶ እና ሌሎችም የሚሰጡን የትብብር መስኮች ቢኖሩ ሕጋዊ መስመሮች ተዘርግተው ልምዳቸውን የሚያካፍሉን ሁኔታዎች እንዲመቻቹ፣ ብሎአል

በመጨረሻም የፓርቲው መግለጫ ሲደመድም ጥሪያችንን ስናጠቃልልም በአንድ ሀገር ህዝብ እንደ ህዝብ በብልሹ የአስተዳደር ሥርዓቱ ላይ የሚያቀርባቸው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሞራላዊ የፍትህና የዴሞክራሲ፣ የመብትና የነፃነት ጥያቄዎችና የሚወስዳቸው እርምጃዎች ሁል ጊዜ ሰላማዊ ይሆናሉ ወይንም እንዲሆኑ ይገደዳሉ በማለት ኃይልን መጠቀም ወይም በኃይልና በጡንቻ መመካትና መተማመን አርቆ አስተዋነትና ጤናማ መፍትሄ ነን ለማለት አያስደፍርም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ በወርቃማ ምሳሌነቱ ሲጠቀስና ሲሞገስ የሚኖርበትን ሁኔታ መፍጠር ይቻል ዘንድ የቤታችንና የጓዳችንን ሁሉ አቀፍ ችግሮች ራሳችን በራሳችን በጠረጴዛ ዙሪያ በግልፅነትና በቅንነት በመነጋገር፣ በመወያየትና ብሔራዊ መግባባትን በማዳበር ብሎም በፈርሃ እግዚአብሔርና በሠለጠነ ኢትዮጵያዊ ጨዋነት የመደማመጥ መርሆቻችን ላይ ተመስርተን መሠረታዊ ችግሮቻችንን በሰላማዊ የጋራ መድረክ በውይይት የምንፈታበትን ጊዜ የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲያፋጥነው የኢትዮጵያ ራዕይ ፓርቲ (ኢራፓ) በሁሉም ዘንድ የተከበረውንና የሚናፈቀውን ይህን የእንነጋገር ጥሪውን ለ5ኛ ጊዜ አጠናክሮ ያቀርባል፤ በጎና ወቅታዊ ምላሽ በመስጠት ከሚተባበሩ ወገኖች ጋር አብረን ለተግባራዊነቱ ለመንቀሳቀስ የኢራፓን ዝግጁነት ከወዲሁ ለማረጋገጥ እንወዳለን፡፡" ብሎአል፡፡

# የኢህአዴግ እድሜ . . .

ከገፅ 14 የዞረ

በየአመቱ ከግብር ከፋዩ የገቢ እድገት ጋር አብሮ ማደግ ሲገባው በአንድ ጊዜ ከመቶ ወደ ሺህ ብሮች መሻገር አገርን የሚጐዳ አካሄድ ነው፡፡

የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ አመለካከት ለምን ግብር እንከፍላለን የሚል አይደለም፡፡ ተገቢነቱ አያጠያይቅም፡፡ የመንግሥትም አንዱ ሥራ ግብርን በወቅቱ በመሰብሰብ አገርን ማስተዳደር ነው፡፡ ከአቶ መለስ ጀምሮ የወር ደመወዝተኛው እንኳን ከሚሰበሰበው ግብር ነው የሥራው ዋጋ የሚከፈለው፡፡ ጩኸቱ ግን የሕዝብን አቅምና የገቢ መጠን ያገናዘብ አይደለም ነው፡፡ ዛሬ በችሎታ የምናየው የግብር ከፋዩ ምሬት ብዙ ጣጣ ያስከትላል፡፡ ከሌሎች ብሶቶች ጋር ተዳምሮ ሕዝብን ያስቆጣል፡፡

ዕድሜ ማሳጠሪያ ስድስት

የመሬት ቅርምትና የሊዝ አዋጅ

የመሬት ቅርምትና አዲሱ የመሬት ሊዝ አዋጅ ይኼኛው ከሁሉም ይከፋል "አይጥ ሞቷን ስትሻ ስታበዛ ሩጫ ሄዳ ታሽታለች የድመት አፍንጫ" እንዲሉ ነው፡፡ ኢህአዴግ የገጠሩን ሕዝብ ከእርሻ መሬቱ እያፈናቀለ ከውጭ ባለ ሀብቶች በሊዝ መሸጥን ከጀመረ ውሎ ቢያድርም አሁን ግን የሚታየው በብርቱ የከፋ ሆኗል፡፡ በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ወረዳዎች ለአበባ ምርትና ለተለያዩ ተግባራት በሊዝ የቸረቸረው ኢህአዴግ አድማሱን አስፍቶ ጋምቤላ ደርሷል፡፡ እንደ ሂዩማን ራይትስዎች ጥናት ጋምቤላ ውስጥ ሀቦቦ በሚባል አካባቢ እስከ 5.6 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ከአርሶ አደሮች ነጥቆ ለባለሀብት ሸጧል፡፡ ይህ ድርጊት በፍጥነት እየጨመረ የመጣውን የሕዝብ ቁጥር መጨመር ያላገናዘበና ዛሬ የሚገኘውን ገንዘብ ብቻ ከግምት ያስገባ ነው፡፡

የፓርላማ ህግና ደንብ ተጥሶ በ "ሱሪ ባንገት" የአቶ መለስ መመሪያ እንዲፀድቅ የተደረገው የመሬት ሊዝ አዋጅ ብርቱ አደጋ አለው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ከመሬት ጋር ያለውን ታሪካዊ ቁርኝት የማይረዳ ባለስልጣን ያለ አይመስለኝም፡፡ ቤት ያለ መሬት አይታሰብም፤ ሁለቱም የማይነጣጠሉ ናቸው፡፡ ድህው ኢትዮጵያዊ ችግሩ ጠንቶ ግራ ካጋባው ከይዞታው ቆረሶ መሸጥ ባህሉ ነው፡፡ በዚህ አዋጅ የከተማውን ነዋሪ መገዳደር ኢህአዴግ የጉዞ አቅጣጫው ግራ የሚያጋባ ሆኗል፡፡ ለወትሮው በምርጫ ዋዜማ የአዲስ አበባን ነዋሪ ባንቀልባ ማዘል የሚቃጣው ኢህአዴግ ከፊት ለፊቱ የ2005 ዓ.ም ምርጫ እያለበት ይህንን አዋጅ ሊተገብር መጣደፉ ምናልባትም ጠብመንጃውን ተማምኖ ይሆናል፡፡

በአዋጁ ዙሪያ የአዲስ አበባን ህዝብ ለማሳመን የተደረገው ጥረት በእጅጉ አልተሳካም፡፡ ነዋሪው ተቃውሞውን የገለፀው በከፍተኛ ጩኸትና ምሬት ነው፡፡ በአንዳንድ ሥፍራዎችማ ህዝቡ አዳራሹን ጥሎ በመውጣት ነበር ኢህአዴግን የሞገተው ብዙ ምሁራንም ሆኑ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች አዋጁ እንደገና ለፓርላማ ቀርቦ እንዲጠና እየወተወቱ ናቸው፡፡ ግን ማን ይሰማቸዋል? ብዙዎች እንደሚስማሙበት ኢህአዴግ ምላስ እንጂ ጆሮ የለውም፡፡

እንደ መከደኛ

የከፈትኩትን የንባብ ማዕድ ልክደነው፡፡ ለረጅም አመታት ስልጣን ላይ የሚቆዩ መሪዎች በቀናትና በወራት ውስጥ ዕድሜያቸው ሲያጥር ከሰሜን አፍሪካ አገራት ተምረናል፤ ኢህአዴግ ስለመማሩ ማወቅ ባይቻልም፡፡ የጥቂቶች በዙሪያቸው ተኮልኩለው ማሸቃበጥ በህዝቡ ዘንድ ተወዳጅ መሪ እንደሆኑ አድርገው የተዘናጉት ኮሎኔል ጋዳፊ እንደ ልባቸው የፋነኑባትን ዓለም በውርደት ሞት ተሰናበቷት፡፡ ኢህአዴግም በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ ተቀባይነት እንደሌለው ካወቀ (ከተገነዘበ) ውሎ አድሯል፡፡ ዕድሜውን ለማራዘም በተለያዩ ጊዜያት የጣፋቸው ድሪቶዎች ጊዜያዊ ማዘናጊያና አቅጣጫ ማስቀየሻዎች ከመሆን ባለፈ የፈየዱለት ነገር የለም፡፡ ራሱን በቀጣይ ስልጣን ላይ ለማቆየት ሲል የሚያወጣቸው ሕጎችና መመሪያዎች የዜጎችን ህልውና በብርቱ ከመፈታተን አልፈው ምሬቱን በአደባባይ ለመግለፅ ወደሚገደድባት ደረጃ ሊያሸጋግረው ይችላልና ቆም ብሎ ያስብ፤ "አስተውሎ የሚራመድ ረጅም መንገድ ይጓዛል" እንዲሉ፡፡

# ኢፍዴኃግ ለኢህአዴግ ጥብቅና ቆሟል ሲል መኦሕዴፓ ገለፀ

ብዙአየሁ ወንድሙ

"የመላው ኦሮሞ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ / መኦህዴፓ/ በኢህአዴግ ላይ ያነጣጠረ መግለጫ አውጥቶ የኢትዮጵያ ፍትህ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ግንባር / ኢፍዴኃግ/ ለኢህአዴግ ጥብቅና መቆም የገዢው ፓርቲ ቀኝ ክንፍ እና ቀኝ እጅ መሆናቸውን ያበስራል" ሲል አስታወቀ፡፡ መኦህዴፓ ይህንን ያስታወቀው በትላንትናው ዕለት "ሳንነካቸው የሚነኩን ፓርቲዎች ከአድራጐታቸው እንዲቆጠቡ አጥብቀን እናስገነዝባለን" በሚል ርዕስ ባወጡት መግለጫ ነው፡፡

ፓርቲው ለዝግጅት ክፍላችን በላከልን በዚሁ መግለጫ እንደሚገልፀው "በአገሪቱ ውስጥ ከ60 በላይ ፓርቲዎች አሉ፡፡ ኢህአዴግ የሚፈልጋቸውን ስድስት የፖለቲካ ፓርቲዎች መርጦ አንድ ሚሊዮን ብር ለሥራ ማስኬጃ መድቦላቸው የፓርቲዎች ም/ቤት ብሎ አደራጅቷቸዋል፡፡ ቀሪዎች ፓርቲዎች የፋይናንስ ድጋፍ ተከልክለው ከፖለቲካ ተሳትፎአቸውም ተገልለው ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ፓርቲዎች በራሳቸው ገቢ የቆሙለትን ዓላማና የፓርቲያቸውን ፕሮግራም በማከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡ ኢፍዴኃግ ከገዢው ፓርቲ ፋይናንስ ከማይመደብላቸው የተቃዋሚ ፓርቲዎች ጐራ መመደብ አይችልም፡፡" ብሎአል፡፡ መግለጫው በመቀጠልም "ከምርጫ 2002 በኋላ ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ምንም በፓርላማ መቀመጫ ባይኖራቸውም አብረን እንሠራለን፡፡ ብለው ነበር፡፡ በዚሁ መሠረት ለመጀመሪያ ጊዜ የተወሰኑ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በማግለል በርካታ ፓርቲዎችን ሰብስቦ ጠርተው ነበር፡፡ ፓርቲያችንም በስብሰባው ላይ ከተገኘ በኋላ በነበረው እምነት ሁሉም ተቃዋሚ ፓርቲ መድረክንም ጨምሮ መጠራት እንዳለበት ሐሳብ አቅርበን ነበር፡፡ መድረክ በፓርቲዎች ስብሰባ ላይ መካተቱ ለአገርና ለህዝብ ይጠቅማል ብለን በማመናችን ነው፡፡ ገዢው ፓርቲ ተቃዋሚዎችን እየመረጠ ማግለልና ከመከፋፈል ድርጊት እንዲታቀብ ማሳሰቢያ ሰጥተን ነበር፡፡ በወቅቱ ሐሳባችንን የተቃወመን ኢህአዴግ ሳይሆን እነዚህ በአሁኑ ወቅት በፓርቲዎች ም/ቤት የታቀፉት ስድስቱ ፓርቲዎች ነበሩ፡፡ እኛም በወቅቱ ለኢህአዴግ ጥብቅና መቆማቸው በመገረም አልፈናዋል" ሲል ያብራራል፡፡ በማያያዝም የመኦህዴፓ መግለጫ እንደሚለው "ገዢው ፓርቲ የኢህአዴግ የገባውን ቃል በማጠፍ አብዛኛው ፓርቲዎችን መኦህዴፓን ጨምሮ በማግለል ይመቹኛል ያላቸውን ስድስት ፓርቲዎች መርጦ የፓርቲዎች ም/ቤት አቋቋምኩ ብሎአል፡፡ ፓርቲያችን ድርጊቱን በማውገዝ መግለጫ ማውጣቱ ይታወቃል፡፡ መግለጫ የወጣበት ኢህአዴግ እያለ ኢፍዴኃግ ኢህአዴግን ለምን ትነኩብናላችሁ በማለት በፓርቲያችን ላይ መግለጫ ማውጣቱ ማንነቱን በግልጽ ያሳወቀበት ነው፡፡ ዛሬም ለኢህአዴግና ለኢፍዴኃግ ደግመን ደጋግመን ማሳወቅ የምንፈልገው በአገራችን ዴሞክራሲ እንዲያብብ ሰብአዊ መብት እንዲከበር ህዝብ የሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን ኢህአዴግ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር መድረክንም ጨምሮ መወያየትና መከራከርና በጋራ መሥራት አለበት ብለን እናምናለን፡፡ በአገራችን ጉዳይ ማንም ህጋዊና በሠላማዊ መንገድ የሚታገል ፓርቲ መገለል የለበትም የሚል ጽኑ እምነት አለን" በማለት ባለ ሦስት ገጽ ላይ አምስት የፓርቲው ሥራ አስፈጻሚዎች ፈርመው ከላኩልን መግለጫ መረዳት ተችሎአል፡፡

## ከአፍሪካ ሕንፃ ፊት ለፊት የቀ.ኃ.ሥላሴ ሐውልት እንኳንም አልቆመ!!

ሰሞኑን የአፍሪካ ህብረት 18ኛ መደበኛ ስብሰባ መከናወኑ ይታወቃል። በዚሁ ስብሰባ የመክፈቻ ሥነ-ሥርዓት ዕለት በቻይና መንግሥት ድጋፍ ወይንም ቀጥታ ርዳት በአፍሪካ ድንቅ የተባለለት አዳራሽ ተሠርቶ ተመርቋል። "ዴሞክራቱ መንግሥታችን" መሬቱን ከሊዝ ነፃ በሆነ መልኩ በመስጠቱ ተመስግኗል። ሲያንሰው ነው። ይኸው ድንቅ አዳራሽና ጽ/ቤት ሲመረቅ የአፍሪካ አድነት ድርጅት (አአድ) ሲመሠረት ከመሥራች መሪዎች መሀከል አንዱ የነበሩት የጋናው መሪ ኩዋሚ ኑኩሩማ ሐውልት ተመርቋል። ከምርቃቱ በኋላ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሐውልት አለመሠራቱ የብዙዎች መናጋገሪያ ሆኗል፡፡ አብዛኞቹ በመቆጨት "በቁጥር አንድ መሠራት የነበረበት የሳቸው ነበር" ሲሉ ተደምጠዋል። እኔ ግን እንኳንም አልተሠራ አልኩኝ።

በመሠረቱ መንግሥታችን "ዴሞክራት በመሆኑ እንጂ ቀ.ኃ.ሥላሴ እንኳንስ አፍሪካ አህጉርን ወክለው ሐውልት ሊቆምላቸው ይቅርና ገና በታሪክ የሚጠየቁባቸው በርካታ ጥፋቶች አሉባቸው። ጥቂቶቹ፡-

የመጀመሪያውና ዋናው ጥፋታቸው ከሀገራቸው አልፈው ፀረ-ቅኝ አገዛዝን ከሚቃወሙ ታጋዮች ጎን በመሠለፍ፣ ማንም ሳይፈቅድላቸው ኢትዮጵያ የሌግኦፍኔሽን መስራች እንድትሆን ማድረጋቸው፣ ጣሊያን ኢትዮጵያን ስትወር ጄኔቭ ድረስ ሄደው ሉዓላዊቷ ኢትዮጵያ በጣሊያን መወረሯን ማጋለጣቸውና የመንግስታቱ ድርጅት ለነፃይቱ ኢትዮጵያ ድጋፍ እንዲሰጣቸው በመጠየቃቸው መጠለያም በመሆን የአፍሪካ ሀገራትን ከቅኝ ገዥዎች በማላቀቅና ራሳቸውን የአፍሪካውያን የነፃነት አባት በማድረግ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በኢትዮጵያ (በአ.አ) እንዲመሠረት በማድረጋቸው በዛሬው ትውልድ ተጠያቂ ናቸው። እሳቸው አአድን አዲስ አበባ እንዲመሠረት ባይፈቅዱ ኖሮ ዛሬ በአፍሪካ የመጀመሪያ ህንፃ የተባለበትን አዳራሽ ማየት አንችልም ነበር። ዳሩ ግን መንግሥታችን "ልማታዊ መንግሥት" በመሆኑ በትራንስፎርሜሽኑ እቅድ መሠረት "ከርቸሌ" የነበረውን ወደ ዘመናዊ ህንፃነት በመቀየሩ በዚህ እንፅናናለን። እንድቀንም የቃሊቲን መጎሪያ ወደ አቃቂ ፈቀቅ አድርጎ ቃልቲ ላይ ደግሞ የተባበሩት መንግሥታትን ጽ/ቤት ይገናባልን ይሆናል።

ጥፋት ሁለት፤ ኤርትራን በዴፕሎማሲያዊ ሁኔታ አንድ ጥይት ሳያጮሁ በሰላማዊ መንገድ ወደ እናት አገሯ መቀላቀላቸው።

ጥፋት ሦስት፤ የዐሰብን የባሕር በር በቁጥጥራቸው ሥር በማድረግ ሽቀጣ ሽቀጦች ወደ ውጭ እንዳይወጡና እንዳይገቡ የቀይ ባሕርን የመተላለፊያ መሥመር በመዝጋታቸው።

ጥፋት አራት የመተማን የአሶሳንና የጋምቤላ አዋሳኞችን የሱዳን ግመሎች ሸገር ብለው እንዳይገጡ የብረት አጥር በመሆናቸው።

ጥፋት አምስት የብሔር ብሔረሰቦችን መብት በመጨፍለቅ አንዲት ኢትዮጵያ ብለው ነክሰው በመያዛቸው።

ጥፋት ስድስት ጂቡቲን ወደ ኢትዮጵያ እንደ ኤርትራ ሳይቀላቅሉ በደርግ ተቀልምመው በመገደላቸው። እንግዲህ እነዚህንና መሰል ጥፋቶችን ተሸክመው መቃብር የወረዱ ንጉሥ በምን ውለታ ነው አፍሪካ ሕብረት ሕንፃ ፊት ለፊት ሐውልት የሚቆምላቸው? የእርሳቸው ይህን ያህል ጥፋት የተሸከሙት ንጉሥ ሐውልት ይቁምላቸው ቢባል እንኳን ይች ሀገር አይጣልባትና "መተኪያ የሌላቸው" መሪያችን ክቡር ጠ/ሚንስትር አንድ ነገር ቢሆኑ ምን አይነት ሐውልት ሊሠራላቸው ነው? ከርቸሌ የነበረውን መሬት አስረክበው መቸስ መና ይቅሩ ማለት ሕሊና ማጣት ነው። እንዲያውም ሰው ጠፍቶ እንጂ እንደ ብፁዕ አባታችን ቦሌ መዳሕኒ ዓለም በህይወት እንዳሉ እንደቆመላቸው ሁሉ የሳቸውም ከኩዋሚ ኑኩሩማ ጎን ሊቆምላቸው በተገባ ነበር። ዋናው ነገር ካልተረገምን በስተቀር የቀ.ኃ.ሥ ሐውልት ሊቆም አይገባውም። ይልቅ እኛ የምንጠይቀው ይኸ ተገኘ የተባለው አፅም የሳቸው ከሆነ እንደ ሉሲ አፅም ተለቅሞ ወደ አሜሪካን ተልኮ ይቺ አገር በቀልተኞችን እንድታፈራ ተመርቃም እንደሆነ እንዲመረመርልን እንጠይቃለን።

# የከተማ ቦታ የሊዝ "መነሻ ዋጋ ስንት ነው?"

ከወርቁ በለጠ ይመር

በነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ውስጥ የተለያዩ ገቢዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ ገበያዎች ውስጥ የመሬት የምርት ገበያ፣የሥራ፣የፋይናንስ እና የቤት ገበያ የመሳሰሉት የገኙባቸዋል፡፡ በአያንዳንዱ ነፃ ገበያ ውስጥ የአቅራቢው ብዛትና የተረካቢው ብዛት እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ የአቅራቢው ቁጥር በመብዛቱ የገበያ ዋጋ ይወርዳል፡፡ የአቅራቢው ቁጥር አንድ ብቻ ከሆነ ነፃ ገበያ መሆኑ ይቅርና መኖፖል ይሆናል፡፡ በሞኖፖል የሚቀርብ መሬት ወይም ምርት ገበያ ዋጋው በጣም ይንርና ገዥውን ለከፋ ብዝበዛ ይዳርገዋል፡፡ ገዥው በጥራት ጉድለትም ሊጐዳ ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ ጉዳቱን የሚከላከልለት የሞኖፖሉን ኃይል የሚሰብርለት የተወካዮች ምክር ቤት ያስፈልገዋል፡፡ ግን ሞኖፖሉ የመንግሥት፣የተወካዮች ምክር ቤትም የገዢው ፓርቲ በሆነበት አገር ሸማቹ ወይም ገዥው አለኝታ የሚሆነው ተገን ያጣል፡፡

በአንፃሩ የአቅራቢው ቁጥር በዝቶ ገዥው አንድ ብቻ ከሆነ ደግሞ የሸቀጡ ወይም የቤቱ ዋጋ በጣም አነስተኛ ይሆናል፡፡ በዚህ ጊዜ አቅራቢውን የሚታደግ ኃይል ያስፈልጋል፡፡ በኢትዮጵያ መሬትን በተመለከተ መንግሥት ሞኖፖል ነው፡፡ ቤቶችን በተመለከተ ደግሞ በርካሽ ዋጋ ይገምትና ለባለቤቱ ትንሽ ገንዘብ ይሰጠዋል፡፡ ከላይ የጠቀስኳቸውን የገበያ ዓይነቶች በልባችን ይዘን አዲስ የወጣውን የከተማ ቦታ ሊዝ አዋጅ እንድምታ ቀጥዬ ባጭሩ ላሳይ፡፡ ስለዚሁ አዋጅ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አቶ ኩማ ደመቅሣና የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስትር ክቡር አቶ መኩሪያ ኃይሌ ከረዳቶቻቸው ጋር በመሆን ታኅሣሥ 30 ቀን 2004 ዓ.ም በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡ ታዳሚዎችም ጥያቄና አስተያየት አቅርበዋል፡፡ ታዳሚዎቹን በሦስት መደብ ከፍዬ አይቻቸዋለሁ፡፡ አንደኛው፣ከንቲባው፣ሚኒስትሩና ረዳቶቻቸው ያቀረቡትን መግለጫ በጭፍን የሚደግፉ፣የጉዳዩን ጭብጥ ያልተገነዘቡ ካድሬዎች ቡድን ነው፡፡ ሁለተኛው፣ መግለጫውን ተረድተው፣አዋጁን አንብበው ጠቃሚ ጥያቄዎችንና አስተያየቶችን ያቀረቡ ዜጐች የተገኙበት ቡድን ነው፡፡ ሦስተኛውና አብዛኛው ታዳሚ ግን ጉዳዩ የገባውም ያልገባውም ወይም ዝምታን የመረጠ ምድብ ነው፡፡

በመጀመሪያ ማንሳት የምፈልገው ስለአዋጁ ገለፃ ያበረጉትም ሆኑ፣ጥያቄና አስተያየት ያቀረቡት በአንድ ጉዳይ ላይ የተስማሙ መሆናቸውን ነው፡፡ ይኸውም ነባር ይዞታ ያላቸው ዜጐች የሚከፍሉት የሊዝ ዋጋ "የመነሻ ዋጋ" ነውና "አነስተኛ" ነው በሚለው የተስማሙ ይመስላል፡፡ ዝምተኛው ምድብ ምን እንዳሰበ ግን አይታወቅም፡፡

በመሬት ገበያ የኢህአዴግ መንግሥት በሞኖፖል ስለያዘ የመሬት ሊዝ ዋጋን ያለተወዳዳሪ በመተመኑ "የመነሻ ዋጋው" ከፍተኛ ሆኗል፡፡ ለምሣሌ ብር 500 የሚያወጣውን አንድ ካሬ ሜትር ቦታ የመነሻ ዋጋው ብ 4,500 ነው ቢል ሌላ መሬት አቅራቢ ስለሌለ መቀበል ብቻ ነው፡፡ በቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ዘመነ መንግሥት መሬት አቅራቢዎች ወይም ሻጮች ወይም ወለድአገድ ወይም መሬት የሚያከራዩ ሰዎች ቁጥራቸው ብዙ ስለነበር፣በውድድሩ ምክንያት የመሬት ዋጋ ዝቅተኛ ነበር የደርግ መንግሥት ለመሬት ዋጋ አላወጣም ነበርና መሬት ነፃ ነበር፡፡ ለማለት ይቻላል፡፡ ይህ ግን በነፃ ገበያ ሥርዓት ትክክል ባይሆንም በሶሻሊስት ሥርዓት ማዕቀፍ ውስጥ ይታይ፡፡ የኢህአዴግ መንግሥት የመሬት ሊዝ ዋጋ በነፃ ገበያ ነው ወይስ በሶሻሊስት ሥርዓት የሚተመነው?

የቤት ገበያን ያየን እንደሆነ፣የኢህአዴግ መንግሥት ብቸኛ (ያለተወዳዳሪ) የዋጋ ተማኝ መሆን ይችላል፡፡ በተለይ በመሐል ከተማ ከፍተኛ የገበያ ዋጋ ያለው ቦታ ላይ የሚገኙ ቤቶቹን ከባለንብረቶቹ ይወስዳል፡፡ ቤቶቹን አፍርሶ ይህን ከፍተኛ ዋጋ ያለውን ቦታ ከባንክ ለሚበደሩ 'ኢንቬስተር' ተብዬዎች ባለብዙ ፎቅ ሕንጻ እንዲሠሩ በከፍተኛ የሊዝ ዋጋ ያዛውርላቸዋል፡፡ የግለሰቦችን ቤት በርካሽ ተምኖ ሲረከብ መንግሥት ሞኖፖሶኒ ነው፡፡ ቤቶቹ ያረፉበትን ቦታ በሊዝ ሲያስተላልፍም ሞኖፖሊ (monopoly) ይሆናል፡፡ ይህ በኢኮኖሚ ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ አዲስ ሬኮርድ ሳይሆን አይቀርም፡፡ አያድርስ ነው!

ወደ "መነሻ ዋጋ" እንመለስና ሁለት የዋጋ ተመን ፅንሰ-ሀሳቦችን እንመልከት፡፡ አንድ መሬት ወይም ሸቀጥ ትክክለኛ ዋጋ (Value) እና የገበያ ዋጋ (market price) አለው፡፡ ዋጋው ሸቀጡን ለማምረት ወይም መሬቱን ለማልማት የፈሰሰውን የሰው ጉልበትና እውቀት፣በእውቀት ውስጥም የምርምር ሥርፀት፣ለቴክኖሎጂ ግኝት የዋለውን ሀብት ሁሉ በማስላት ሊታወቅ ይችላል፡፡ የገበያ ዋጋ (market price) ደግሞ በአቅርቦትና ፍላጐት ሚዛን የሚወስን ይሆናል፡፡ እንደሚዛኑ ሁኔታ የገበያው ዋጋ ከትክክለኛው ዋጋ በላይ ወይም እኩል ወይም ሊያንስ ይችላል፡፡ ታዲያ መንግሥት የከተማ ቦታን የሊዝ "መነሻ ዋጋ" ሲተምን የትኛውን ሥሌት መሠረት አድርጐ ነው? ትክክለኛ ዋጋን ወይስ የገበያ ዋጋን? የገበያ ዋጋ እንዳይባል በመሬት ገበያ ውስጥ በሞኖፖልም ሆነ በሞኖፖሶኒ ኃይሉ ዋና ተዋናይ መንግሥት ነው፡፡ ስለዚህ ጥያቄው የከተማ ቦታ ትክክለኛ ዋጋ (value) እንዴት ታወቀ? የመሬት ሊዝ ወጋስ እንዴት ተተመነ? የሚለው ይሆናል፡፡ በሊዙ ዋጋና በትክክለኛው ዋጋ መካከል ያለው ልዩነት ስንት ነው? በአሁኑ ጊዜ እነዚህን ጥያቄዎች የኮንዶሚኒየምና የግል ይዞታ ቤቶች ካረፉባቸው ቦታዎች የሊዝ ዋጋዎች ጋር አያይዞ ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡

ኮንዶሚኒየም ያረፈበት ቦታ፣በግቢው ውስጥ የሚገኘው ክፍት ቦታ፣የመዝናኛ ሥፍራው፣ቤቱ ያረፈበት ወለል፣በየፎቁ ያለው ወለል፣ወ.ዘ.ተ የሊዝ ዋጋው ስንት ነው? ከኮንዶሚኒየሙ ይዞታ አጠገብ በሚገኝ የግል ይዞታ ላይ 4 ደሳሳ ጐጆ ያረፈበት ቦታ የሊዝ ዋጋ ስንት ነው? የሁለቱ ቦታዎች የሊዝ ዋጋ ሲወዳደር፣የኮንዶሚኒየሙ ቦታ ከፍተኛ ልማት ስለተካሄደበት የሊዝ ዋጋው መብለጥ አለበት፡፡ የደሳሳ ጐጆው ወለልና ቦታ ብዙም ልማት ስላልተካሄደበት የሊዝ ዋጋው አነስተኛ ሊሆን ይገባል፡፡ ነገር ግን ደሳሳ ጐጆው ያረፈበትን ቦታ የሊዝ "መነሻ ዋጋ" አንሮ ባለግል ይዞታውን መክፈል ካልቻልክ ልቀቅ የሚባል ከሆነ ኢ-ፍትሐዊ ነው፡፡ ይህ የናረ የሊዝ ዋጋ "መነሻ ዋጋ" በሚል አነስተኛ አስመስሎ መከራከር ጭብጥ የሌለው ክርክር ነው፡፡ በመንግሥት ሞኖፖል ኃይል የሚወሰን የ "መነሻ ዋጋ" የብዝበዛ ዋጋ መሆኑን እያወቅን ልንክድ አይገባም፡፡

ሌላው ጉዳይ፣በከንቲባውም ሆነ ሚኒስትሩ ባደረጉት ገለፃ እንዲሁም በባለብዥታ ካድሬዎች ትኩረት ያላገኘው ጉዳይ የኢትዮጵያ ከተሞች ያለገደብ መስፋፋትና ገጠሩንና የእርሻ መሬቱን ወደ ከተሞች ድንበር የማስገባት ጉዳይ ነው፡፡ ለምሣሌ ያህል፣ተፈራ ዋልዋ ከንቲባ በነበሩበትና በአሁኑ የኩማ ደመቅሣ ጊዜ የከተማዋ ድንበርና ስፋት ምን ያህል እንደጨመረ መልስ ሊሰጥበት፣ማብራሪያም ሊታከልበት ይገባል፡፡ በመቶዎች በሚቆጠሩ ያገሪቱ ከተሞች ዙሪያ ያሉትን የገጠር ቦታዎች በከተማ ክልል ውስጥ ማስገባትና ገጠሬዎችን ከተሜዎች ናችሁ ማለት ከጥቅሙ ጉዳቱ ሊያመዝን ይችላል፡፡ ገጠሬዎች ከተሜዎች የሚሆኑት በልማት ሂደት እንጂ በአስተዳደራዊ ውሳኔ የከተማ ቦታን በማስፋፋት የሊዝ ገቢን ለማሳደግ ሲባል አይደለም፡፡ ገጠሬውን ሁሉ ከተሜ ማለቱ የራሱ የሆነ ሥነ-ልቡናዊ መናጋትን ያስከትላል፡፡ ከተሜዎች የሚያገኙትን ልዩ ልዩ ዘመናዊ መሠረተ-ልማቶችን፣ውሃን፣ስልክን፣መብራትን ሁሉ አዲሶቹ "ከተሜዎች" መቼ እንደሚያገኙ በጉጉት መጠበቃቸው አይቀርም፡፡

ቀጥሎ የምናየው የኢንቨስተሮችን ሥጋት ነው፡፡ ከመሬት ጋር በተያያዘ በየጊዜው በሚወጡ አዋጆች፣መመሪያዎችና ደንቦች ኢንቨስተሮች ሊበረግጉ ይችላሉ፡፡ የከተማ ቦታን በሊዝ ተከራይተው ሀብታቸውን ለልማት ያዋሉ ባለሀብቶች ሥራቸውን ለማስፋፋት አቅደው ከሆነ ከመተግበር ይቆጠባሉ፤ይገታሉም፡፡ "ደግሞ ምን መጣ? ፖሊሲ ተለወጠ እንዴ?" የሚሉ ጥያቄዎችን ያነሣሉ፡፡ የዚህ ዓይነት ጥያቄዎች ገና ኢንቨስት ያላደረጉ ባለሀብቶችን ጥርጣሬ ላይ ይጥላቸዋል፡፡ የፖሊሲው ለውጥ የማያሳስበው በርካሽ ወለድ በባንክ ብድር የሚዋኙት መንግሥት ከላይ የሚሰበስብባቸው ኢንቨስተሮችን ብቻ ነው፡፡ ሥራው ካላዋጣቸው ድርጅታቸውን፣ ሕንፃዎቻቸውን፣ ወ.ዘ.ተ ለአበዳሪው ባንክ አስረክበው ነፃ ይወጣሉ፡፡ በዚህ ሂደት የሚከሥሩት ባንኮች ናቸው፡፡ "በደንባራ በቅሎ ቃጭል - - -" እንደሚባለው፣ሌሎች ኢንቨስተሮች ድርጅታቸውን ለባንክ ለማስረከብ በተጠንቀቅ ላይ ሳየሆኑ አይቀሩም፤የከተማ ቦታ ሊዝ ኪራይም እናታቸው ላይ ይናጥርባቸዋል፡፡

በውይይቱ ወቅት ያልተብራራው ጉዳይ ቤት ያረፈበት የከተማ ቦታ ትርጉም ነው፡፡ ቤት ያረፈበት የከተማ ቦታ የመንግሥት ቤቱ ግን የግል እንደሆነ በውይይቱ መሪዎችና በታዳሚዎች መካከል ስምምነት ያለ ይመስላል፡፡ ዓለም አቀፍ የቤት ትርጉም ውስጥ ጣራና ወለል መካተታቸው የታወቀ ነው፡፡ ስለዚህ አንድ የቤት ባለንብረት ቤቱ ያረፈበትን ቦታ ጭምር በይዞታው ሥር ሊያውል ይገባል፡፡ የቤቱ ወለል የመንግሥት መሬት፣የቤቱ ጣራና ግድግዳ ግን የግለሰቡ እንዴት ሊሆን ይችላል? መቼም ቤት በአየር ላይ አይሠራምና መጪው ትውልድ ይህች አገር "ሰው ያልነበራት ወና ነበረች" እንዳይለን እሰጋለሁ፡፡ እባካችሁ ፖሊሲ፣/አዋጅ፣/መመሪያና ደንብ የምታወጡ ባለሙያዎች መሪዎቻችን፣በልዩ ልዩ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጉዳዮች ስለሚወጠሩ የምታመኑበትን አማክሩአቸው፡፡

ቦታና ቤትን በተመለከተ አንድ የሚያሳዝነኝ ጉዳይ አለ፡፡ በቀዳማዊ አፄ ኃ/ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ከሚያገኙአት ትንሽ ገቢ ራሳቸውንም ልጆቻቸውንም በድለው መሬት ገዝተው ወይም በወለዳአግድ ይዘው ጐጆ ቀልሰው ይኖሩ የነበሩ ታታሪ ዜጐች በደርግም በኢህአዴግም በደል ደርሶባቸዋል፡፡ ትርፍ ጐጆ ሠርተው በማከራየታቸው ደርግ ወረሰባቸው፡፡ የተወረሰውን ቤት ይከራዩ የነበሩ ሰዎች ደግሞ አሁን የተከራይ አከራይ ሆነው ላባቸውን ባላፈሰሱበት ቤት ገቢ ያገኙበታል፡፡ ነገር ግን ደርግ ጐጆአቸውን የወረሰባቸው ዜጐች በገዛ ቤታቸው የበይ ተመልካች ሆነዋል፡፡ስለተበደሉት በደል መናገር እንኳ አይችሉም፡፡ ይህ አንሷቸው በንጉሡ ዘመን ቦታ ገዝተው ጐጆ ቀልሰው የሚኖሩበትን ቤት ያረፈበትን ምድር ግቢና ኢህአዴግ ሊዝ ሊያስከፍላቸው ነው፡፡ በእውነት ይህች አገር ምን ያህል የተረገመች፣ለዜጐቿ ሲኦል የሆነች አገር ናት? ታታሪ ዜጐች ለምን እየተበደሉ ይኖራሉ? ምን አጥፍተዋል? እድሜያቸው በገፋ ቁጥር በአንድ በኩል በዋጋ ንረት በሌላ በኩል በመሬት ሊዝ ክፍያ ሲጨነቁ ኖረው በሀዘንና በቁዘማ፣ሕይወታቸው ማን ይጠቀማል? አገር ወይስ መንግሥት? እትብታቸው የተቀበረበትን ቦታ በድህነታቸው ምክንያት 'ሊዝ' ባለመክፈላቸው ለምን ይነጠቃሉ? የከተማ ቦታ ሊዝ አዋጅ ጥቂቶችን ብቻ ነው የሚጐዳው እየተባለ ለምን በመንደር ካድሬዎች እንዲታለሉ ለምን ይደረጋል?

ቀደም ሲል በጠቀስኩት ስብሰባ ላይ አንድ ታዳሚ ስለ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አንስተው ነበር፡፡ በዚህ ሥርዓት የብዙሃን ድምፅ ያለው የፖለቲካ ፓርቲ ሥልጣንም ቢይዝም ቃሉ የጥቂቶችን መብትም ማክበር እንዳለበት አሳስበው ነበር፡፡ ይህ የፖለቲካ ሥልጣን ለመያዝ ከሆነ ትክክል ነው፡፡ ንብረትን በተመለከተ ግን ጉዳዩ የሚመለከተው ግለሰብ ዜጋን እንጂ የድምፅ ድምር ውጤትን አይደለም፡፡ ራሱ መንግሥትም ቢሆን የግለሰብን ንብረት፣/ድርጅት፣/ ቤት ወ.ዘ.ተ የሚመዘገበው በግለሰቡ ስም ነው፡፡ ይህ ግልፅ ያልሆነላቸው ካድሬዎች የከንቲባውንና የሚኒስትሩን ፊት እያዩ "አዋጁ የሚጐዳቸው ጥቂት ግለሰቦችን ነው፡፡ እንዳውም 40% ቢሆኑ ነው" ይሉ ነበር፡፡ ይህ አባባላቸው ባለፈው ሥርዓትም መሪው መንግሥቱ ኃ/ማርያምን ለማስደሰት ካድሬዎች ምን እንደሚዘላብዱ እንዳስታውስ አደረገኝ፡፡

ካለፈው የምንማር ከሆነ ሀሳብን በሀቅ ለአለቆቻችን ማቅረብ እንጂ እነርሱ ለውይይት ያቀረቡትን ሐሳብ ያለቀለት ጉዳይ አድርጐ ምንም "የሐሳብ እመርታ" ሳያሳዩ የመቅረቱ ባሕል መቅረት አለበት፡፡ ገዥው ፓርቲና መንግሥትም ቢሆኑ ያለቀለትን ጉዳይ፣በአዋጅ የፀደቀን ሕግ ለሕዝብ ውይይት ማቅረባቸው ፋይዳ የለውም፡፡ ምናልባት አዋጁን የማሻሻል ወይም የማስቀረት ድፍረቱ ካለ ስብሰባው ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡ በተገላቢጦሽ የሕዝብን ድጋፍ ለማግኘት ከሆነ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሳያፀድቀው ቀደም ብሎ ቢሆን ኖሮ ሕዝብን ሰብስቦ ማወያየቱ ጠቃሚ ይሆን ነበር፡፡

ባለፈው ሥርዓት ደርግ የተሳሳተ አዋጅ አምልጦት ከወጣ በኋላ አዋጁን የመሠረዝ ብርታት አልነበረውም፡፡ ለዚህም ምክንየቱ "አዋጅን መሰረዝ ለሕዝብ መንበርከክ ነው" የሚል ነበር፡፡ እርግጥ ደርግ የሕዝብ መንግሥት ስላልነበረ ሕዝብን የሚጐዳ አዋጅ አልሰርዝም ቢል አግባብ ነው፤ኢህአዴግስ? (የሕዝብ ብሶት የወለደኝ ነኝ¡) ይል አልነበር እንዴ? ከደርግ እንዴት እንለየው?

## በጋሞ ጎፋ . . .

ከገፅ 1 የዞረ

የሚሾሙትም የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ኃይማኖት ተከታዮች ናቸው በሚል ሆን ብለው በአካባቢው ግጭት እንዲፈጠር ማድረጋቸው እየተነገ ይገኛል፡፡ ለተፈጠረውም ግጭት ዞኑ የወሰደው የማጣራትም ሆነ የእርምት እርምጃ እንደሌለ ተጠቁሟል፡፡

በተያያዘ ዜና በዞኑ ጨንቻ ወረዳ ጥር 21 ቀን 2004 ዓ.ም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች የአስተርዮ ቅድስት ማርያም ንግስ በዓልን ምዕመናን በጨንቻ ከተማ እያከበሩ፣ ካህናቱም ታቦቱን ይዘው በጉዞ ላይ ኃይማኖታዊ ሥርዓት እየተፈፀሙ ሳለ አንድ የማረሚያ ቤት ፖሊስ ሥርዓቱን ጥሶ በታቦቱ ፊት በመገኘቱ የቤ/ክርስቲያኒቱ ሥርዓት አስከባሪዎች ወደ ጥግ ሂድ ብለው ሲነግሩት ግርግር በመፍጠሩ ምዕመናኑ ፖሊሱን ይዘውት ወደ ጥግ አውጥተውታል ብለዋል፡፡ በዚህም ፖሊሱ በመበሳጨት እቤቱ በመሄድ ክላሽንኮቭ ጠብመንጃ ይዞ በመምጣት ምዕመኑ ላይ በመተኮስ አንድ የዶኮ ቀበሌ ነዋሪ ወዲያውኑ ህይወታቸው ሲያልፍ ሌሎች ሰዎች መቁሰላቸውንና በአርባ ምንጭ ሪፈራል ሆስፒታል ህክምና ላይ እንደሚገኙም ምንጮቻችን ጠቁመዋል፡፡

የአካባቢው ማኅበረሰብም ከዚህ በፊት በኮንሶ፣ በጊዶሌ እና ጉማይዴ (ሰገን) አካባቢ ተመሳሳይ ግጭት ተፈጥሮ የብዙ ሰዎች ህይወት ማለፉንና ከመንግስትም መፍትሄ አለመገኘቱን አስታውሰው ከዚህ በኋላ እያየን አንሞትም ራሳችንን በመከላከል የራሳችንን እርምጃ እንወስዳለን በማለታቸው በአካባቢው ውጥረት መንገሱ ተጠቁሟል፡፡ በዞኑም በርካታ የመልካም አስተዳደር እጦት መከሰቱንና ነዋሪውም በተደጋጋሚ የመብት ጥያቄ እያነሳ መልስ እንዳለገኘ በአርባ ምንጭና አካባቢዋም ከወቅታዊ የሀገሪቱ የኑሮ ችግርና ሥራ አጥነት በተጨማሪ ሴቶች በቀን እየታፈኑ አርባ ምንጭ ጫካና በተለምዶ አውሮፕላን ማረፊያ በሚባል ሥፍራታፍነው እየተወሰዱ እየተደፈሩ እንደሆነ ነዋሪዎቹ ለዞኑ መስተዳደር ሰላምና ፀጥታ ዘርፍ ተደጋጋሚ ጥቆማ ቢያቀርቡም መፍትሄ እንዳላገኙና ችግሮቹ እየተባባሱ መምጣታቸውም ተገልፃዕል፡፡

2ኛ ዓመት ቅጽ.2 ቁ.28



# በሀድያ ዞን ሊደረግ የነበረው ውይይት መቋረጡ ተገለፀ

ብሥራት ወ/ሚካኤል

በመልካም አስተዳደር እጦትና በመሬት ወረራ ዙሪያ በደቡብ ክልል በሀዲያ ዞን ሊደረግ በነበረው ስብሰባ ነዋሪው ሕዝብ ረግጦ መውጣቱ ተገለፀ፡፡ የክልሉ እና የዞኑ አመራሮች በተገኙበት በሆሣዕና ከተማ እሁድ ጥር 14 ቀን 2004 ዓ.ም በዞኑ ስላለው የመልካም አስተዳደር እጦትና በመሬት ወረራ ዙሪያ ውይይት ለማድረግ በሀዲያ ባህል አዳራሽ የአካባቢው ነዋሪ ተጠርቶ ስብሰባው ቢጀመርም በወቅቱ በተፈጠረው አለመግባባት ውይይቱ መቋረጡን የዜና ምንጮቻችን ገልፀዋል፡፡

በተለይ ጥሪ የተደረገላቸው ነዋሪዎች በዞኑ ከፍተኛ አመራሮችና በከተማው አስተዳደር የሙስና ተግባር እና ብልሹ አሰራር የፈፀሙ አካላትን ስም ከነድርጊታቸው ሲገልፁ አወያዮቹ "የሰው ስም አትጥቀሱ ስብዕናቸውን እየነካችሁ ነው፤ችግሮቻችሁን ብቻ ጥቀሱ" የሚል አስተያየት ሲያቀርቡ የውይይቱ ተካፋይ ሕዝብም "ታዲያ ለምን ጠራችሁን? ሙስና የፈፀሙትን እያበረታታችሁ የቦታ ለውጥ በማድረግ የክልሉ ከፍተኛ ባለሥልጣናት እያደረጋችሁ እናንተ ያልታረማችሁና ያላረማችሁትን እኛ ምን እንድናደርግ ነው የምትፈልጉት?" የሚሉ ጥያቄዎችን እንዲሰነዝሩ ተጠቁሟል፡፡ በዞኑ ከፍተኛ ሙስናና በደል በነዋሪው ሕዝብ ላይ ፈፅመዋል ከሚባሉት ውስጥ በስብሰባው ላይ አሁን የደቡብ ክልል ፀረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር የሆኑት አቶ መለስ ዓለሙ እንደሚገኙበት የተገለፀ ሲሆን በዚህም የክልሉና የዞኑ አመራሮች ቅር በመሰኘት በድጋሚ የሰው ስም እንዳይጠቅሱ ነዋሪውን ሲያስጠነቅቁ ተሳታፊው ሕዝብ በንዴት ስብሰባውን ረግጦ መውጣቱ ተገልጿል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከዞኑ ንግድና ኢንድስትሪ ቢሮ ተወክለው በውይይቱ ላይ እንዲሳተፉ የተላኩ ባለሙያ አቶ አጫሞ ቦቄ በአዳራሹ ቢገኙም ይሄ ስብሰባ አንተን አይመለከትም፤ስለዚህ አዳራሹን ልቀቅና ውጣ" የሚል ትዕዛዝ እንደተሰጣቸው እሳቸውም "እኔ ከመስሪያ ቤቴ ተወክዬ የመጣሁ ባለሙያ ነኝ ማስረጃም ይዤለሁ፤ሌላው የሀገር ጉዳይ ስለሆነ ይመለከተኛል" የሚል መልስ ሲሰጡ አለመግባባት እንደተፈጠረና አቶ አጫሞም ተሳታፊውን ላለመረበሽ መውጣታቸው ተጠቁሟል፡፡ ይሁን እንጂ በመጨረሻም የእሳቸው እንዲወጡ መደረግ ተከትሎ ተሳታፊው ህዝብ ተቃውሞ ቢያሰማም ከመድረኩ ምላሽ ባለመገኘቱ ሕዝቡ ስብሰባውን ጥሎ በመውጣቱ ውይይቱ መቋረጡንና ለሌላ ጊዜ እንዲተላለፍ ተገልጿል፡፡ አቶ አጫሞ ተቃዋሚ ፖለቲከኛ መሆናቸውም ከሥፍራው የደረሰን ጥቆማ መረዳት ተችሏል፡፡

# የትምህርት ደረጃቸውን ያሻሻሉ ባለሙያዎች የደረጃ ዕድገት መከልከላቸውን ገለፁ

ብሥራት ወ/ሚካኤል

በአማራ ክልል ሰሜን ወሎ ዞን ዋድላ ወረዳ የሚገኙ የግብርና ባለሙያዎች የደረጃ ዕድገት መከልከላቸውን አስታወቁ፡፡ ባለሙያዎቹ ከዚህ በፊት በዲፕሎማ መርሃ ግብር ተምረው በወረዳው ግብርና ቢሮ ተቀጥረው እየሰሩ እንደሆነ፤በመንግሥት የትምህርት ማሻሻያ ዕድል ሳያገኙ በመቅረታቸው በራሳቸው በተለያዩ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚሰጥ ትምህርት ተከታትለው ደረጃቸውን ቢያሳድጉም ማሻሻያው እንዳልተፈቀደላቸው ጠቁመዋል፡፡ መንግሥት ተምረው ራሳቸውን ለሚያሻሽሉ የመንግሥት ሰራተኞች ከሚኒስትሮች ጀምሮ ድጋፍ እንደሚያደርግ በተደጋጋሚ ቢናገርም በአማራ ክልል ግን በተለይ በግብርናው ዘርፍ ተግባራዊ እየተደረገ አይደለም ሲሉ ባለሙያዎቹ ያላቸውን ቅሬታ ገልፀዋል፡፡ ቅሬታቸውንም ለክልሉ ግብርና ቢሮ ቢያቀርቡም ወረዳው ይሰጣቸው የነበረውን መልስ በመድገም የክልሉ ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ገድሉ አንዳርጋቸው ባለሙያዎችን "የእናንተ የትምህርት ማሻሻያ አይያዝም" የሚል መልስ እንደሰጧቸውና ምክንያቱን ግን እንዳልገለፁላቸው ተናግረዋል፡፡ ይህንንም ለማጣራት የክልሉ ግብርና ቢሮ ኃላፊ የሆኑት አቶ ገድሉ አንዳርጋቸውን በተንቀሳቃሽ ሥልካቸው ደውለን ስለ ጉዳዩ መልስ እንዲሰጡን በተደጋጋሚ ብንሞክርም አልተሳካም፡፡ ይሁን እንጂ እነሱን በተመለከተ ከግብርና ሚኒስቴር የተላለፈ መመሪያ እንዳለ ጠይቀናቸው የሚመለከተው ክልሉን ነው ሲል ምላሽ ሰጥቷል፡፡

# መሬትን ከህዝብ ነጥቆ ለከበርቴዎች መስጠት የኮሎኒያሊስቶች አገዛዝ እንጂ የዴሞክራሲያዊ መንግስት ባህርይ አለመሆኑን መዐህድ ገለፀ

ብዙአየሁ ወንድሙ

"መሬት የመንግስትና የህዝብ ንብረት ሆኖ ሳለ መንግስት ከህዝብ ነጥቆ በሊዝና በጨረታ ለከበርቴዎች መሸጡ የኮሎኒያሊስት አገዛዝ እንጂ የኢትዮጵያዊ ዴሞክራት መንግስት ሊያሰኘው አይችልም" ሲል የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት/ መአህድ/ አስታወቀ፡፡ መዐሕድ ይህንን ያሳወቀው ጥር 24 ቀን 2004 ዓ.ም ባወጣው ባለ ሦስት ገጽ መግለጫ ነው፡፡

የአዲሱን የከተማ ቦታ በሊዝ ስለመያዝ የፀደቀውን አዋጅ በመቃወም የወጣው መግለጫ እንደሚዘረዝረው የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ በጉዳዩ ላይ ተወያይቶ "ፓርቲው የዜጐችን ሰብአዊ መብትና የግል ንብረት እንዲጠበቅ እንደሚታገል አቋም ላይ ደርሰናል" ብለዋል፡፡ "ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በግልም ሆነ በጋራ ንብረት የማፍራት የመጠቀም፣ የመሸጥ የመለወጥና የማውረስ መብት እንዲኖረው የማድረግ የመዐሕድ የፖለቲካ ፕሮግራም ነው፡፡" ይላል፡፡

መግለጫው በማያያዝም ሲዘረዝር "በአሁኑ ወቅት እንደሚደረገው እንደ ኢህአዴግ ቢሆንማ ኖሮ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር ባልተገኘችም ነበር፡፡ ከጥንታውያን ጠላቶቻችን ይቅርና በቅርቡ በ1990 ዓ.ም ባድሜ በተባለው የሰሜኑ የሀገራችን ክፍል መስዋዕትነት የተከፈለበት ጦርነት ለምን አስፈለገ? በአሁኑ ወቅት ወደተቀረው የኢትዮጵያ ክፍል ስንገባ ዳርዳሩ አልቆ መሀል በመምጣት የግለሰብ ብሎም በተጓዳኝ የቡድን መብቶችን ጨርሶ በማጥፋት ሕዝብን በጨቆና ቀንበር ሰንጎ ለመያዝና በአጠቃላይ የመንግስት አደግዳጊና ጭሰኛ አድርጎ ለመግዛት የታለመ በዓለም ደረጃ ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቅ አዲስ የአገዛዝ ስልት እየመጣብን መሆኑን ማስረጃዎችንም በማጥፋት ስር የሰደደ ኢትዮጵያውያንን የመጥላት አባዜ ነው እንላለን፡፡" ካለ በኋላ አዋጁ የዜጐችን ህገ መንግስታዊ መብት መጣሱን ይገልጻል፡፡

በመጨረሻም መግለጫው እንደሚገልፀው "ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ለፍቶ ጥሮ ግሮ የግል ንብረት ባለቤት የመሆንና በዚህም ንብረት እንዲጠቀምበት ሙሉ መብቱ እንዲከበርለት ያስፈልጋል፡፡ ሆኖም መንግሥት አሁን ያወጣው አዋጅ ይህን መብት በመግፈፍ ሕዝቡን መጠለያ በማሳጣት ለድህነት ዳርጎታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በየጊዜው በብዙሀን መገናኛ በተለይ በቴሌቪዥን ከደርግ ጨቋኝ አገዛዝ አወጣኋችሁ በማለት ለ17 ዓመታት ያደረጉትን ትግል በየጊዜው ያሳዩናል በእውነቱ ሁኔታዎችን ስንገመግማቸው ያደረጉት ትግልና መስዋዕትነት ለራሳቸው ስልጣን ላይ መቆናጠጫ እንዲሁም ሀገርንና ወደብን አሳልፎ ለመስጠት፣ ወገኖቻቸውን ለመጥቀም እንጂ ለመላው ኢትዮጵያ ነፃነት እንዳልሆነ እንረዳለን፡፡ ሌላው እጅግ የሚያሳዝነው የኢትዮጵያን ሕዝብ ንብረት ያለውንና የሌለውን ለመከፋፈል መሞከራቸው ነው፡፡ "ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ንብረት ቢኖረውም ባይኖረውም አዲስ ሕግ በሚወጣበት ጊዜ ለመደገፍ ወይንም ለመቃወም መብቱ ነው፡፡ የኢህአዴግ መንግስት ባለስልጣናት ግን ንብረት የሌላቸውን ያለ አንዳች አመክንዮ የሊዙን አዋጅ እንዳይቃወሙ ማሳሰቢያ አይሉት ማስጠንቀቂያ ሰጥተዋል፡፡ ይህ ሁኔታ በዓም አቀፍ ደረጃም ሲታይ፡- እንግሊዝ ከብዙ የቅኝ ግዛት አገሮቿ ጋር ከ99 ዓመት በኋላ ያለአንዳች ካሳ አገራቸውን ለቆ ለመሄድ ስምምነት አድርጎ ነፃነታቸውን ሰጥቷል፡፡ አፄ ምኒልክም የባቡር መስመርን በሚመለከት ከፈረንሳይ መንግስት ጋር ለ99 ዓመት ውል ተፈራርመው ጊዜው ሲደርስ ፈረንሳይ ያለአንዳች ካሣ መስመሩን አስረክባለች እኛ ኢትዮጵያውያን በምን ምክንያት ነው መሬት ለ99 ዓመት በሊዝ ይዘን ለልጅ ልጆቻችን ለማውረስ በሚሊዮን የሚቆጠር ሀብት አፍስሰን እስከ 20 ከዚያም በላይ የምንሠራውን ፎቅ መንግሥት ከፈለገ ያለአንዳች ካሣ ለቀን የምንሄደው? በመሆኑም የሊዝ ማነቆ በአጠቃላይ ስንመለከተው በስነ ልቡና፣ በማህበራዊ መስተጋብር እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በሀገሩ ሠርቶና ከብሮ የሚኖርበትን ትልቅ ሀገራዊ ፋይዳ የሚያፋልስ በመሆኑና መሬትን የመቀራመትና በመሬት ላይ ያለውን ጥንተ ይዞታ ከስር መሠረቱ በማጥፋት የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት (መዐሕድ) የሚያስተላልፍልህ መልዕክት በዘር፣ በጎሣ፣ በብሄር የተጠመደብህን ዜግነትህን የማጥፋት ስራ በጥሰህ በመጣል ነፃነትህን እንድታስከብር ታሪካዊ ጥሪ እናቀርብልህለን፡፡" በማለት ያጠቃልላል፡፡

# የኦሮሚያ ትራፊክ ፖሊስ ለሌሎቹ ምሳሌ ሊሆን እንደሚገባ ተገለፀ

ብዙአየሁ ወንድሙ

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትራፊክ ፖሊስ የሚያከናውናቸው ደንብ የማስከበር ሥራ ለሌሎች ክልሎችም ጥሩ ምሳሌ ሊሆን ይገባል፡፡ ሲሉ የትራንስፖርት ተገልጋዮች ለዝግጅት ክፍላችን ገለፁ፡፡ በተለይ ከአዲስ አበባ ወደ ኦሮሚያ ዞንና ወረዳ ከተማዎች በተለያየ ምክንያት በትራንስፖርት ተንቀሳቅሰው የተመለሱ ተገልጋዮች እንደሚሉት "የኦሮሚያ ትራፊክ ፖሊሶች የሚያከናውኑት ቅድመ አደጋ ክትትልና ቁጥጥር እጅግ እንዳስደሰታቸው" ይናገራሉ፡፡

የትራንስፖርት ተገልጋዮች እንደሚሉት "በኦሮሚያ ክልል አንድ ተሽከርካሪ ከተገቢው ፍጥነት በላይ ሲበር ከታየ ትራፊክ ፖሊስ አስቁሞ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡ ሹፌሮች ሹፌር መሆናቸውን የሚገልጽ መደበኛ ልብስ አላቸው፡፡ ልብሱን ሳይለብሱ ቀበቶ ሳይታጠቁ የሹፌር መቀመጫ ላይ አይቀመጡም፡፡ ከመኪናው የጭነት ልክ ውጪ ትርፍ ሰው አይጭኑም፡፡ አደጋ ከመድረሱ በፊት እግር በእግር እየተከታተሉ ቁጥጥር ያደርጋሉ፡፡ መመሪያ ይሰጣሉ፡፡ በመሆኑም በኦሮሚያ ጥሩ ነገር ማየት ችለናል፡፡ የትራፊክ አደጋም በእጅጉ የቀነሰ ነው" ይላሉ፡፡

በአዲስ አበባ ያለውን የትራፊክ ፖሊሶች ክትትልና ቁጥጥር ሲገልጹ "በአዲስ አበባ ትራፊክ ፖሊሶች ሥራቸው ዘወትር የዘመቻ ሥራ ነው፡፡ በወረት አንድ መመሪያ ያወጡና ወከባ ይፈጥራሉ፡፡ ወዲያውኑ ይተውታል፡፡ ጥፋቶች ተመልሰው ቦታቸው ላይ ይመለሳሉ፡፡ ሰው በሰው ላይ መጫን፤ መንገድ መቆራረጥ፤ ሲፈልጉ አጭር ተጓዥን መከልከል፡፡ የቀጠና ሥምሪት አለመጠበቅ፤ የተለመደ ነው፡፡ በሱማሌ ክልልም በተመሳሳይ ሁኔታ ይፈፀማል፡፡ በተለይ በሱማሌ ክልል የፍጥነት ጉዞና ከመጠን በላይ በየቦታው የሚከሰተው አደጋ መንስዔ የክትትልና ቁጥጥር ማነስ ነው፡፡ ስለዚህ ሁሉም ክልሎች ከኦሮሚያ ትራፊክ ሊማሩ ይገባል፡፡" ሲሉ አስተያየታቸውን ይሰጣሉ፡፡

# መድረክ በሊዝ አዋጁ ላይ ሊመክር ህዝብ ጠራ

ብዙአየሁ ወንድሙ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ /መድረክ/ በቅርቡ በወጣው የከተማ ቦታ ሊዝ አዋጅ ላይ ከአዲስ አበባ ከተማ ህዝብ ጋር ሊወያይ መወሰኑን ከመድረኩ ጽ/ቤት ያገኘነው መረጃ ያስረዳል፡፡ ከመድረክ ጽ/ቤት ኃላፊ በአቶ ዓለሙ ኮይራ ፊርማ ለስብሰባ አዳራሽ በተጻፈው ደብዳቤ መረዳት እንደተቻለው "መድረክ የካቲት 4 ቀን 2004 ዓ.ም በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 አስተዳደር አዳራሽ ከ7 ሰዓት ጀምሮ ከህዝብ ጋር ውይይት ያደርጋል" ተብሎአል፡፡ በሚቀጥለው እሁድ እለት ቄራ አካባቢ በሚገኘው በተለምዶ "አልማዝዬ ሜዳ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በቀድሞ ወረዳ 20 ቀበሌ 42 አዳራሽ በሚደረገው በዚህ ስብሰባ ላይ ታዋቂ ምሁራን ተገኝተው በሊዙ አዋጅ ላይ ሐሳብ እንደሚያቀርቡ" ታውቋል፡፡ ጽ/ቤቱ እንዳለው "ማንኛውም ሰው በስብሰባው ላይ መሳተፍ የሚችል ስለሆነ ይህ የማንኛውንም ዜጋ ህልውና የሚፈታተን አዋጅ ላይ መነጋገር አስፈላጊ ስለሆነ ሁሉም ኢትዮጵያዊ እንዲገኝ ጥሪውን ያቀርባል" በማለት ጥሪውን አቅርቧል፡፡

ዜና

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ /አንድነት/ መድረክ ጥር 27/05/04 ዓ.ም በእየሩሳሌም ሆቴል በከተማ ሊዝ አዋጅ አንድምታ ላይ የፓናል ውይይት አዘጋጅቶ ነበር:: ኢ/ር ዘለቀ ረዲና የተከበሩ አቶ ግርማ ሰይፉ የመሩትን ውይይት በስፍራው ተገኝቶ የነበረው ባልደረባችን ሰለሞን ስዩም ቀጣዩን ዘገባ አቅርቧል::

# "አሁን መሬት የሌለው ሁሌም የለውም"

ውይይቱን የመሩት ዶ/ር ኃይሉ አርአያ የተመድ አባል ከሆኑት 194 ሀገራት መካከል መሬቱን በመንግሥት ቁጥጥር ስር የያዙ አምስት አገሮች ቬትናም፣ ኩባ፣ ሰሜን ኮሪያ፣ ቻይናና ኢትዮጵያ ብቻ መሆናቸውን በማስታወስ ነበር:: ውይይቱን የጀመሩት እነዚህ ሀገራት በምሳሌነት አይቀርቡም ያሉት ዶ/ር ሀይሉ በተለይ ቻይና ግርምቢጥ ባህሪ በመያዟ ዕድገቷ በተለየ ሁኔታ መታየት አለባት ብለዋል:: በሌላ በኩል ኢህአዴግ ከ200,000 ሺህ የማይበልጡ ሰዎች መሬት በግል በመያዛቸው በምርጫም ሆነ በሌላ መልኩ ጫናቸው ይህን ያክል ነው ቢልም ሂሳቡ መሆን የነበረበት በነዚህ ሰዎች መሬት ዙሪያ ባሉ ዘመድ ወዳጆችና ቤተሰቦች ቁጥር (nuclear family ) ነው ብለዋል::

በመቀጠል የውይይቱን መግቢያ የወሰደው ኢ/ር ዘለቀ ረዲ የኤፌዴሪ ህገ-መንግሥት አንቀፅ 8 ከ1-3 ህዝቡን የሉዓላዊ የስልጣን ባለቤት ናቸው ቢልም ነገር ግን መንግሥት ወስዶባቸዋል ይላሉ:: ኢ/ሩ አቶ መለስ ምርጫ 2002 ተከትሎ "ተቃዋሚዎች ምክር ቤት ቢገቡም ባይገቡምበሀገር ጉዳይ እናወያያቸዋለን፣ እናማክራቸዋለን" ያሉትን አስታወሰው "አሁን ግን እንኳን ተቃዋሚዎችን ወከለነዋል የሚሉትን ህዝብ ማማከርና ማዳመጥ አልፈለጉም" ሲሉ ይተቻሉ::

ኢ/ር ዘለቀ ህገ-መንግሥቱ አንቀፅ 40/3 ጠቅሰው መሬት የመንግሥት እና የሕዝብ ነው መባሉ በሁለት መልኩ ሴራ እንዳለው ገልፀዋል፤ አንደኛ መንግሥትን የሚወክለው የሉዓላዊ የሥልጣን ባለቤት እንዴት በመንግሥት እንደተቀደመ የጠየቁ ሲሆን በሌላ መልኩ "ተከራይ (በሊዝ የተከራየ) እንዴት ባለቤት ሊሆን ይችላል?" ሲሉ ጠይቀዋል::

ዜጎች ገንዘብ የማፍራት መብታቸው መነፈጉን ሲያወሱም "ገንዘቡ ባለበት በዚያ ልቡ አለ" የሚለውን ሀይማኖታዊ ቃል አንስተው አሁን ግን መሬት እንደማይኖረው የተገነዘበውና የተነጠቀው ኢትዮጵያዊ ልቡ ሸፍቷል ብለዋል:: በሌላ አባባል "ድሃ ሀገር እንጂ ቤት የለውም" በሚል "ቤተ ክርስቲያን አካባቢ እንኳ የኔ ቢጤዎች የተከበረላቸው የመለመኛ ቦታ አላቸው" ብለዋል:: በሌላ በኩል ኢህአዴግ ሰዎችን በመከፋፈል በተለይ መሬት የሌለውን አካል እንደማይመለከተው አድርጎ ከትግሉ ለማውጣት እንደሚሞክር አውስተው ትርጉሙ ግን "ለዘለዓለም መሬት አይኖርም፤ ድሃ ሆነህ ትኖራለህ" እንደማለት መሆኑን አብራርተዋል::

ቀጣዩ አቅራቢ የተከበሩ አቶ ግርማ ሰይፉ ነበሩ:: አቶ ግራማ ድሃ ሁሌም ድሃ የመሆን ምኞት እንደሌለው በማስታወስ ኢ/ር ዘለቀን ሀሳብ በማጠናከር ነበር የጀመሩት:: አሜሪካን ሀገር ሰራተኞች ሰራተኛ ማህበራቸው በአሰሪዎቻቸው ላይ ከፍተኛ ጫና እንዲያሳድር እንደማይፈልጉ አብራርተው አብዛኛው ሰራተኛ አንድ ቀን አሰሪ መሆን ስለሚፈልግ በቆፈረው ጉድጓድ እንዳይገባ ነገር ከመተብተብ እንደሚጠነቀቁ አስረድተዋል:: በመሆኑም ኢህአዴግም ለልጅ ልጆቹ መሬት የሌላቸውም ለቀጣይ ተስፋቸው ፍፁም ሊቃወሙት የሚገባ ጉዳ መሆኑን ገልፀዋል:፤

አቶ ግርማ ኢህአዴግ መሬትን ዋነኛው የፖለቲካ መሣሪያ አድርጎ ለመጠቀም በመፈለግ በህገ-መንግሥት እንደከደነው ገልፀው ነገር ግን ህገ-መንግስቱም ቢሆን እንደማይሻሻል አድርጎ ማቅረቡ አንቀጽ 104 እና 105ን ማን አስገባ የሚያሰኝ መሆኑን አብራርተዋል:: ሀሳባቸውን ሲያጠናክሩም መጽሐፍ ቅዱስ ግን ይሻሻላል የሚል ካለመያዙም በላይ የጨመረ የቀነሰ መዓት እንደሚጠብቀው በትክክል ማኖሩን አስታውሰዋል:: አቶ ግርማ "ከሌላ ጊዜ በሌላ ህግ ብንጫወትም ለአሁኑ በዚሁ በህግ አግባብ እንሄድ በጓድ ኢህአዴግ መብት ነጋ ከሚያፈርሰው ህገ-መንግሥት ጫናውን እንዲያነሳ ማስገደድ እንዳለብን አጽንኦት ሰጥተዋል::

"ጅቡቲ የኢትዮጵያ ነበረች፤ በሊዝ ተላለፈች፤ይህየነሆነው በሊዝየወሰዷትመንገድ እንዲሰሩልን ነበር፤ አሁን ግን አትመለስልንም" ያላት አቶ ግርማ ኢህአዴግ በተመሳሳይ መሬት በሊዝ አከራይቼ /99 ዓመታት . . ./ ውሃ፣ መብራት፣ መንገድ እሰራላችኋለሁ ይለናል፤ ነገር ግን ጋምቤላ ስለመመለሱ ያጠራጥራል" ሲሉ አሉታዊ ማሳያውን ተመልክተዋል:: የሊዝ አዋጁ አንቀጽ 5 የከተማ መሬቶች ወደ ሊዝ ስርዓት የሚገቡ መሆናቸውን ያትታል:: ከተማ ማለት 2000 ሰዎች ኖሮት 54% ከግብርና ስራ ውጭ የሚተዳደሩባት ትንሽ መንደር ናት:: "ታዲያ ማን ነው እዚያ ሄዶ መሬትን ለተወሰነ ጊዜ ገዝቶ (በሊዝ ተከራይቶ) የሚያለማት?" የሚሉት አቶ ግራማ "በነፃ ሰጥተውም ባለ ሀብት ቢሄድላቸው መልካም ነበር" ብለዋል::

በሌላ በኩል አንቀጽ 5/4 ተፈፃሚነቱ እስከ 5 አመት ሊዘገይ እንደሚችል ይገልፃል:: ይህ የምርጫ ካርድ መግዣ መሳሪ መሆኑን ያዩት አቶ ግራማ "ኢህአዴግ ሁላችንም በቀበሌ/ ኮንዶሚኒየም ቤቶ ብንኖር ይፈልጋል፤ ምክንያቱም በቤታችን ከኖርን እንደፈለገ ግቡ ውጡ ሊለን ስለማይችል" ሲሉ በኛ ላይ መብት ሊገዛበት መሆኑን አሳይተዋል:: አንቀጽ 12/5 በምደባ ስለሚሰጥ የከተማ ቦታ የከተማ አስተዳደሩ የሚወስን መሆኑን ይገልፃል:: በዚህ አጋጣሚ አንድ በመንግሥት /ቀበሌ የንግድ ቤት በህጋዊነት ተከራይተው የነበሩ ነገር ግን በመልሶ ማልማት ተነሺ ቢሆኑ የሚከተለው ችግር ሊኖረው ይችላል፤ "አንደኛ በዚህ ህግ በመጠቀም ተቃዋሚ የሆነ ህጋዊ ነጋዴን ቤቱን በማፍረስ ከጫወታ ማስወጣት በቂ ነው:: የሚወሰነው መስተዳድሩ ከሆነ ያው ይታወቃል፤ በሌላ በኩል በንግድ ላይ ያለን ከንግድ አስወጥቶ ለንግዱ ማህበረሰብ ጠቃሚ ነው ማለት እንደምን ይቻላል?"

ሌላው አቶ ግርማ "ምቀኝነት" ሲሉ የሰየሙት የከተማ ቦታ የሊዝ ዋጋን የተመለከተው ነው:: የሊዝ ዋጋ በየሁለት አመቱ እንደሚከለስ የሚያትተው ይህ ክፍል ለ50 ዓመታት የተከራየ ሰው ከ10 ዓመታት በኋላ መብቱን ማስተላለፍ ቢፈልግ ዋጋው አይጨምርለትም:: መንግሥት ግን በዚህ 10 ዓመት ቢያንስ 5 ጊዜ የዋጋ ጭማሪ በማድረጉ ከፍተኛ ክፍያ የሚቀበል ሲሆን አስተላለፊው ቀድሞ በተገመተው ዋጋ የ40 ዓመታት ክፍያና ተነሺ የሆነው ንብረቱ ዋጋ እየረከሰ መምጣት እንደሚተርፈው ነው:: በመሆኑም "ከመሬት ይልቅ ወርቅ መግዛት የሚመከር ነው" ሲሉ መክረዋል:: አቶ ግርማ "መንግሥት ህፃን ልጅ ሆኖብናል፤ ሁሉንም የኔ ነው ከማለቱም በላይ አፍርሶም የኔ ነው ይላል" ብለዋል::

አንቀጽ 22/23 የግንባታ ጊዜን ሲወስን ቦታዎችን ለይቶ ያለማየቱን የሚያብራሩት አቶ ግርማ በተለይ የቁጠባ ባህላችንን ከግምት ያላስገባ እና በ24-30 ወራት ውስጥ በሚል ለመንጠቅ የተሰራ መሆኑን አብራርተዋል::

አንቀጽ 24ትም በዋስትና ስለሚስተላለፍ በሚገልፀው ክፍሉ "ማስተላለፍ የሚችለው እኔ ባለሁበት እና ትርፍም ካለ እኔ እወስዳለሁ የሚል ሆኖ እውነትም "ደላሎችን ጠራርገን እናስወጣለን" ያሉት ራሳቸው በዚሁ መልኩ ደላላ ለመሆን መሆኑን አሳይተዋል:: ከዚሁ ጋር የተያያዘው በተደጋጋሚ ማስተላለፍ ማሳገዱን የሚገልፀው ነው:: "ይህ ምቀኝነት ነው" ይላሉ አቶ ግራማ::

አንቀጽ 24/5 ስለ ዋስትና አንስቶ የሊዝ መብቱን በዋስትና ያስያዘ ሰው የዋስትና ግዴታውን ባለመወጣቱ በዋስትና መያዣው ላይ የፍርድ አፈፃፀም ትዕዛዝ የተላለፈበት የዕዳ ጥያቄ ከቀረበ አግባብ የለው አካል የሊዝ ውሉን አቋርጦ መሬቱን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 22/3 መሠረት የሚቀነሰውን ተቀናሾች አስቀርቶ ቀሪውን ለዋስትና ባለ መብት ይከፍላል ይላል:: እንግዲህ ዋስትና የሚይዘውና ብድር የሚሰጠው ባንክ/የገንዘብ ተቋም ነው:: ታዲያ "ከተረፈ ገንዘብ ታገኛለህ ተብሎ ብድር የሚሰጥ ይመስላችኋል?" ሲሉ አቶ ግርማ ይጠይቃሉ:: "ይህ ዜጎች ንብረታቸውን ባለው የገበያ ዋጋ አሲይዘው እንዳይበደሩና ሀብት እንዳያፈሩ የሚገድብ ኢ-ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ ነው" ያሉት አቶ ግርማ ተጠያቂነት ከሌለበት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ውጭ ሌሎች ከጨወታ ይወጣሉ" ይላሉ:: በሌላ በኩል ቤትን ከመሬት ለይቶ ማየት "ፀሐይን ስታዩ ሰማዩን አትዩ!" የማለት ያክል ነው ብለዋል::

በመጨረሻም አንቀጽ 30ን ጠቅሰው የከተማን ቦታ ማስለቀቅን እና የካሳ ክፍያን በተመለከተ "የይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በየክልል ከተማ መስተዳድሮች ይቋቋማል" ማለቱን አውስተው "በፍትህብሄር አይዳኝም ማለቱ ኢንቬስትመንቱን የካድሬዎች የሙስና ምንጭ ለማድረግ የታሰበ ይመስላል" ሲሉ ገልፀው እነዲህ አይነቱ አግባብ ግለሰቦች በራሳቸው ላይ የማይሰሩትን ሙስና ሌላ አካ እንዲሰራባቸው መስራት ነው" ብለውታል::

# በአገሪቱ ውስጥ . . .

ከ ገፅ 1 የዞረ

ሠራተኞች ተይዞ በምርጫ 97 ከተቃዋሚዎች ጋር ተሳትፈሐል ተብሎ ያለ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ሰንደፉ ፖሊስ ካምፕ 3 ወር ታስሮ ተፈቷል::" ይላል::

ህገ ወጥ እስርን በሚመለከት "ታደሰ መለስ፣ እስክንድር መላኩ፣ መለስ ሰጠኝ፣ አሸናፊ አየለ፣ ማንደፍሮ አከልነው፣ ቴውድሮስ አያሌው የተባለ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት የመኢአድ አደረጃች ወጣቶች ከአማራ ክልል ጐጃምና ወሎ ተይዘው ቃሊቲ በእስር ላይ ይገኛሉ ደሳለኝ ደበል፣ ተስፋ ሞተር፣ ሳምሶን ዓለሙ፣ በላይ ኮርሜ፣ ኢታና ሰንበቶ፣ ነጋሽ ኩሽ፣ ኑራ በድሩ የተባሉ ከኦሮሚያ ክልል የተለያዩ ዜኖች ተይዘው በእስር ላይ ሲገኙ፤ ቀኖ ማቲዮስ፣ መንግስቱ ሞሲሳ፣ አያና ቀበታ፣ ኩመራ ሰንበታና ታዬ ዳምጠው ከኦሮሚያ ክልል ተይዘው መለቀቃቸውን" መግለጫው ይዘረዝራል:: አቶ መላኩ በየነ የተባሉ የአዲስ አበባ ነዋሪ ከግለሰብ ጋር በነበራቸው ገንዘብ ብድር አለመግባት ተከሰው ላንቻ ፖሊስ፤ ቂርቆስ ክ/ከተማ ፖሊስ መምሪያና አዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ታስረው ጨለማ ቤት ታስረው በተደጋጋሚ ድብደባና ስቃይ እንደደረሰባቸው የአካል ጉዳት እንደደረሰበት ገልፀዋል" ተብሎአል::

ህገ ወጥ እስርና ኢ-ሰብአዊ አያያዝን መግለጫው ሲዘረዝር "በምዕራብ ጐጃም ዞን ባህርዳር ከተማ ቀበሌ 16 ውስጥ ነዋሪ በሆኑት ቤተሰብ የ60 ዓመቱ አቶ ሙጩ ዓለሙ የ45 ዓመት ወ/ሮ አበዝ አታሎ፣ የ21 ኣመቷ ወ/ሮ እመቤት ሙጫ ወንጀል የፈፀመ ልጃችሁን ደብቃችኋላ ተብለው በ6ኛ ፖሊስ ጽ/ቤት አባል በሆነ በፖሊስ ድብደባ ተፈጽሞባቸዋል:: ወ/ሪት ንጹህ ወርቅ ዱቢሳ በአዲስ አበባ ዲቪዲ ሰርቀሻል ተብላ ሁለት ወር ከ15 ቀን ህፃን ልጇ ጋር ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ አንገቷን ተጨምድዳ በቁልቁለት እየተገፈተረች ተወሰደ 6 ቀን መታሰሯን:: ከ6 ቀን በኋላ ዲቪዲውን የሰረቀቺው ፍ/ቤት ቀርባ የሰረኩት እኔ ነኝ:: ንፁህወርቅ ሰረቂ ብለኝ ነው ብለሽ መስክሪ ተብዬ ተገድጄ ነው በማለቷ ንፁህወርቅ በ300 ብር ዋስ ተብትለቀቅም ህፃን ልጇ በእስር ወቅት የእናት ጡት ባለማግኘቷ ታማ በየካቲት 12 ሆስፒታል ተኝታ ትገኛለች:: አቶ ዳኜ ቦንሳ ጐቡ በበቾ ወረዳ በኦሮሚያ ፖሊስ ፈጥሮ ደራሽ ፖሊስ ድብደባና ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ መታሰሩን" ይዘርዝራል::

የሰመጉን ሪፖርት ሙሉ ዝርዝር www.andinet.org.et ድረ ገጽን ይጐብኙ

# ወረዳ 24 የአንድነት ፓርቲ አመራሮችን መረጠ

## - በ2005 ለሚደረገው ምርጫ ጠንክሮ እንደሚሰራ ቃል ገባ

ብዙአየሁ ወንድሙ

በአዲስ አበባ ከተማ ኮልፌ ቀራኒዮ አካባቢ የሚገኘው የወረዳ 24 የምርጫ ክልል የሚገኙ የአንድነት ፓርቲ አባላት ከትላንት በስቲያ ባደረጉት ጠቅላላ ስብሰባ በተለያዩ አጀንዳዎች ላይ መክረው ውሳኔ ከማሳለፋቸውም በላይ ለሚቀጥለው ሦስት ዓመት ፓርቲውን የሚመሩ አመራር መሰየማቸውን አስተባባሪዎቹ ለዝግጅት ክፍላችን ገለጹ:: አስተባባሪዎቹ እንደገለጹት "በስብሰባው ላይ የሥራ ሪፖርት ቀርቦ ውይይት ተደርጐበት ፀድቋል:: በቅርቡ የፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ በወሰነው መሠረት ለመንቀሳቀስ ስምምነት ላይ ተደርሷል" ብለዋል::በመጨረሻም አስተባባሪዎቹ እንደሚሉት "የወረዳው የፓርቲው አባላት በ2005 ዓ.ም መጀመሪያ አካባቢ ለሚደረገው የአዲስ አበባ ምርጫ ወደ ህብረተሰቡ ወርደው ጠንክረው እንደሚሠሩና ቃል የገቡ ሲሆን" ለሚቀጥለው ሦስት ዓመት ፓርቲውን የሚመሩ አመራሮችን ሰይመዋል ተብሎአል:: በዚሁ መሠረት "ሰባት አመራሮች የተመረጡ ሲሆን አቶ ሰለሞን አበራ ሰብሳቢ አቶ አዲስ ካሳ ም/ሰብሳቢ አቶ ሲሳይ ስምኦን ዋና ፀሐፊ ሲሆኑ 4 ተጨማሪ አባላት በአመራርነት ተመርጠዋል" ተብሎአል::

# ፕሮፓጋንዳና ተጨባጭ እውነታዎች

በለጡ ጉሹ ወ/ሚካኤል

የኢህአዴግ የፕሮፓጋንዳ ማሽን የሆነው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ጥር 7 ቀን 2004 ዓ.ም ከምሽት ዜና ፕሮግራሙ በኋላ የውጭ ዜጐች በኢትዮጵያ እያካሄዱ ያለውን የመሬት ወረራና ቅርምት በመደገፍ ዘጋቢ ፊልም (documentary film) ያሳየ ሲሆን፣ እኔም ጓደኞዬ እንድከታተለው አስቀድሞ በነገረኝ መሠረት እያንገሸገሸኝም ቢሆን አይቼው ተገርሜአለሁ፡፡

በፊልሙ ላይ እንደተመለከትኩት፣ እስካሁን ወደ ሦስት መቶ ሰማኒያ ሺ ሄክታር መሬት ለባዕድ ኢንቬስተር ተብዬዎች እንደተሰጠና ወደፊትም እስከ ሶስት ሚሊዮን ሄክታር የሚደርስ መሬት እንደሚሰጥ ተገልፆአል፡፡ አንዳንድ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ለምሳሌ ሂውማን ራይትስዎች (Human Rights watch) ባወጧቸው ሪፖርቶች መሠረት የኢህአዴግ መንግሥት ለባዕዳን ለመስጠት ያቀደው ጠቅላላ የመሬት ስፋት እስከ አምስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺ ሄክታር (5.6 ሚሊዮን ሄክታር) እንደሚደርስ ይነገራል፡፡

የመሬት ቅርምቱ (Land grab) እየተካሄደ ያለው ነዋሪዎችን በማፈናቀል ጭምር መሆኑ በእነዚህ የውጭ ሀገር ሪፖርቶች የተገለፀ ሲሆን ጥቅጥቅ ያሉና የብዝሃ ህይወት መሠረት የሆኑ ደኖችም እንደሚጨፈጨፉ ተዘግቦአል፡፡ በመሬት ወረራው ምክንያት ከቀዬአቸው የሚፈናቀሉ ዜጐች በደርግ ወታደራዊ አገዛዝ ጊዜ ይደረግ እንደነበረው፣ ያለፈቃዳቸው እየተገደዱ በሠፈራና በገጠር መንደር ምሥረታ ፕሮግራሞች ወደ ሌሎች አካባቢዎች እየተጋዙ እንዲሠፍሩ እየተደረገ ነው፡፡

በተቋቋሙትና ይቋቋማሉ በተባሉት ሰፋፊ እርሻዎች ይመረታሉ ተብለው የተገለፁት ሰብሎች (ሩዝ፣ የነዳጅ ተክሎች፣ ወዘተ) በአብዛኛው ዓላማ ያደረጉት የውጭ ገበያውን (export market) ሲሆን ለዚህም የሚሰጠው ምክንያት የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ግኝት ለማዳበር ነው የሚል ነው፡፡ የኢህአዴግ መንግሥት መሬቶቹን ለባዕዳን የሰጠው በረጅም ጊዜ ሊዝ (እስከ 50 ዓመታት) ይሁን እንጂ፣ የሊዝ ዘመኑ እየታደሰ ሊሄድ ስለሚችል፣ መሬቱ ወደፊት ወደ ኢትዮጵያውያን ይዞታ ለመመለሱ ምንም ዓይነት መተማመኛ የለም፡፡ አስገራሚው ነገር፣ የመሬት ኪራይ ክፍያው ከዓለም አቀፍ ዋጋ ጋር ሲታይ እጅግ አነስተኛ መሆኑ ነው፡፡ በሄክታር ከአንድ ዶላር ያነሰ የሚከፈልባቸው መሬቶች እንዳሉ የተገለፀ ሲሆን፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ግን በሄክታር እስከ አሥር ሺ ዶላርና ከዚያም በላይ እንደሚያስገኝ ተመልክቶአል (ለምሳሌ የዶ/ር አክሎግ ቢራራን ጥናቶች ይመልከቱ)፡፡

**የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን አነብናቢዎች እና የኢህአዴግ ካድሬዎች “የተሞሉትን ረቂቅ ዕውቀት” ያንበለብሉት ጀመሩ፣ በዕለቱ ጥር 7 ቀን 2004 ዓ.ም፡፡ “በጋምቤላ የመሬት እጥረት የለም፤ እኛ ለ`ፈረንጆች` የሰጠነው ታርሶ የማያውቀውን መሬት ነው፤ የጋምቤላ ሕዝብ ቁጥሩ ትንሽ ነው” እያሉ ከዚህ” ረቂቅ ዕውቀታቸው” ሊያቋድሱን ሞከሩ፡፡ ለመሆኑ ጋምቤላ የኢትዮጵያውያን መሬት አይደለም እንዴ? ኢትዮጵያውያን የመሬት እጥረት ካለባቸው ክፍላተ ሀገር (እንበል ወላይታ፣ ሰሜን አካባቢዎች፣ ወዘተ) ወደ ጋምቤላ ሄደው ሊያርሱ፣ አይችሉምን? በተመሳሳይ ጋምቤላ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በፈለጉት ክፍላተ ሀገር ተዘዋውረው ሊሠሩና ሊኖሩ አይችሉምን? ሕዝብስ ቁጥሩ በየዓመቱ እየጨመረ መሄዱ ይቀራልን? የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛትስ? ኢህአዴግ በኃይል ሥልጣን ከተቆናጠጠ ወዲህ እንኳን የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት ቢያንስ በ35 ሚሊዮን ጨምሮአል! …. .**

የኢህአዴግ መንግሥት መሬታችንን በዚህ መልክ የሚቸበችበው እኛ ኢትዮጵያውያን በጉዳዩ መክረንና ዘክረን አይደለም፡፡ ሌላው ቀርቶ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የሚባለውም ፓርላማ ተብዬ በወጉ አልተወያየበትም፡፡ ጥቅምና ጉዳቱ በግራና ቀኝ ክርክር አልተካሄደበትም፡፡ የአቶ መለስ አምባገነን አገዛዝ በደመ ነፍስ ትዕዛዝ የተጫነብን ዕዳ ነው፡፡ ከላይ በተጠቀሰው ዘጋቢ ፊልም ውስጥ በገጠር ልማት ምርምር የታወቁት ምሁር ደሳለኝ ራሕማቶ ከሚናገሩት ያለቦታው እየተቀነጨበ (out of context)፣ የኢህአዴግ መንግሥት አዋቂ፣ ብልህና አርቆ አስተዋይ፣ ምሁሩ ደሳለኝ ረሕማቶ ግን ምንም የማያውቁ ጭፍን ተቃዋሚ አድርጐ ለማቅረብ የተሞከረው ጨርሶ ይቅር የማይባል ወንጀል ነው! ደሳለኝ ራሕማቶ በተለይ በገጠር ልማት መስክ አያሌ መጻሕፍትና ጥናታዊ ጽሁፎችን ያቀረቡ እውቅ ተመራማሪ ናቸው፡፡ የመሬት ወረራውን እንኳን በተመለከተ፣ ዝም ብለው በደመ-ነፍስ አይደለም የሚናገሩት፡፡ ከመናገራቸው በፊት አስፈላጊውን ጥናት አድርገዋል፡፡ የዚህ ጥናታቸው ውጤትም በቅርብ ጊዜ ታትሞ የወጣው፣ “Land to Investors Large Scale Land Transfers in Ethiopia” የሚለው መጻሕፋቸው ነው፡፡ ይህ ጥናት የሚያመለክተው፣ ሕዝቡን ሳያማክር ኢህአዴግ የፈቀደው የመሬት ቅርምት ስትራቴጂ ከጥቅሙ ጉዳቱ እንደሚያመዝን ነው፡፡

በአንፃሩ፣ በፊልሙ ውስጥ የቀረቡት የኢህአዴግ ካድሬዎች ፓርቲአቸው እንደ ቴፕ የሞላቸውን አርቲ ቡርቲ እንደ በቀቀን ሲደጋግሙ እንደ ገደል ማሚቱ ሲያስተጋቡ ተስተውለዋል፡፡ የካራቱሪ ሕንዶች እና የሳውድ ስታር “ባለሀብቶች” ከሰማይ የወረደላቸውን ሲሳይ ሲያወድሱና ሲያንቆለጳጵሱ ተደምጠዋል፡፡ እኔ በበኩሌ በእነሱ አልፈርድም፡፡ “ጮማ መሬት” ነፃ በሚባል ክፍያ ሲያገኙ ያልተደሰቱ መቼ ሊደሰቱ ነው? በደመ ነፍስ በሚያነበንቡ ወጣት ካድሬዎች የተሞላው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን አቶ ደሳለኝ ራሕማቶን መሀይም ለማድረግ እንደሞከረው፣ ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ ከተናገሩት ውስጥ ቁንፅል ሃሳቦችንና አረፍተነገሮችን እየቀነጫጨበ፣ ካለቦታቸው እየደነቀረና እየሠነቀረ፣ ፕ/ር በየነንም አላዋቂና ጭፍን ተቃዋሚ አድርጐ ለማቅረብ ሞክሮአል፤ ግን አልተሣካለትም፡፡ ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ በትምህርትና በምርምር የተፈተኑ ምሁር ናቸው! የፕሮፌሠርነት ማዕረጋቸውን ያገኙት ከዩኒቨርሲቲ እንጂ ከጠመንጃ አፈሙዝ አይደለም! እዚህ ላይ፣ በአንድ ወቅት ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም ያሉትን መጥቀሱ ጠቃሚ ይመስለኛል፡፡ በሀገራችን ሥልጣን ከጠመንጃ አፈሙዝ ይገኛል፤ ከሥልጣን ደግሞ “ዕውቀት” ይገኛል ነበር ያሉት፡፡ በዘመነ ደርግ ኮ/ል መንግሥቱ ኃ/ማርያም ሁሉን አዋቂ ሆነው ለመታየት ይሞክሩ ነበር፡፡ ኮ/ል መንግሥቱ መድረኩ በጠየቀው መሠረት፣ አዛዥ ጀኔራል፣ የሕክምና ዶክተር፣ ኢንጅነር፣ ኢኮኖሚስት፣ የህዋ ሳይንቲስት (space scientist) ስታትስቲሺያን ወዘተ ለመሆን ይጥሩ እንደነበር በዚህም “ሕልማዊ ዓለማቸው” መሠረት በሠጡት መመሪያና ትዕዛዝ ኢትዮጵያና እኛ ኢትዮጵያውያን ምን ያህል መከራና ውድቀት እንደደረሰብን በሚገባ እናውቀዋለን!

አቶ መለስ ዜናዊም ተመሳሳይ ባሕርይ እንዳላቸው የማያውቅ ሰው ያለ አይመስለኝም፡፡ በተለይ በኢኮኖሚክስ መስክ ያሳዩት “ረቂቅ እውቀት” ይበል የሚያሰኝ ነው፡፡ “የወደብ አገልግሎት ሸቀጥ ነው፡፡ በገንዘባችን እንገዛዋለን” አሉ፣ አቶ መለስ፡፡ ይህ በቁሙ ሲመረምሩት እውነት ነው፤ በእርግጥም የወደብ አገልግሎት ሸቀጥ ነው፤ ግን በሀገራችን ወደብን አስመልክቶ የተነሳው ጥያቄ የሸቀጥነት ጉዳይ ሳይሆን፣ የባለቤትነት (owner ship) ጥያቄ ነው! በእሳቸው አመለካከት የአሰብ ወደብ የፕሬዘዳንት ኢሣያስ አፈወርቂም ሆነ የጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ልዩነት የለውም! ይህቺ ናት ኢኮኖሚክስ፤ በሌላ በኩል አቶ መለስ “መሬት ሸቀጥ አይደለም” አሉ፡፡ እጥረት (scarcity) እሴት (value) እና ዋጋ (price) ያለውን መሬት “አይሸጥም፣ አይለወጥም” ብለው ደነገጉ! ይህ መሠረታዊ የኢኮኖሚክስ ሕግን ለመሻር እንደመሞከር ነው፡፡ በፊዚክስ የስበት ሕግን (the law of gravity)በመመሪያ ወይም በሕግ ለመሻር እንደመድፈር ይቆጠራል! መሬት ሸቀጥ ለመሆን የሚያስፈልጉትን መሥፈርቶች ሁሉ ስለሚያሟላ የመሬት ገበያ መኖር የግድ ነው፡፡ ይህም መሸጥ መለወጥን ያስከትላል፡፡ ይሁንና መሬት የእግዜር ስጦታ እንደሚሆን፣ ከመነሻው ፍትሐዊ በሆነ መንገድ መከፋፈል እንዳለበት ይታወቃል፡፡

የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን አነብናቢዎች እና የኢህአዴግ ካድሬዎች በዚህ መልክ “የተሞሉትን ረቂቅ ዕውቀት” ያንበለብሉት ጀመሩ፣ በዕለቱ ጥር 7 ቀን 2004 ዓ.ም፡፡ “በጋምቤላ የመሬት እጥረት የለም፤ እኛ ለ`ፈረንጆች` የሰጠነው ታርሶ የማያውቀውን መሬት ነው፤ የጋምቤላ ሕዝብ ቁጥሩ ትንሽ ነው” እያሉ ከዚህ” ረቂቅ ዕውቀታቸው” ሊያቋድሱን ሞከሩ፡፡ ለመሆኑ ጋምቤላ የኢትዮጵያውያን መሬት አይደለም እንዴ? ኢትዮጵያውያን የመሬት እጥረት ካለባቸው ክፍላተ ሀገር (እንበል ወላይታ፣ ሰሜን አካባቢዎች፣ ወዘተ) ወደ ጋምቤላ ሄደው ሊያርሱ፣ አይችሉምን? በተመሳሳይ ጋምቤላ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በፈለጉት ክፍላተ ሀገር ተዘዋውረው ሊሠሩና ሊኖሩ አይችሉምን? ሕዝብስ ቁጥሩ በየዓመቱ እየጨመረ መሄዱ ይቀራልን? የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛትስ? ኢህአዴግ በኃይል ሥልጣን ከተቆናጠጠ ወዲህ እንኳን የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት ቢያንስ በ35 ሚሊዮን ጨምሮአል! ለዛውስ፣

ለመሆኑ፣ ኢህአዴግ የመሬት ወረራውን የሚደግፍበት ምክንያቶች ምንድን ናቸው? የምግብ ዋስትና፣ የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ማዳበር፤ የቴክኖሊጂ ሽግግር እና የሥራ ዕድል ማስፋፋት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ እስኪ እነዚህን ምክንያቶች አንድ በአንድ እንመርምራቸው፡፡ የምግብ ዋስትና የምትለዋ ምክንያት “አይናችሁን ጨፍኑ ላሞኛችሁ” ዓይነት ቀልድ ነች! ምክንያቱም፣ ባዕዳኑ በተቀራመቱት መሬት ላይ እያመረቱና ለማምረት ያቀዷቸው ሰብሎች አብዛኛዎቹ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ አሊያም የራሳቸውን ሀገር የውስጥ ፍላጐት ለማሟላት የታሰቡ ናቸው፡፡ እናም በምን ተዓምር ነው ሕንዶች የሚመገቡት ሩዝ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ፍጆታ ሊውል የሚችለው? ይህቺ እንግዲህ የኢህአዴግ የተለመደች “የቁጩ ፖለቲካ” መሆኗ ነው! የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ለማዳበር የተባለውም ምክንያት ውሃ የሚቋጥር መከራከሪያ ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ እርግጥ፣ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት፣ አንድ ወደ ውጭ ሀገር የምርት ውጤት የሚልክ የውጭ ኢንቨስተር፣ የምርቱን ሽያጭ በውጭ ምንዛሪ ለሀገር ውስጥ ባንኮች ገቢ አድርጐ በምንዛሪ የኢትዮጵያ ብር መውሰድ አለበት፡፡ ይሁንና፣ በቢዝነስ እንቅስቃሴው ያገኘውን የተጣራ ትርፍ በውጭ ምንዛሪ ወደ ሀገሩ የመላክ መብት አለው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በኩባንያው ውስጥ የሚሠሩ የውጭ ዜጐች ከደመወዛቸው ውስጥ የፈለጉትን ያህል በውጭ ምንዛሪ ወደ የሀገራቸው መላክ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም፣ ምንም እንኳን አንዳንድ ትላልቅ የካፒታል ዕቃዎችን የውጭ ምንዛሪ ሳያስፈልግ በቀጥታ ከውጭ ማምጣት ቢቻልም፣ እንደ መለዋወጫ፣ ማዳበሪያ፣ ፀረ-ተባይ፣ ወዘተ የመሳሰሉትን ከሀገር ውስጥ ባንኮች በምንዛሪ በሚገኝ የውጭ ገንዘብ ማስመጣት ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም የውጭ ዜጐች በሀገር ውስጥ ገበያ በኢትዮጵያ ብር የሚገዟቸው ከውጭ የሚመጡ ዕቃዎች ስለሚኖሩ፣ በዚህም በኩል የውጭ ምንዛሪ ወጪአችን ይጨምራል፡፡ ስለዚህ ከወጪ ቀሪ የሚገኘው የተጣራ የውጭ ምንዛሪ እስከዚህ ከበሮ የሚያስደልቅ አይሆንም፡፡

ከኪሣራ እና ትርፍ ትንተና (Cost Benefit analysis) አኳያ ሲታይ፣ ከቴክኖሎጂ ሽግግርና ከሥራ ዕድ ል መስፋፋት ጋር የተያያዙት መከራከሪያዎች ሩቅ መንገድ የሚያስኬዱ አይደሉም፡፡ ኢህአዴግ የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚለው ትራክተር መንዳትን ጭምር ነው! በሌላ በኩል፣ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ኢንቨስትመንት ሲደረግ፣ የተወሰነ የሥራ ዕድል መከፈቱ አይቀርም፤ ግን እዚህ ላይ የሚነሣው ዋና ጥያቄ፣ የሀገር ውስጥ ኢንቨስተሮች በቀላሉ ሊሠሩት የሚችሉትን ሥራ ለምን ለባዕዳን እንሠጣለን? የሚለው ነው፡፡ ይህን ጉዳይ በተመለከተ፣ የኢህአዴግ ቱልቱላ የሆነው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን፣ “አላዋቂ ምሁርና ጭፍን ተቃዋሚ” አድርጐ ያቀረባቸው ደሳለኝ ራሕማቶ፣” “The peasant and the state” በሚለው መጽሐፋቸው ውስጥ በዘመነ ኃይለ ሥላሴ እንኳን ከአምስት መቶ አርባ (540) ያላነሱ የዘመናዊ እርሻ ገበሬዎች (ኢንቬስተሮች) እንደነበሩ ገልፀዋል፡፡ ለመሆኑ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ይህንን የአቶ ደሳለኝን መጽሐፍ አይቶት ይሆን? ከእነዚህ የሰፋፊ እርሻ ኢንቨስተሮች መካከል ስመ ጥር ገበሬው ተድላ አበበም ይገኙበታል፡፡ “ተድላ አበበ፤ የዘመናዊ እርሻ ፋና ወጊ” በሚል ርእስ በተፃፉት የሕይወት ታሪካቸው፣ በዚያን ጊዜ በዓመት ወደ አርባ ሺ ኩንታል (40,000 ኩንታል) የሚጠጋ እህል ያመርቱ እንደነበር ተዘግቦአል፡፡ የቅርብ ዘመዶቻቸው እንደሚሉት ከሆነ፣ ተድላ አበበ፣ “እኔ ተድላ፣ ብቻዬን ለአዲስ አበባ ሕዝብ ቀለብ ማቅረብ አያቅተኝም” እያሉ ይፎክሩ ነበር! የደርግ መንግሥት መጥቶ ላባቸውን አንጠፍጥፈው ያፈሩትን ንብረት ሁሉ ባይወርስባቸው ኖሮ፣ ይህን ሕልማቸውን እውን አያደርጉም ነበር ለማለት ያስቸግራል! በደርግ ዘመንም በኢትዮጵያውያን የሚካሄዱ በርካታ ሰፋፊ እርሻዎች ነበሩ፡፡ ይህ ሁሉ የኋላ ታሪካችን የሚያሳየው፣ እኛ ኢትዮጵያውያን ለዘመናዊ እርሻ ሥራ አዲስ አለመሆናችንን ነው፡፡

እኔ በበኩሌ ኢህአዴግን ለሃያ አንድ ዓመታት ያህል በደንብ አጥንቼዋለሁ፡፡ መሠረታዊ አቋሙ ፀረ ኢትዮጵያ ነው፡፡ ለዚህ ማስረጃ ለማቅረብ መሞከር አንባብያንን ማሰልቸት ነው የሚሆነው፡፡ እኛ የምናውቃትን ኢትዮጵያ በካርታም ሆነ በተግባር በታትኗታል፡፡ እኛ የምናውቀው የኢትዮጵያ አንድነት ዛሬ የለም፡፡ ኢህአዴግ ኢትዮጵያን በጐሣ ፖለቲካ ጨርሶ ካልበታተናት፣ ቢበዛ ለመፍጠር እየሞከረ ያለው “የጐሣዎች ማኅበረሰብ” ነው፡፡ ኢትዮጵያ መሸራረፍ ግቡ ያረገ ይመስላል፡፡ እስከዛው በጠመንጃ አፈሙዝ ባገኘው ሥልጣን ተጠቅሞ ሀብቷን እየዘረፈና እያዘረፈ ነው! ኢትዮጵያውያንን እያፈናቀለ፣ ለም መሬታቸውን ለባዕዳን በዶላር እየቸበቸበ ነው፡፡ በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ስርዓት ኢትዮጵያን እንደቀድሞዋ ዚምባብዌ ለባዕዳን እያስረከበ ነው!

በበኩሌ ኢህአዴግን ጥፋተኛ አላደርግም፤ ምክንያቱም ከመጀመሪያውኑ ነፍጥ አንስቶ በረሃ የገባው የውጭ ጠላቶቻችንን ዓላማ ለማስፈፀም ነው፡፡ ጥፋተኞቹ እኛ ኢትዮጵያውያን ነን! እኔንም ጨምሮ ለምንድነው ነው ከጠላት ያላነሰ ወታደራዊ አገዛዝ ለሃያ አንድ ረጅም ዓመታት ዝም ብለን ያየነው? ፍርሃት ከመጠን ያለፈ ራስ ወዳድነት፣ ጐሠኝነት፣ እርስ በእርስ አለመተማመን፣ የዕውቀትና የንቃተ ህሊና ማነስ ለእኛ ነፃነት ሌሎች እንዲሞቱልን መፈለግ በጥቅማጥቅሞች መደለል፣ ኃያላን መንግሥታት የእኛን ችግር እንዲፈቱልን መመኘት፣ ከውጭ ሀገር የሚላከው ከፍተኛ ሐዋላ ያሣደረው ዳተኝነት ወይስ “ከመሞት መሰደድ” የሚለው ፈሊጥ? በእኔ ግምት እነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ዝም ብለን ለመገዛታችን (ለመረገጣችን) መንስዔ ሆነዋል፡፡ ግን ከእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የትኞቹ ናቸው በነጠላም ሆነ በድምር ከፍተኛውን ተፅዕኖ ያደረጉት? እንደሚታወቀው ኢህአዴግ የሚግተን የግፍ ፅዋ ሞልቶ የሚፈሠው በተለይ የኢኮኖሚ ችግሩ ሲባባስ ነው፡፡ ዝምታችንን ትዕግሥታችንን ሊሠብሩ የሚችሉት ረሀብ፣ የውሃ ጥም፣ እና የመጠለያ እጦት ናቸው፡፡ እርግጥ፣ ንቃተኃሊናው ከፍተኛ ደረጃ የደረሰ ሕዝብ ከምግብ፣ ውሃ እና መጠለያ ባሻገር ብዙ ነገሮችን ይመኛል ሲታመም የሕክምና አገልግሎት ይፈልጋል፡፡ በእግሩ ረጅም መንገድ ከመኳተን ዘመናዊ ትራንስፖርት ቢያገኝ አይጠላም፡፡ ትዳር መሥርቶ “ዓይኑን በዓይኑ ማየት” በእጅጉ እንደሚያስደስተው አያጠራጥርም፡፡ ከዚህም አልፎ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቹ ቢከበሩለትና እንደ ከብት ሳይሆን እንደ ሰው ቢታይ ከፍተኛ የመንፈስ እርካታ ያገኛል፡፡

የኢህአዴግን ፋሺስታዊ አገዛዝ እንዴት ለሃያ አንድ ዓመታት ታገሥነው? ይህን ስል በጥቅማጥቅም ሕሊናቸውን የሸጡትን ጥቂት ሰዎች አይመለከትም፤ እኔ የማወራው ስለ ብዙኃኑ ነው፡፡ በእኔ ግምት ሕዝቡ በራሱ ቀስቃሽነት ሆ! ብሎ ተነስቶ መብቱን ለማስከበር ያልቻለው፤ የረሀቡ የመጠለያ እጦቱ፣ የእርዛቱ፣ በአጠቃላይም የኢኮኖሚ ችግሩ ገና ከሚፈለግበት ደረጃ ባለመድረሱ ይመስለኛል፡፡ ለሕዝባዊ ትግሉ እጅግ አስፈላጊ የሆነውን የኢኮኖሚ ችግር የሚያባብስልን ራሱ ኢህአዴግ ነው! ስለዚህ፣ በኢህአዴግ ላይ ዋናውን የጥቃት ዘመቻ እያካሄደ ያለው ራሱ ኢህአዴግ ነው! ለዚህም ልናመሠግነው ይገባናል! የገበያ ዋጋውን የሚያንረው ከአቅም በላይ ታክስ የሚቆልለው፣ ሕዝብን ከቀዬው እና መኖሪያ ቤቱ የሚያፈናቅለው፣ የሚያፈርሰው፤ የመጠጥ ውሃ እጥረት እያለ ሕንፃ የሚገነባው፣ የሕዝብ አንጡራ ንብረት የሆነውን የከተማ ቦታ በሊዝ የሚነጥቀው፣ በሙስና የተጨማለቀው፣ ሀብት እየዘረፈ ከሀገር የሚያሸሸው ወዘተ ራሱ ኢህአዴግ ነውና!

በሌላ በኩል፣ እየተባባሰ የመጣውን የኢኮኖሚ ችግር የሚያረግቡና የሚያለዝቡ ቢያንስ ሁለት ነገሮች አሉ፡፡ አንደኛው ዳያስፖራው (ውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን) የሚልከው ሐዋላ ነው፡፡ ውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በየዓመቱ 3.2 ቢሊዮን ዶላር 56 ቢሊዮን ብር ሀገር ቤት ላሉ ይህም ገንዘብ ከ7-10 ሚሊዮን የሚደርሱ ኢትዮጵያውያንን ይደጉማል፡፡ ሁለተኛው የችግር ማስተንፈሻ ኢህአዴግ በርግዶ የከፈተው የስደት

ኢኮኖሚ

# የኢህአዴግ መንግስት እና የወጣቱ ስራ አጥነት ችግር

በአማኑኤል ዮሴፍ

በእርግጥ የስራ አጥነት ችግር በአሁን ሰአት በአለም አቀፍ ደረጃ ሳይቀር በተለያዩ ምክንያቶች እየጨመረ የመጣ ክስተት ቢሆንም በሁለት ዲጂት እያደገች ነው በምትባለው ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው መልክ እና ተፈጥሮ ግን በተለየ መልኩ እየተጋነነ መጥቷል፡፡ ከተወሰኑ አመታት በዋላ የኢትዮጵያ ህዝብ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ጎራ እንደሚቀላቀል በኢህአዴግ አመራር ቢነገረንም እንደኔ ግምት ግን ደሀ የሚባለውን ስም እንኳን ለወደፊቱ ለመጠቀም እንዳይነፍጉን እፈራለሁ፡፡ እንደ 2006ቱ የአለም ባንክ ጥናት መሰረት ከ40% በላይ የሚሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ የሚኖረው ከድህነት ወለል በታች ነው፡፡ 70% የሚጠጉት ሰራ ያላቸው ወጣቶች ደሞዝ ገቢ በቀን ከ2 የአሜሪካ ዶላር (35 ብር) ያነሰ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ፈጣን የሆነው የሀገራችን ህዝብ እድገት ከስራ አጥነቱ ቁጥር መጨመር ጋር ሲዋሀድ ድህነታችንን ካላባባሰው በቀር ታዲያ እንዴት ወደ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ሊቀላቅለን እንደሚችል አሁንም ግልጽ አይደለም፡፡

አሁን ባለንበት ጊዜ ስራ አጥነት የሚለው ቃል በራሱ ብዙ አተረጓጎም እንዳለው ቢታወቅም ለጊዜው እኔም ወደ ዝርዝር ማብራርያው ባልገባም አንድ እውነት ግን ጠቁሜ ማለፍ እፈልጋለሁ፡፡ እንደ አለም አቀፍ የሰራተኞች ድርጅት ILO አገላለጽ ከሆነ ስራ አጥነት የሚለው ቃል ህጋዊ ከለላ የሌላቸው እና በቂ ያልሆነ ወይም አነስተኛ ደሞዝ የሚከፈላቸውንም ሰራተኞችን ጭምር ያጠቃልላል፡፡ በቂ የሆነ ክፍያ የሚለው መስፈርት አሁንም በራሱ አከራከሪ ነጥብ ቢሆንም ቢያንስ ግን መሰረታዊ የሆነውን የራስን ምግብ ፣ ቤት እና ልብስ የሚሸፍን መሆን እንዳለበት ለመገመት አያስቸግርም፡፡ ከዚህም ሀሳብ ከተነሳን ደግሞ ምናልባትም ቢያንስ ከ90% በላይ የሆነው የኢትዮጵያ ተቀጣሪ ሰራተኛ፣የመንግስት ተቀጣሪውን ጨምሮ፣ስራ የሌለው ነው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም የአብዛኛው ሰው ስራ ገቢ የራሱን ምግብ ፣ ልብስ እና የመጠለያ አቅርቦት በበቂ የማይሸፍን እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ቤት ማለት ቢያንስ ለአደጋ የማያገልጥ ጠንካራና ንጹ ግድግዳ ፣ ጣርያ ፣ በር እና መስኮት ከመጸዳጃ ጋር ያለው ለኑሮ አመቺ የሆነ መጠለያ ሲሆን በውሰጡ ቋሚ የሆኑ መገልገያዎች ማለትም እንደወንበር ፣አልጋ እና ማብሰያ እቃዎች ከመብራት እና የንጹህ ውሀ አቅርቦት ጋር ያለው ማለት ነው፡፡ ምግብ ሲባልም ተመጣጣኝነት ያለው ማለትም አትክልትን፣ፍራፍሬን፣ጥራጥሬን፣የእንስሳ አስተወጽኦ የሆኑትን እንቁላል፣ወተት እና ስጋን ያካተተ እንደሆነ የታወቀ ነው፡፡ እውነቱ ግን ህጋዊ ተቀጣሪ የሚባለው አብዛኛው የሀገራችን ሰራተኛ ቤት እንኳ የሌለው የቤተሰብ ጥገኛ ወይም ቤት ሊባል በማይችል መጠለያ ውስጥ የሚኖር እና በቀን ሶስቴ እንኳን እራሱን ሊመግብ የማይችል መሆኑ ነው፡፡ የእኔም ፍላጎት የአለም አቀፍ አኗኗር ደረጃዎችን መዘርዘር መፈለጌ ሳይሆን በየጊዜው ምን ያህል ከአለም ህዝብ አኗኗር ደረጃ እየራቅን መሄዳችንን ለማሳየት ፈልጌ ነው፡፡ መሰረታዊ ፍላጎትን ገድቦ ካልሆነ በቀር መማር እና ወቅታዊ መረጃዎችን መከታተልማ በአሁን ሰዓት ለአብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ቅንጦት ነው፡፡ አብዛኛው ቋሚ ሰራተኛ ህጋዊ የሆኑ እንደ ጤና ኢንሹራንስ ፣ የትምህርት ድጋፍ እና የስራ አገልግሎት ክፍያን ጥቅም ስለማያገኝ እንደ ILO አገላለጽ አሁንም ሰራተኛ የሚባለውን መስፈርት አያሟላም፡፡

እስቲ አሁን ደግሞ ወደ መሰረታዊ ርእሴ ተመልሼ በአገራችን በፍጥነት እያደገ ስለመጣው የወጣቱ ስራ አጥነት መንስኤዎች እና በቀጣይ ስለሚያስከትለው አደጋ ልጠቁም፡፡ በአሁን ሰአት ኢትየጵያ ውስጥ በተለይም ከ40% በላይ የህዝብ ቁጥር በሚሸፍነው ወጣቱ ሀይል ለይ ከፍተኛ የሆነ ስራ አጥነት ችግር እድገት እየተከሰተ ይገኛል፡፡ ይህ ስራ አጥነት በተለይም የአገሪቷን 83% የህዝብ ብዛትን በሚሸፍነው የገጠሩ ህዝብ ለይ ከፍተኛ የሆነ ሲሆን ከተሞቻችንም በአለም ለይ ከፍተኛ የስራ አጥነት ቁጥር ከሚታይባቸው ከተሞች ዋንኛዎቹ ናቸው፡፡ ከ50% በላይ የሚሆኑት የሀገራችን የከተማ ነዋሪ ወጣቶች ከፍተኛ የሆነ የስራ ማግኛ የመረጃ እጦት ችግር አለባቸው፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ በተለይም በወጣቱ ክፍል በከፍተኛ ፍጥነት እየጨመረ የመጣው ከገጠር ወደ ከተማ ስደትም ከተማዎች ውስጥ ያለውን ችግር እና የስራ አጥነት ቁጥር አባብሶታል፡፡ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ከሆነ በሀገራችን ያለው ህጋዊ መደበኛ የሰራተኛ ቅጥር ( Formal Labor Market) እጅግ አነስተኛ በመሆኑ ሳብያ የአብዛኞቹ ሰራተኞች ከስራ ሰአት በላይ ይሰራሉ፤ድግሞም ጉልበት እና ክህሎታቸው አግባብ ባልሆነ ዝቅተኛ ክፍያ ይበዘበዛል፣ ለዚህ አይነተኛ ችግር መፈጠርም ዋንኛ ምክንያት መንግሥት በቂ የሆነ የማህበራዊ ግኑኝነት (social network) መፍጠር አለመቻሉ ነው፡፡

የወጣቱን ስራ አጥነት ቁጥርን ከጨመሩት ምክንያቶች መሀል አንዱ የወጣቱ ዲሞክራሲያዊ ጥያቄ አለመመለሱ እና እየተዳፈነም መሆኑ ነው፡፡ በግልጽ እንደሚታየው ከሆነ አሁንም የኢትዮጵያ ወጣት ከህግ አውጪነት እና ውሳኔ ሰጪነት ተሳትፎ ሙሉ ለሙሉ የተገለለ ነው፡፡ ስለሆነም አሁንም ወጣቱ ትውልድ በሀገራችን ፖለቲካ ውሳኔ ሰጪነት እርምጃ ውስጥ ድርሻውን "እኔ አውቅልሀለሁ" ለሚለው አንበሳ አሳልፎ ሰጥቷል፡፡ በዚህም የተነሳ የወጣቱ ትውልድ መሰረታዊ ችግር እንዳይታወቅ እና እዲሸፋፈን ተደርጓል፡፡ ከምርጫ 97 ክስተት በዋላ ከስተቱ እንደሚታረም እና ለወጣቱ ከፍተኛ ትኩረት እንደሚሰጥ የተናገረው ኢህአዴግ የአስተሳሰብ ችግሩን አፍርሶ እስከአሁንም ወጣቱን በሀገሩ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ አልቻለም፡፡ እንዳውም ይሄ የሀገር ዘብ እና አምራች ሀይል የመንገድን ያህል በመንግስት ትኩረት የተሰጠው አይመስለኝም፡፡ ይልቁንም ኢህአዴግ የወጣቱን እና የእናቶችን የኑሮ ችግር በመረዳቱ አነስተኛ የሆነ የአባልነት አገልግሎት ድጎማ በመስጠት እምነትቸውን በርሱ ላይ ብቻ እንዲያደርጉ በማድረግ የፖከቲካ ስልጣን ማግኛ ማስፈጸምያ መሳርያ ካላደረጋቸው በቀር አሁንም የወጣቱን ትውልድ ጥያቄ አልመለሰም፡፡

በአሁኑ ሰአት እጅግ ብዙ የተማሩ ወጣቶች ያለስራ ቤታቸው ተቀምጠው እንደሚገኙ ይታወቃል፡፡ የዚህ ችግር መፈጠር ዋነኛ ምክንያት የወቅቱን ገበያ ያላገናዘበው የመንግስት ትምህርት ፖሊሲ ሲሆን መንግስትም ይህን ችግር ለመፍታት የወሰደው እርምጃ አለ ለማለት እቸገራለሁ፡፡ ወጣቶቹም ምንም እንኳ ስለተማሩት ትምህርት እና የሙያ ስልጠና እውቀቱ ቢኖራቸውም ምንም አይነት የስራ ልምድም ሆነ የክህሎት ማሳያ ቦታዎች ስለሌሉ የሙያ መህበራቱም ከስራ ይልቅ በተራ ፖለቲካዊ አፈጻጸም ለይ የተተበተቡ ለመሆኑ ስራ እንዴት ማግኘት እና መፍጠር እንደሚችሉ እንኳ መረጃ የላቸውም፡፡ ሀገር ውስጥ ያሉት ዩንቨርሲቲዎችም ሆነ የቴክኒክ እና ሙያ ማሰልጠኛ ማዕከሎች አስተምሩ የተባሉትን ትምህርት ከማስተማር በቀር ተማሪዎቹ ተመርቀው ሲወጡ በቀጣይ ለሀገር የሚሰጡት ተያያዥነት ያለው ፋይዳ የሚያስሰባቸው አይመስሉም፡፡ ስለዚህ እነዚህ ተቋማት እየሰሩት ያለው ስራ "የትም ፍጪው" ዱቄቱን አምጪው መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ኢህአዲግም ደግሞ እንደ ቁጥር ሪፖርት (quantitative report) ውጤት የሚያስደስተው ነገር ስለሌለ ብቃት ፣ ጥራት ፣ ክህሎት የሚባሉትን ውጤቶች እና መስፈርቶችን ለሪፖርት ዝግጅት አይጠቅማቸውም፡፡ ቢወዳቸው ኖሮ ግን ይሄ ሁሉ ወጣት ትምህርት ተምሮ እና ሙያን ሰልጥኖ እንዴት ገና በዚህች ምንም ባልተሰራባት ሀገር ስራ ሊያጣ ይችላል የሚለው ነገር ፍንትው ብሎ ይታየው ነበር፡፡ ግን ምን ዋጋ አለው በአመቱ መጨረሻ የምንሰማው ይህን ያህል ተማሪ አስመርቀናል የሚል ተያያዥነት የሌለው ነጠላ ሪፖርት ነው፡፡ የባለፈው አመት ተመራቂ ተማሪዎች ከምን ደረጃ ደረሱ የሚል ጠያቂ ቢኖር መልስ እንደሌለ ግልጽ ነው፡፡

ሌላው ቀርቶ ከሀገሪቷ ተጨባጭ የገበያ ሁኔታ ጋር ተያይዘው በዩንቨርስቲ እና በሙያ ማሰልጠኛ መአከላት ደረጃ መንግስት ነደፍኳቸው የሚላቸው የትምህርት መስኮች ጥናት ጥልቀት የሌላቸው እና ስሜት የፈጠራቸው ግኝት መሆኑን ለማስረዳት በተጨባጭ ከተመዘገበው እጅግ አነስተኛ ውጤት በላይ ምስክር የለም፡፡ ይህንን እውነትም በምሳሌ ለማስረዳት በሀገራችን ከአበባ ምርት ገበያ መስፋፋት ጋር ተያይዞ በጥናት ለይ ተመስርቶ ተቋቋመ የሚባለውን የሆርቲካልቸር (horticulture) የዲግሪ ትምህርት ፕሮግራም ማየት ብቻ በቂ ነው፡፡ የአበባ ማምረቻ እርሻዎች በስፋት በመስፋፋታቸው ገበያ በጣም አለው ተብለው በዚህ የትምህርት መስክ የተመረቁት ተማሪዎች አብዛኞቹ ስራ ያጡ ናቸው፡፡ ስራ ያዙ የሚባሉትም ምርቱን ከሀገር አውጥተው በዶላር ከሚሸጡት የውጭ ኢንቨስተሮች የሚቀበሉት ደሞዝ እጅግ አሳዛኝ እና አሳፋሪ ነው፡፡ በእርግጥ ሙያዊ/professional) የሚባሉት የነዚህ ወጣቶች ክፍያ ብቻ አይደለም አሳዛኙ፤በነዚህ አበባ እርሻዎች በቀን ሰራተኝነት የተቀጠሩት ወገኖቻችን ጭምር እንጂ፡፡ ነገሩን ይበልጥ አሳዛኝ የሚያደርገው ደግሞ፣ለነዚህ ዜጎች የሚከፈላቸው አነስተኛ ክፍያ እና የጉልበት ብዝበዛ በግልጽ እያየ የብዙ ዜጎች ህይወት በዚህ ዘርፍ ተጠቃሚነት ተቀይሯል እያለ በቴሌቭዥን መስኮት ሳይቀር መለፈፉ ነው፡፡ አንዳንዴ እንዲህ አይነት ጭፍን የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች በማይበት ጊዜ የዚህ መንግስት ተጠሪነት ለማን እንደሆነ ግራ ይገባኛል እውነት መንግስትን የሚያስደስተው የውጭ ባለሀብቶቹ ትረፋማነት ነው ወይስ የዜጎች ተጠቃሚነት የሚለው ጉዳይ በአእምሮዬ ይመላለሳል፡፡ ጥያቄው ድምዳሜአችንን ወዴት እንደሚወስደው የታወቀ ነው፡፡ ነገሩ ብዙ እናውቃለን፡፡ ብንናገር እናልቃለን ሆኖብን እንጂ፡፡ በራሱ ምድር ለይ የሚኖር አንድ ዜጋ መቼም በሌላ ሀገር ዜጋ አማካኝነት ዝቅተኛ ክፍያ ከተከፈለው በራሱ ሀገር ባይተዋር ሆኗል ማለት ነው፡፡ ምናልባትም ይህ ችግር ከተዘዋዋሪ ቀኝ ግዛት (Indirect colonialism) ሳይቀር የማይለይበት ሁኔታ ነው፡፡

የወጣቱ ስራ አጥነት ችግርን ያባባሰው ሌላው እውነት ደግሞ በግልጽ እየታየ የመጣው ተመጣጣኝነት የሌለው የሀገራችን ህዝብ ኢኮኖሚ እድገት ነው፡፡ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ታደጊ ሀገራት በእድገታቸው ውስጥ ማከናወን ካለባቸው ወሳኝ የእድገት ማረጋገጫዎች አንዱ እና ዋናው መሀከለኛ ገቢ (Middle income) ያለውን ህዝብ በብዛት መፍጠር ነው፡፡ ምክንያቱም መካከለኛ ገቢ ያለው ህዝብ በአንድ ሀገር ውስጥ በብዛት አለ ማለት አብዛኛው ህዝብ በቂ የሆነ የስራ ገቢ እና ነጻነት አለው ማለት ነው፡፡ በህዝቡ መካከል ያለው የኢኮኖሚ እድገት ስርጭት እየሰፋ መጥቶ ጥቂት ሀብታሞች እና ብዙ ደሃዎች ከተፈጠሩ ግን በሀገሪቱ ውስጥ ብዙ ስራ እጦች ብቻ ሳይሆን ብዙ ርሀብተኞች እና ጭቁን ዜጎች ጭምር እንደሚፈጠሩ ማሳያ ይሆናል፡፡ ጭቆና ካለ ደግሞ ህዝብ በነጻነት ተንቀሳቅሶ እና ተደራጅቶ እንዳይሰራ እና እውቀቱን እንዳይጠቀም ተደርጓል ወይም ተገዷል ማለት ነው፡፡ አሁን በሀገራችን እየታየ ያለውም እውነት ይህ ነው፡፡ በአሁኑ ሰአት ኢትዮጵያ የትንሽ ሀብታም እና የብዙ ደሀ ህዝብ መኖሪያ ሀገር እየሆነች ነው፡፡ የሀገሪቷ ትልልቅ የንግድ ድርጅቶች እና ፋብሪካዎች ባለቤቶች ለራሳቸው የተሻለ ነጻነት የሰጡ እና ዜጎችን የጨቆኑ ናቸው፡፡ ስራ ለማግኘትም ሆነ ስራን ተደራጅቶ እና በነጻነት ተንቀሳቅሶ ለመስራት ገዢውን ፓርቲ መደገፍ እና አካሄዱን ያለምንም ተቃውሞ መቀበል ያስፈልጋል፡፡ ይህ አካሄድ ደግሞ የአስተሳሰብን ነጻነት የሚጋፋ እና የሰብአዊ መብት መከበርን የሚጥስ አካሄድ ከመሆኑም በላይ ገዢው ፓርቲ ምን ያህል የዲሞክራሲ አስተሳሰብ ችግር እንዳለበት በግልጽ የሚያመለክት ነው፡፡

ወቅታዊውን የሀገራችንን ወጣት የስራ አጥነት ችግር በአጠቃላይ መልኩ ስናየው የኢህአዲግ ፖሊሲ ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር ምን ያህል ክፍተት እንዳለው ያሳየናል፡፡ ሥራ የሌላቸውን እንኳ ብንተው ባለ ስራ ናቸው የተባሉት አብዛኛዎቹ ወጣቶች የተሰማሩበት ዘርፍ ሲገመገም አብዛኛው የሚሰሩት ለወደፊቱ ህይወታቸው መሻሻል ምንም አስተዋጽኦ የሌላው፣ ዝቅተኛ ክፍያ ያለው፣ ለተሻለ ስራ የማሰብያ ጊዜ የማይሰጣቸው እና የሥራ ተነሳሽነትና የመሻሻል ስሜታቸውን የሚገድል ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ለምሣሌ የቀን ስራ፣የመኪና መጠበቅ፣የሊስትሮ እና ልብስ አጣቢነት፣ የቤት ሰራተኝነት፣ እንጀራና ዳቦ ጋጋሪነት፣ አስተናጋጅነት፣ በጥበቃ ሙያ... ወዘተ ምሳሌ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ብዙ ሊባሉ የሚችሉ ስራ ያጡ ወጣቶች ደግሞ ጊዜአቸውን በሱሰኝነት በማሰለፍ ወገንን ጎጂ ለሆኑ የሌብነት እና ሴተኛ አዳሪነት ስራ ይዳረጋሉ በዚህም አምራች የሆነው ዜጋ እራሱን በአላስፈላጊ የሱስ ፀቦች እና ተላላፊ በሽታዎች ከመግደሉም በላይ የአካባቢውን ሰላም አደጋ ውስጥ እንዲወድቅ ያደርገዋል፡፡ ሀቁን ለመረዳት ደግሞ ድሮ እጅግ በቁጥር አነስተኛ የነበሩትን በአሁኑ ሰአት ግን በየአካባቢያችን በብዛት የሚገኙትን ጫት ቤቶች እና እህቶቻችን ገላን ከመጠጥ ጋር የሚቸበቸብባቸው መሸታ ቤቶች ትኩረት ሰጥቶ መመልከት ነው፡፡ አሁን አሁንማ የለማኙ ቁጥር ከተለማኙ ቁጥር እኩል ሊሆን ትንሽ የቀረው ይመስላል፡፡ የጎዳና ህይወት የሚኖሩ ህጻናት እና ወጣቶች ቁጥር የሚጨምር እንጂ የሚቀንስ አይመስልም፡፡ ለልመናውም ሆነ ለጎዳና ህይወቱ መፈጠር ግን ዋና መሰረቱ ስራ ማጣት ነው፡፡ ስለዚህ የወጣቱ ስራ ማጣት ልክ እንደ አክሱም ሀውልት መመለስ ትኩረት ተሰጥቶት ካልተፈታ ብዙም ሳይቆይ በቀጣይ ጥቂት ዓመታት ይህች ሀገር ምን ልትመስል እንደምትችል መገመት አያስቸግርም፡፡

---

በር ነው፡፡ በየዓመቱ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በገዛ ፈቃዳቸው ሀገራቸውን ጥለው በአራቱም ማዕዘናት ወደ ባዕድ ሀገሮች ይሰደዳሉ፡፡ እንግዲህ፣ ኢህአዴግ የራሱን የሥልጣን ዕድሜ የሚያሣጥር ሥራ ሲሰራልን እኛ ግን ዕድሜውን የሚያራዝም ተግባር እየፈፀምን ነው፡፡ ሀገር ጥሎ ከመሰደድ ይልቅ፣ እዚሁ ሆነን መታገል ነበረብን፡፡ ለመሠረታዊ ፍላጐቶች ከሚያስፈልገው በላይ ከውጭ የሚላከው ሐዋላ ለኢህአዴግ ትልቅ ሲሳይ ከመሆኑም በተጨማሪ አያሌ ወጣቶችን ከትግል እያገለለ ነው! ውጭ ሀገር ያሉ ዘመዶቻቸው በሚልኩላቸው ገንዘብ አንዳንዶቹ ጫት እየቃሙ ድራፍት ቢራ የሚገፉ ወጣቶች እንዴት በሕዝባዊ ትግሉ ሊሳተፉ ይችላሉ?

በመጨረሻም፣ ኢህአዴግ መሬታችንን ለባዕዳን መቸብቸቡ የሕዝቡን ብሶት ስለሚጨምረው ለሕዝባዊ ትግሉ መጠናከር በጣም ጠቃሚ ነው! ሕዝቡ በአንድነት ሆ! ብሎ ኢህአዴግን ከሥልጣን ሊያባርረው የሚችለው ኢህአዴግ የሚፈፅምበትን ግፍ መሸከም ሲያቅተው ብቻ ነው! ያን ጊዜ የሚመጣበትን ዕለት ለማፋጠን በተለይ የኢኮኖሚ ችግሩን የሚያረግቡትንና የሚያለዝቡትን ነገሮች (ከላይ የተጠቀሱትን) መቀነስ ይኖርብናል፡፡ በበኩሌ፣ የመሬት ወረራውንና ቅርምቱን በመደገፍ ለተሠራው የፕሮፓጋንዳ ዘጋቢ ፊልም የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንን አመሰግናለሁ! እውነተኛ የሕዝብ ብሶት የሚወልዳትን ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ለማየት እግዚአብሔር ያብቃን!

# የኢ.ህአዴግ እድሜ ማሳጠሪያዎች



በበለጠ ጉሹ ወ/ሚካኤል

"አስተውሎ የሚራመድ ብዙ መንገድ ይጓዛል፡፡"

የሕዝብን ዝምታ ከፍርሃት መቁጠር ተላላነት ነው፡፡ ኢህአዴግ የኢትዮጵያን ሕዝብ ዝምታ ሊፈራው ይገባል፡፡ ሕዝቡ በተፈጥሮው ቻይ፣ በባህርይው ታጋሽ በሕልውናውም ከመጡበት እንደ አራስ ነብር ቁጡ ነው፡፡ ይህንን ሕዝብ ፍቅር ሰጥቶ መብቱን መጠበቅ፣ ማስተዳደርና ማስተዋልን ይጠይቃል፡፡ ባለፉት መንግሥታት የተፈጠሩ የታሪክ ስህተቶችን ላለመድገም ከታሪክ መማር ብልህነት ነው፡፡ ለገዢዎቻችንም ደጋግመን የምንወተውተው ይህንን ነው፡፡ የህዝብን ድምፅ ሰሙ፣ ብሶቱን ተባሱ፣ ቀርባችሁ ችግሩን ተረዱ ነው የዘወትር ጩኸታችን፡፡ ሕዝብን በመናቅ የራስን አገዛዝ ዘመን ለማራዘም የሚደረገው ሩጫ ውሎ አድሮ መሪዎችን የከፋ አደጋ ላይ እንደሚጥልና አገርንም እንደሚጎዳ ከግብፅና ከሊቢያ ክስተቶች ልንማር ይገባል፡፡

አንድ በሥልጣን ላይ ያለ መንግሥት በህዝብ ዘንድ እንዳይጠላ ካልተጠነቀቀ "መካሪ የሌለው ንጉስ . . ." እንዲሉ እድሜው ያጥራል፡፡ የህዝብን የልብ ትርታ በማዳመጥ የሚጠላውን የአገዛዝ አካሄድ ማሻሻል ተገቢነቱ አያጠራጥርም፡፡ በተለይም ከምርጫ 97 በኋላ ኢህአዴግ በህዝብ ጫንቃ ላይ የሚያሳርፈው ጫና ከአመት አመት እየከበደ መጥቷል፡፡ ቅድመ 97 ምርጫ በነበሩት የኢህአዴግ አገዛዝ አመታት ሕዝቡ በደሉን በውስጡ አምቆ፣ ስሜቱን በምርጫ ካርድ (በድምፁ) ብቻ መግለፁ ለገዢዎቻችን የማንቂያ ደወል ይመስለኛል፡፡ በዚያን ዓመት ነበር ኢህአዴግ ያበቃለት፤ በአገራችን እውነተኛ ዴሞክራሲ የሰፈነ ቢሆን ኖሮ ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር ሲደረግ ለማየት የታደልን የ21ኛው ክ/ዘመን ኢትዮጵያዊ ትውልድ እንሆን ነበር፡፡ የኢህአዴግ መሪዎችም ስማቸውና ግብራቸው ከመቃብር በላይ ሲዘከር ይኖር ነበር፡፡ ግና አልሆነም፡፡ "የሕይወት መስዋዕትነትን ከፍለን ያገኘነውን ሥልጣን በብጣሽ የምርጫ ወረቀት አንሰጥም" በሚል አምባገነን አስተሳሰብ የህዝብ ድምፅ በአደባባይ ተሻረ፡፡

"ከፉ ጎረቤት እቃ ያስገዛል" እንዲሉ በምርጫ 97 ሕዝቡ በቅንጅት ማኒፌስቶና የምርጫ ቅስቀሳ ለምን እንደተማረከ መማር ለኢህአዴግ ይጠቅመው ነበር፡፡ የራሱንም ጓዳ እየፈተሸ ያሉበትን ችግሮች ግን መንቀስ አልቻለም፡፡ ዛሬም ከህዝብ ጋር የሚያቃቅረውን ፖሊሲ እየነደፈና የዴሞክራሲን ጭላንጭል በፅልመት እየጋረደ ራሱን ለአውራ ፓርቲነት ማብቃቱ "የውሃ ጠብታ አለትን ትሰረስራለች" እንዲሉ የኋላ ኋላ እየጨመረ የመጣውን የሕዝብ ብሶት ለመመለስ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

እድሜ ማሳጠሪያ አንድ

- የምርጫ ዋዜማ ቃልኪዳኖች

በልጅነታችን የአበሻ ኮሶ ተበጥብጦ እንድንጠጣ ሲደረግ "ዶሮ ማታ ሽሮም የለ" እየተባልን እንባበል እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡ ያንን መራራ ኮሶ ስንጨልጥ የሚታየን የሚታረድልን ዶሮ ብቻ ነው፡፡ አይ ልጅነት! ልጅነት እኮ መልካም ነው፡፡ ምሽት ላይ ሲያሽረን ግን ገንፎ ነገር ትሰራና በቅቤ እየነከርን እንድንበላ ይደረጋል፡፡

ምርጫ ሲደርስ ኢህአዴግ እንደ እድር ነጋሪ በየሰፈሩ በሚያሰማራቸው ካድሬዎቹ (ዘመናዊ ቆራሌዎች) አማካኝነት ሕዝብን በአንቀልባ ለማዘል ይዳዳዋል፡፡ የጨረቃ ቤት የሚል ስያሜ የተሰጣቸው ሕገወጥ ግንባታዎች ሕጋዊ እንደሚሆኑና እንደሚፀድቁ ይለፍፋል፡፡ ወጣቶችና ሴቶች በጥቃቅን አነስተኛ ተደራጅተው እንዲንቀሳቀሱ ጥሪ ይደረጋል፡፡ በየመስሪያ ቤቱ ህዝብ ለአቤቱታ ከመጣ ጉብ (ቂጥጥ) እየተባለ ይስተናገዳል፡፡ ብቻ ምኑ ቅጡ! ይሄ ሁሉ መራጩ ህዝብ ካርዱን እንዳይነፍገው ለመሸነጋገል ነው፡፡ የዶሮ ማታው አይነት የኮሶ ማጠጫ የማይተገበር ቃል ኪዳን፡፡

ምርጫው እንዳለፈ አፍንጫችሁ ላሱ ይላል፤ ከዚህ በኋላ፡፡ ካቢኔዎቹ አካፋና ዲጂኖ ያነገቡ ወዛደሮችን ከኋላ አስከትለው ሕዝቡ በችግር እየተጠበሰ የቀለሳትን ጎጆ በጠራራ ፀሐይ ይንዷታል፡፡ ያደራጃቸው ማህበራት በችግር ሲቆላለፉ እያየ ፊቱን ያዞራል፡፡ በየመስሪያ ቤቱ የሚስተዋለው ቢሮክራሲ ጭራሽ ብሶበት ሕዝብ ሲጉላላና ሲያጉረመርም ይታያል፡፡ ይህን ጊዜ ሕዝብ ቂም ያረግዛል፣ ጥርሱን ይነክሳል፡፡ "አይነጋ መስሏት . . ." እያለ ይዝታል፤ በቀጣዩ ምርጫ ካርድ በመንፈግ ሊበቀለው አያስብም ማለት የዋህነት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ዴሞክራሲ ባልሰፈነባቸው እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገራት ተቀናቃኞች በምርጫ አሸንፈው ስልጣን ለመያዝ ሲበቁ ማየት የሕልም እንጀራ እየሆነብን መጥቷል፡፡ ተስፋችንም እየጨለመ ነው፡፡ ሕዝቡ ግን ቂም እንዳረገዘና እህህ እንዳለ ማዝገሙ የኢህአዴግን ተጠይነት እያጎነው መጥቷል፡፡

ዕድሜ ማሳጠሪያ ሁለት

የመልካም አስተዳደር እጦትና ሙስና እድሜ ማሳጠሪያዎች ናቸው፡፡ በአንድ የመንግስት አስተዳደር ውስጥ የመልካም አስተዳደር መስፈን ለገዢው አካል ዋስትናን ይሰጣል፡፡ ሕዝብ ባግባቡ የሚያስተዳድሩት፣ ቀርበው ለጥያቄው ምላሽ የሚሰጡት፣ ዝቅ ብለው የሚያገለግሉት አስተዳዳሪዎች በየደረጃው ሲሾሙለት አሜን ብሎ በፍቅር ይገዛል፡፡ ኢህአዴግ ግን በዚህ ረገድ እጅግ የገዘፈ ችግር አለበት፡፡ ሹመኞቹ በብቃት ማነስ የእውር ድንብራቸውን ሲጓዙ እና በየቀኑ በሚደረጉ አሰልቺና ፀያፍ ግምገማዎች ካድሬዎቹ ከስልጣን ሲወርዱና ሲወጡ ማየት የዘመነ ኢህአዴግ ተውኔት ነው፡፡ ችግሩ ደግሞ ከታችኛው እስከላይኛው መዋቅር ድረስ የሚታይ ነው፡፡

አሁን በቅርቡ እንኳን በአቅም ማነስ ችግር በሚል ማሳበቢያ የንግድ ሚኒስቴር ሚኒስትሩና ሚ/ር ዴኤታው አንድ አመት እንኳን ሳያገለግሉ መነሳታቸው አሳፋሪ ነው፡፡ ታህሣሥ 24/2004 በተካሄደው የጋምቤላ ክልል ካቢኔዎች ግምገማ ላይ ለረጅም አመት ስልጣን ላይ የቆዩ ሹመኞች በአቅም ማነስ እና በመልካም አስተዳደር ችግር ከቦታቸው እንዲነሱ ተደርጓል፡፡ ገዢው ፓርቲ በየደረጃው የሚያስቀምጣቸው የሕዝብ አስተዳዳሪዎች ነጋ ጠባ ህዝብን ለምሬት የሚዳረጉት ከሆነ ኢህአዴግ ዕድሜው እንደሚያጥር ሊገነዘብ ይገባል፡፡

በሌላ በኩል የመልካም አስተዳደር ችግር ለሙስና በር የሚከፍት ይሆናል፡፡ በጥቅማ ጥቅም እየተደለሉ ፍትህን ማዛባት የከፋ አደጋ ያስከትላል፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ በቀን አንድ ጊዜ ለመመገብ በተቸገረበት በአሁኑ ሰዓት ጥቂት የኢህአዴግ ሹመኞች ከቀበሌ እስከ ፌዴራል ድረስ የአገርን ሀብት እየተቀራመቱ ኑሮአቸውን ሲያደላድሉ ማየት እንደ ባህል እየተቆጠረ መጥቷል፡፡ ኢህአዴግም ሚስጥሩን አፍኖ እንጂ ሙስና ከቁጥጥሩ በላይ ሆኖበታል፡፡ በቅርብ ጊዜ ውስጥ በአለም አቀፍ ደረጃ የወጡ መረጃዎች እንዳመላከቱት በየጊዜው በባለሥልጣናትና በኢንቬስተሮች መካከል በሚሰሩ የረቀቁ ወንጀሎች እስከ 11.7 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ከአገር መውጣቱ ተዘግቧል፡፡ ይህ አስደንጋጭ አሀዝ ከመገታት ይልቅ በየአመቱ እየጨመረ መምጣቱ ሁኔታውን ውስብስብ አድርጎታል፡፡

ከዘመኑ ሹመኞች (ከቀበሌ እስከ ሚ/ር ማዕረግ ከተሾሙት) በሙስና ያልተነካካን ሰው ማግኘት እጅግ አስቸጋሪ ነው፡፡ ኢህአዴግም ሹመኞችን በሙስና ሰበብ በህግ ፊት የሚያቀርበው ግለሰቦቹ ፖለቲካዊ ችግር የሚፈጥሩ ከሆነ ብቻ ነው፡፡ ይሄ ደግሞ የገዢው መደብ በተለይም የአቶ መለስ ክፉ አመል እንደሆነ ከአቶ ታምራት፣ ከአቶ ስዬ አብርሃ የግፍ ውንጀላ መገንዘብ የሚቻል ይመስለኛል፡፡ ትናንት በየአካባቢው የሚያውቀው የኢህአዴግ ሹመኛ ከብርሃን ፍጥነት በመጠቀ ሁኔታ ባለ ትላልቅ ፎቆችና ባለ ዘመናዊ መኪና ባለቤት ሲሆን ሲያየው "ምን ሠርቶ አገኘ?" የሚለውን ጥያቄ እያነሳ ይገኛል፡፡ እውነት ለመናገር በስመ ታጋይና ተጋዳላይ ጥቂት የትግራይ ተወላጆች እና ጀሌዎቻቸው ቁንጮ ኢንቬስተሮች መሆናቸው አነጋጋሪ ከሆነ ውሎ አድሯል፡፡ የህዝቡን አንጡራ ሀብት በመዝረፍ ባፍንጫቸው ቅቤ እየጠጡ የሚንደላቀቁ ሹማምንት ቅጥ ያጣ ኑሮ ሲኖሩ የሚያየው ኢትዮጵያዊ ዜጋ ነኝ ለማለት አይደፍርም፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያዊ ለመሆን የሥርዓቱን የነቀዘና በሙስና የበከተ አካሄድ ለመታገል ግድ ይላልና፡፡ ሕዝቡ ተቃውሞውን በአደባባይ ማሰማቱ አይቀርም፡፡

ዕድሜ ማሳጠሪያ ሦስት

- የኑሮ ውድነት

ይሄኛው አደገኛና ቅፅበታዊ የእድሜ ማሳጠሪያ ነው፡፡ ዛሬ የሚታየው የኑሮ ውድነት በተለይም የምግብ እህል ዋጋ በፍጥነት ማሻቀብ ክስተቱ ዓለም አቀፋዊ (universal) ቢሆንም የእኛ ግን እጅግ የከፋ ነው፡፡ የዶላር ምንዛሪው በየእለቱ ሽርፍራፊ ሳንቲሞችን እየጨመረ በመሄዱ የዕቃዎች ዋጋም በየቀኑ እየናረ ሲሄድ ይስተዋላል፡፡ የውጭ ምንዛሪን ለማግኘት ሲባል የሀገር ውስጥ ፍጆታን ግምት ውስጥ ባላስገባ መልኩ እያንዳንዷ የአገር ውስጥ ምርት ገበያ እየተፈለገላትና እየተለቀመች መላኳ የሕዝቡን ጦም አዳሪነት እያባባሰው ይገኛል፡፡ በምጣኔ ሀብት ባለሞያዎች ቋንቋ ብዙ ብር ጥቂት ምርትን ማሳደዱ ኢትዮጵያ ለድሆች መኖሪያ ሥፍራ እንደሌላት የሚያሳውቅ ይመስላል፡፡ ምናልባት ኢህአዴግ ድህነትን ለማጥፋት ድሀን ማጥፋት የሚል እኩይ ሚስጥራዊ ተልዕኮ ያነገበ ከሆነም አካሄዱ ዕድሜውን የሚያሳጥረው ነው፡፡

አሁን ባለው የገበያ ሁኔታ ደመወዝተኛው የወር ገቢውን በጅቶ ለመኖር አልቻለም፡፡ ደመወዙም እስከ ወር አጋማሽ አያደርሰውም፡፡ የሀገራችን የኑሮ ውድነት ወዴት እያመራ እንደሆነ ለአፍታ ቆም ብሎ ማስተዋል ገዢውን ፓርቲ ግድ ሊለው ይገባል፡፡ በኑሮ ውድነቱ ላይ ከህዝብ ጋር ተቀራርቦ መወያየትም አስፈላጊ ይመስለኛል፡፡ ህዝቡ በረሀብ አለንጋ እየተገረፈና በቀን አንድ ጊዜ ለመመገብ እንኳን እየተሳነው ባለበት ተጨባጭ ሁኔታ በቴሌቪዥን መስኮት ነጋ ጠባ "አድገናል፤ ተመንድገናል፤ ካደጉት አገሮች ተርታ ልንሰለፍ ተቃርበናል፤ ድህነት ታሪክ ሊሆን ነው" እያሉ መለፈፍ ኢህአዴግን አያዋጣውም፡፡

ከምርጫ 97 በኋላ በሚያስገርም ፍጥነት እየጨመረ የመጣው የኑሮ ውድነት ያሳሰበው ኢህአዴግ በ2003 ዓ.ም ገበያን አረጋጋለሁ በሚል በስሜት ተነሳስቶ የወሰደው እርምጃ ችግሩን አባባሰው እንጂ ለድሀው የፈየደው አንዳች ነገር የለም፡፡ ሹማምነቱ ግን በቀበሌ ይከፋፈሉ በነበሩ የዘይትና የስኳር ምርቶች ኪሳቸውን አደለቡበት፡፡ ዛሬ የመጨረሻው ድሃ ኢትዮጵያዊ ምግብ የሆነችው ሽሮ እንኳን (ጥሬው እህል) አንዱ ኪሎ 28 ብር ገብታለች፡፡ ከዚህ በላይ የኑሮ ውድነት አለ እንዴ? "ሽሮን ሲያታልሏት ጥሮቲን ነሽ አሏት" የሚሏትን ሽሮ ለመመገብ ብርቱ ፈተና ሆኗል፡፡

እስቲ ለአንድ አፍታ ከ97 ዓ.ም በፊት የነበረውን የሥጋ ዋጋ እናነፃፅር፡፡ ኢህአዴግ ራሱን ከኃይለ ሥላሴና ከደርግ መንግስታት ጋር ያነፃፅር የለም እንዴ፡፡ በዚያን ወቅት (ከ97 ዓመት በፊት) በአዲስ አበባ ከተማ ኮተቤና ካራ አካባቢ አንድ ኪሎ ሥጋ ከ7 እስከ 10 ብር ይሸጥ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ዛሬስ? ዛሬማ አንድ ኪሎ የሽሮ እህል እንኳን 28 ብር ገብቷል፡፡ ሥጋንማ የትኛው ኢትዮጵያዊ ሊበላው? የጊዜው ሹመኞች ካልሆኑ በቀር፡፡

ዕድሜ ማሳጠሪያ አራት

- ሥራ አጥነት

ዛሬ የምዕራቡን አለም ዜጎች ጭምር በየአገራቸው ለአደባባይ አመፅ የጋበዘ አንገብጋቢ ችግር ነው፡፡ የሁሉም ነገር ምሳሌ አድርገን የምንጠቅሳቸው ያደጉት አገሮች በተለይም አሜሪካና እንግሊዝን የመሣሠሉትንም የሥራ አጥነቱ ችግር መፈናፈኛ አሳጥቷቸዋል፡፡ በየጊዜው አደባባይ እየወጡ በሚያካሂዱት ሰላማዊ ሠልፍ መሪዎቻቸውን ሲወርፉና አልፈው ተርፈው ሕንፃዎችንና ተሽከርካሪዎችን ሲያወድሙ እያየን ነው፡፡ መሪዎቹም ቢሆኑ ከዲሞክራሲያዊ አካሄዳቸው አንፃር የህዝቡን የገነፈለ ብሶት ማፈን አይችሉም፡፡

ዛሬ የሚታየው የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የነገ ፈታኝነቱ ከቶም አያጠራጥርም፡፡ አለም አቀፍ መረጃዎች እንደሚያመላክቱት የህዝባችን ቁጥር እጅግ በሚያስደነግጥ ፍጥነት እየጨመረ መጥቷል፡፡ የተማረው የሰው ሀይል ቁጥርም በዚሁ መጠን በእጅጉ ጨምሯል፤ ይጨምራልም፡፡ መንግሥታችን በውጭ እርዳታና ብድር ላይ በተመረኮዘ የሚገነባቸውን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ብዛት እያደነቀና የቅበላ አቅማቸውም ከ100 ፐርሰንት በላይ መጨመሩን ያወጋል፡፡ ጥሩ ነው፡፡ ግን እነዚህ ተማሪዎች የነገ ምሩቃን መሆናቸው ግድ ነውና በየትኛው የሥራ መስክ ይሰማራሉ? ከትምህርት ተቋማቱ ግንባታ ጐን ምን የተመቻቸ የሥራ እድል ተፈጥሯል? በሌላ በኩል የገጠሩ ነዋሪ ወጣት ወደ ከተማዎች እየፈለሰ ሥራ ፍለጋ ሲንከራተት ሲታይ መጨረሻው ወዴት ሊያመራ እንደሚችል ከወዲሁ ለመገመት አያዳግትም፡፡ ወደ አረብ አገራት በሞምባሳ፣ በጅቡቲ በሱዳን፣ በሞያሌ ወዘተ እየኮበለሉ የሚወጡ ወጣቶች በአገራችን ሥር የሰደደው የሥራ አጥነት ችግር የፈጠረው ነው፡፡ ዓለም አቀፍ ሰብአዊ ድርጅቶች በተለይም የስደተኞች ጉዳይ ኮሚሽን (UNHCR) የኢትዮጵያ ስደተኞች ጉዳይ በብርቱ እንዳሳሰበው በጥር ወር መግቢያ ላይ በሚገባ ዘግቦታል፡፡ በ2011 (እ.ኤ.አ) ዓ.ም ከምሥራቅ አፍሪካ ተሰድደው ወደ የመን ከገቡት 103 ሺህ ስደተኞች መሀከል 75% (3/4) የሚሆኑት ኢትዮጵያውያን ናቸው፡፡ ይህም ማለት ከአራት (4) ስደተኞች መሀከል ሦስቱ (3) ኢትዮጵያውያን መሆናቸው ነው፤ ያውም በየበረሀውና በየባህሩ ወድቀው የቀሩትን ሳያካትት፡፡

ከዚህ የምንረዳው የሥራ አጡ ቁጥር አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን ከመጠቆም ባሻገር ውሎ አድሮ የኢህአዴግ ፈተና ሊሆን ይችላል፡፡

ዕድሜ ማሳጠሪያ አምስት

- አቅምን ያላገነዘበ ታክስ (ግብር)

ሰሞኑን የአሜሪካው ፕሬዝዳንት ባራክ አባማ ግብርን (ታክስን) በተመለከተ ከፍተኛው ክፍያ መከፈል የሚገባቸው ትልልቅ ባለሀብቶች መሆን እንዳለባቸው እየወተወቱ ነበር፡፡ ከአንድ ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ያለው ባለሀብት እስከ 30% ታክስ መከፈል እንዳለበት ለህዝባቸው አስታውቀዋል፡፡ አባባሉ ካለው ይወሰድበታል፤ ለሌላው ይሰጠዋል የሚል አንድምታ አለው፡፡

የእኛ ግን ያለውንና የሌለውን ያገናዘበ (የለየ) አይደለም፡፡ በመንግሥት የግብር ተመን መወሰኛና መሰብሰቢያ መዋቅር ውስጥ የታጨቁት ሹመኞች በየደረጃው የአቅም ማነስ ችግር እንዳለባቸው የ2004 ዓ.ም የግብር አሰባሰብ ሂደት ወቅት የታየው ከፍተኛ ክፍተት ከፈጠረው የሕዝብ እሮሮ አንፃር ኢህአዴግም ያመነው ጉዳይ ነው፡፡ በተለይም ከ2002 ምርጫ በኋላ ኢህአዴግ ከመጠን በላይ ለለጠጠውና እስከ 500 ቢሊዮን ብር /የአባይን ግድብ ወጭ ሳያካትት/ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ መተግበሪያ ገቢ ለመሰብሰብ ሲባል ህዝብን እርቃኑን ማስቀረት ውጤቱ አደገኛ መሆኑ አይቀርም፡፡

የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ክፍያን ብንወስድ ከፋዩ ተጠቃሚው ተራ ህዝብ ነው፤ ሻይ ያለ ቫት መጠጣት ከማንችልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል፡፡ የንግዱ ማህበረሰብ (ከቸርቻሪው እስከ ጅምላ አከፋፋዩ) (VAT) ተጠቃሚ እንዲሆን በተገደደ ቁጥር ኪሳራቸውን የሚያወራርደው በተጠቃሚው ላይ ነው፡፡ በተለይም ባለፉት አመታት በፓርላማም ጭምር በተቃዋሚዎች ተነስተው ከነበሩት ጉዳዮች አንዱ በአንድ ዕቃ ላይ በየደረጃው እየተደጋገመ የሚጠየቀው የቫት ክፍያ ለዋጋ ንረቱ ምክንያት መሆኑን ነበር፡፡ ኢህአዴግ ግን በተለይም አቶ መለስ የወረዱ ቃላት ተጠቅመው ሃሳቡን አጣጥለውት አልፈዋል፡፡

በ2004 ዓ.ም የግብር ክፍያ ግር ግር ወቅት የፀጉር አስተካካይ ደንበኛዬ ዘንድ ሄድኩኝ ፀጉሬን ልስተካከል ግድግዳው ላይ አዲስ የዋጋ ተመን ለጥፏል፡፡ ለአዋቂዎች 5 ብር የነበረው 10 ብር ሆኗል፡፡ "ምን ተገኘ አልኩት?" በመገርመም፣ በመደንገጥም ስሜት "ምን ላድርግ? አምና 240.00 ብር ግብር የከፈልኩበትን ሥራ ዘንድሮ 2,800.00 ብር እንድከፍል ተገደድኩኝ፡፡ ስለዚህ ያለኝ አማራጭ ዋጋ መጨመር ብቻ ነው አለኝ" ፍርጥም ብሎ፣ እውነቱን ነው፡፡ የቤት ኪራይ ክፍሎ ቤተሰብ አስተዳድሮ ለሥራው የሚያስፈልጉትን ግብአቶች አሟልቶ ኑሮን ለመቋቋም በደንበኞቹ ላይ ለመጨመር ይገዳዳል፡፡

ሰዎች አስተውሉ በአንድ ጊዜ የተጨመረው የግብር ክፍያ ስንቱን ነጋዴ (በተለይም ትንንሽ ቸርቻሪዎችን) ምንኛ ያስደነገጠና ብዙዎቹ ንግድ ፍቃድ መልሰው ድርጅታቸውን ለመዝጋት መገደዳቸውን እናውቃለን፡፡ የግብር አተማመኑ

ወደ ገፅ 8 ዞሯል



ኢ/ር ዘለቀ ረዲ
mesayewa2011@gmail.com

# እናንተ ይህንን አትችሉትም

ኢ/ር ዘለቀ ረዲ

ብዙ ጊዜ ቀደም ብለው አንድን ነገር ያወቁ ሰዎች ተከታዮቻቸው እነሱ የቻሉትን የሚችሉ አይመስላቸውም፡፡ ሌላው ቀርቶ ያንን ነገር ሲሰሩ ወይንም ሲሽከሙና ሲከብዳቸው ሳያዩ እንደማይችሉ ርግጠኛ ሆነው ያወራሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች በባህሪ ከኢህአዴግ ጋር ይመሳሰላሉ፡፡ ምክንያቱም ኢህአዴግ ብዙውን ጊዜ "እኔ ብለቅ ይህችን ሀገር ለማስተዳደር አቅም ያለው ተቃዋሚ የለም" ሲል ይሰማል፡፡ እዚህ ላይ ከኢህአዴግ ስህተቶች ውሱኖቹን ብቻ ብንመለከት፡-

1. ኢህአዴግ ተቋዋሚዎች ብቁ መንግሥት ለመሆን የሚያደርጉትን ጥረት በእጅግ ተከታትሎ ይጎዳል፡፡ እንዳውም ጠጋ ብለው መማር ቢፈልጉ እንኳ ቅርበታቸው አስጊ መስሎ ከታየው የተለያዩ የስም ታርጋዎች አንዱን ለጥፎ ወደ እስር ቤት ያጉራቸዋል፡፡ በዚህም ለሀገር ሳይሆን ለሥልጣኑ ብቻ በማሰብ ተቃዋሚዎቹ ሀገር የማስተዳደር አቅም እንዳይኖራቸው በማድረግ እና የሀገሪቱ ብቸኛ አማራጭ ተደርጎ እንዲቆጠር አመቻችቷል፡፡

2. አንድን ነገር ምንነቱን ሳያውቁ በሩቅ መገመት ፈፅሞ አይቻልም፡፡ በጣም የሚያብረቀርቅን ነገር ከሩቅ አይቶ ወርቅ ነው፤ የደበዘዘ ብረትንም አይቶ መዳብ ነው ብሎ እነደመናገር ማለት ነው፡፡ አንድን የሚያብረቀርቅ ነገር ወርቅ ነው ለማለትየወርቅ መፈተሻ በሆነው እሳት መፈተን ግድ ይላል፡፡ ወይንም ስላላብለጨለጨም ሁሉንም መዳብ ነው ማለት ፈፅሞ አይቻልም፡፡ በዚህ ረገድ ኢህአዴግ ለተቃዋሚዎች የሚጠናከሩበትንናለሥልጣን የሚበቁበትን ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ሳያመቻች እና ሳያይ አይችሉም ማለት ፈጽሞም አይችልም፡፡

በዚህ ረገድ ትልቁ ከትንሹ፣ባለሥልጣኑ ከተራው ሕዝብ፣መምህሩ ከተማሪው፣ ሽማግሌው ከወጣቱ የተሻልኩ ነኝ የሚለው አባዜ በሁሉም ኢትዮጵያዊ ዘንድ የለም ማለት አይቻልም፤ ወደ ዋናው ጉዳይ ከመግባቴ በፊት አንድ መሳሌ ላቅርብ፤በአንድ ወቅት አንድ የ5 ዓመት ልጅ ያለው አባት ከቤቱ ሳሎን ተቀምጦ የጽሑፍ ሥራ እየሠራ እየለ ልጁ የተለያዩ ነገሮችን ይጠይቀዋል፡፡ አባትም የተወሰኑትን እየመለሰ ልጁም ጥያቄው እየቀጠለ ስለሄደ አባት ልጅ ሥራ አላሰራኝም በሚል መንፈስ ልጁን ቢቆጣም ልጁ ጥያቄውን መጠየቅ ሊያቆም አልቻለም፡፡ በዚህ በልጁ ሥራ የተበሳጨው አባት ለምን ይሄንን ልጅ ከባድ እና የማይጨርሰውን ሥራ ሰጥቼ አልገላገልም ብሎ አንድ ባጠገቡ ያለ የዓለም ካርታ ያለበት ወረቀት ቀዳዶ "ይህንን እንደነበረ ገጣጥመህ አምጣ" ይለዋል፡፡ የአባትየው ሐሳብ የገባው ልጅ ያንን የዓለም ካርታ ለመገጣጠም ረጅም ጊዜ አልፈጀበትም፡፡ 5 ደቂቃ ባልፈጀ ጊዜ እንደነበር አስተካክሎ ለአባቱ ይሰጠዋል፡፡ አባቱም በጉዳዩ ተገርሞ "እንዴት በአጭር ጊዜ ልታስተካክለው ቻልክ?" ይለዋል፡፡ ሕፃኑም ሲመልስ "ወረቀቱ ከጀርባው የሰው ስዕል ነበረው፡፡ ሰውየውን ሳስተካክለው ዓለሚቱ ተስተካከለችልኝ" አለው ይባላል፡፡

ከዚህ ታሪክ አንድ ትልቅ ነገር ልንማር እንችላለን፡፡ ወረቀቱን የቀደደው አባት የታየው ከፊት ለፊት ያለው የዓለም ካርታ ብቻ ሲሆን ልጁ ግን በአንድ ጊዜ ሁለት ነገር ታየው፡፡ ሕፃኑ ካርታውንለማስተካከል ከውስብስቡ የዓለም ካርታ ይልቅ የሚያውቀው እና ቀላሉ የሰው ስዕል ጠቅሞታል፡፡ ቀድሞም ያውቀዋልና፡፡ ደግሞም የሰው ሥዕል የምድር ወገብ የኬንትሮስ መስመሮች የሉትም፡፡

ልጁ ይህንን የተበጣጠሰ ካርታ በነበረበት እንዲመልስ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት በሚያመቸው መንገድ ሄዶ አጠናቀቀ፡፡ ባለንበት በዚህ ወቅት በኢህአዴግም ይሁን በተቃዋሚው ዘንድ አንድ ተመሳሳይ ባህሪ ይታያል፡፡ የህ ባህሪም አንድን ጉዳይ ብይዝ ከእርሱ ውጭ የሚወጣ ሰው ያለ አይመስለውም፡፡ በተለይ ወጣቱን እንደማይችል አድርጎ የማሰብ አባዜ ከሊቅ እስከ ደቂቅ ከኢህአደግ እስከ ተቃዋሚ፤ብቻ በሁሉም ዘንድ ያለ ባህሪ ነው፡፡

አንዳንድ ጊዜ "የኢትዮጵያ የነፃነት ትግል ለምን ጊዜ ወሰደ?` ለሚለው ጥያቄ በትግሉ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ተሳታፊ ከነበሩ ታጋዮች ውጭ የትግሉን ሂደት በተለያዩ ማዕዘን የሚያዩ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች ባለመኖራቸው ነው፡፡ በፍትሕ ጋዜጣ ቅፅ 5 ቁጥር 166 ታህሳስ 7 ቀን 2004 ዓ.ም ላይ ተመስገን ደሳለኝ አንድ ከማል ሐሲብ የተባሉ የግብፅ የነፃነት ታጋይ በጣሂር አደባባይ ላይ ሆነው በአፕሪል 18 ቀን 2011 ዓ.ም ለታይም መፅሄት በሰጡት ቃለ መጠይቅ የወሰደውን እንዲህ ሲል አኑሯል፡፡"ለ40 ዓመታት በጠመንጃ መገለበጥ ያልቻልነውን ሕዝቡ ያላንዳች ኃይል በ18 ቀን ውስጥ እውን አደረገው"፡፡ እኚህ ሰው 40 ዓመታት እንደታገሉ፣እንደተታኮሱ ነገር ግን ለውጥ ማምጣት እንዳልቻሉ አስረድተው፣የሕዝቡን በአጭር ጊዜ ለውጥ ማምጣት አድንቀዋል፡፡ እነኚህ ታጋይ መንግሥትን ለማውረድ የተጠቀሙበት ነፍጥ በማንሳት ሲሆን ሕዝቡ ግን አምባገነኑን የግብፅ ገዢ መጣል የሚቻልበትን ማዕዘን ነበርና ተሳክቶላቸዋል፡፡

ኢህአዴግም ይሁን የተቃዋሚ መሪዎች ሊያውቁት የሚገባው ነገር የዚህች ሀገር የለውጥ ኃላፊነት በእኛ ላይ ብቻ የተጣለ ኃላፊነት ነው ብሎ ከማሰብ አባዜ መላቀቅ አለባቸው፡፡ እነዚህ አባቶች ለዚህች ሀገር ከፍተኛ መስዋዕትነት የከፈሉ በወጣትነታቸው፣በተማሪነታቸው፣አይደፈሬና መለኮታዊ ኃይል አላቸው ይባሉ የነበሩትን ቀ/ኃ/ሥላሴን በግልፅ በመቃወም መሬት ከፊውዳሎች ነጠቀው ለባለቤቱ ለገበሬው ለመመለስ ያደረጉት ተጋድሎና ጭሰኞች የነበሩ ገበሬዎች ወደ ባለሀብትነት ያሸጋገሩ ባለውለታዎች ናቸው፡፡ ዳሩ ግን ደርግ ባቋራጭ ሥልጣን ከሕዝቡ ነጠቆ በግፍ ወጣቱን መግደል ሲቀጥል ያሁኖቹ ባለሥልጣናት በግልፅ ተቃውመው በረሃ በመግባት ግማሾቹ ከዚህች ሀገር በመሰደድ፣ታግለው ለዚህ ደርሰዋል፡፡ መቼም ያለመታደል ሆኖ ቀ/ኃ/ሥላሴ ደርግ ከደርግም ኢህአዴግ በመቀበል ሀገሪቷ የተሻለ ሳታገኝ ከእጅ አይሻል ዶማ ላይ ትገኛለች፡፡ በወቅቱ ወጣት ታጋዮች ያላደረጉት አልነበረም፡፡

ከላይ ባነሳናቸው የተለያዩ ምክንያቶች ሳቢያ ለረጅም ዓመታት ታግለው ሀገሪቷን እዚህ ያደረሱ አባቶች ወሳኝ የሆነ ውሳኔ መወሰን ይገባቸዋል፡፡ ይሄውም እያንዳንዱ ሰው በትግል ከኢህአዴግ ያልተናነሰ ዕድሜ ታግሎ በዚህም ታጋዮቹም ከእስርና ከእንግልት ያላለፈ ህይወት እንዲመሩ ሲደረጉ በሀገሪቱም ያለው የዴሞክራሲ ዕድገት ከድጡ ወደማጡ መሆኑ ሊያሳስባቸው ይገባል፡፡ ይልቅ ሃላፊነታቸውን ለተከታዩ ትውልድ ያለፍርሃት የሚሰጡበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይገባል፡፡ እነርሱም ተቃዋሚዎቹም "አዲሱ ትውልድ ልሸከመው

ወደ ገፅ 5 ዞሯል

# - ሀገራቸው ያላከበረቻቸው መሪ
# - ንጉሱ ከንኩሩማ ይድነቃቸው ከፑሽኪን ያንሱ ይሆን?

ከብሩክ ከበደ

ኢትዮጵያ ለአፍሪካ አይደለም ለመላው ጥቁር ሕዝብ በነፃነቷ፣በስነ-ጽሑፍ፣በእንግዳ ተቀባይነት፣በጀግንነት፣ የሰው ልጅ ሥልጣኔ መገኛ ወዘተ. በግንባር ቀደምትነት የምትወሳ ለመሆኗ እንኳን ልጆቿና ተወላጆቿ ቀርተው ጠላቶቿ የሚመሰክሩላት ታላቅ አገር ነች፡፡

አገራችን የራሷን ታሪክና ነፃነት ከመጠበቅ አልፋ አገራቸውና ነፃነታቸው በኃይል ለተደፈጠጠባቸው ሕዝቦች ግንባር ቀደም ተሚጋችና አርዓያ በመሆን ላደረገችው እንከን የለሽ ተግባርና ተጋድሎ የመሪዎቿ ስም በየጊዜው በዓለም ሕዝቦች ዘንድ ሲነሳና ምርጥ ሥራዎችን ለዓለም ካበረከቱ ግለሰቦች ተርታ ተሰልፎ መመልከቱም ሆነ ማዳመጡ ለኢትዮጵያ አዲስ አይደለም፡፡

አፄ ምንሊክ የጥቁር ሕዝቦች የነፃነት አርዓያ መሆናቸውን ያስመሰከሩትን ያህል ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴም የተጨቆኑ ሕዝቦች አንድነት እንዲፈጥሩ፣ለነፃነታቸው እንዲዘምሩ ተግተው ከሥራታቸውም በላይ በጥቁሮች ዘንድ መንፈሳዊ /መለኮታዊ/ ኃይል ያላቸው ናቸው እስከ መባል የደረሰ ስብእና የታደሉ እና የተዋጣላቸው መሪ ነበሩ፡፡ ይህ ብቻ አልነበረም የንጉሱ ስብእና መገለጫ፡፡ ጥቁሮች እንዳይረግጡት ይከለከሉ የነበሩ የነጭ ቤተ መንግሥቶችን ምንጣፍም በመርገጥ፣ እጅ በመጨበጥ ነጭ መሪ የሚደረግለት አፊሴላዊ አቀባበል የሚደረግላቸው ብቻ ሳይሆን ከተለያዩ በንጉስ፣ፕሬዘዳንት እና ጠ/ሚኒስትር በሚተዳደሩ ከ50 ሀገራት በላይ የደረት ኒሻንና የክብር ዶክትሬት በመቀበል ግንባር ቀደም ነበሩ፡፡

ንጉሱ በተለያየ ምክንያት ቂምና ፀብ ያለባቸው ጐረቤት ሃገራትን በማስታረቅ የአፍሪካ አባት የሚል ግዙፍ ስም የተቀዳጁና በተለያዩም የአፍሪካ አገራት እንደ ዛንቢያ፣ኬንያ የመሳሰሉት የዋናውና ከተሞቻቸውን መንገዶች ስያሜ በስማቸው የሰየሙላቸው ታላቅ ኢትዮጵያዊ ነበሩ፡፡

በተለይም ቀ/ኃ/ሥ ጥቁር አፍሪካውያኖች ነፃነታቸውን እንዲቀዳጁና በአንድ ማሕበር ጥላ ሥር ተሰባስበው የወደፊት አቅጣጫቸውን እንዲመክሩም አንድ ማሕበር ለመመስረት ያደረጉት እልህ አስጨራሽ ትግል በመጨረሻም ተሳክቶላቸዋል፡፡ በጊዜውም አፍሪካውያኖች ነፃነታቸውን እንዲቀዳጁ ኢትዮጵያ ከፍተኛ ድርሻ በመወጣቷ የባንዲራዋን ቀለም አቀማመጥ በመለዋወጥና መሐሉ ላይ ተጨማሪ ነገር በማከል የራሳቸው ባንዲራ መለያ ያደረጉ ቁጥራቸው ወደ 10 የሚጠጉ አገራት በአፍሪካ ብቻ መገኘታቸው የቀ/ኃ/ሥ ታላቅነት የሀገሪቷንም የነፃነት ምኩራብነት የሚገልፅ ነው፡፡ ከእነዚህ ሀገራት መሃል አንዷ ጋና ናት፡፡

ቀ/ኃ/ሥ አ..ኤ.ዩ./የአፍሪካ አንድነት ድርጅት/ ካዛብላንካ፣ሞሮኮ፣ሞኖሮቪያና ላይቤሪያ የተሰበሰበውን ሁለት ቡድን ተመላልሰው በማስረዳትና በማሳመን ወደ አንድ ማሕበር በማምጣት ከኢዮቤልዩ ቤተመንግሥት ፊት ለፊት መሰብሰቢያ አዳራሽ በማሰራትና ከርቸሌ አጠገብ በነጄነራል ፅጌ ዲቡ አማካኝነት ለፖሊስ ሰራዊት አገልግሎት የተሠራውን በጊዜው በከተማዋ ውስጥ ቁጥር አንድ ረጅምና ውብ የሆነውን ሕንፃ ለማሕበሩ በመስጠት ሃሳባቸውን ብቻ ሳይሆን የአገራቸውን ሃብትና እውቀት በመስጠት ለአፍሪካውያኖች ሕብረት ታሪክ የማይረሳውን ሥራ አበርክተዋል፡፡

ቀ/ኃ/ሥ ለአፍሪካና ለአፍሪካውያኖች ነፃነትና ብልፅግና በነበራቸው ታላቅ ራእይም በእኛ አቆጣጠር በ1960ዎቹ ኔልሰን ማንዴላን ጨምሮ ሌሎች የኤኤንሲ አመራሮች ወደ ኢትዮጵያ በማምጣት ደብረዘይትና ኮልፌ ወታደራዊ ሥልጠና እንዲሰጣቸው አድርገዋል፡፡ ይህ ለአፍሪካውያኖች ነፃነት የማሰብ ተግባርም በኮ/መንግሥቱ ኃ/ማርያም አመራር ጊዜ ቀጥሎ የሞዛቢክ /ፍሪሊሞ/ የዚምባቡዌ /ዛኑፒኤፍ/ አባላት ኢትዮጵያ በመምጣት ሰልጥነውና ታጥቀው በመሄድ አሁንም ይሄኛው አመራር የንጉሱን ድርሻ በመጠኑ ይጋራል፡፡

ከሠልጣኞቹ መሃል ማንዴላ ኢትዮጵያን ጐብኝተው እንደተመለሱ 27 ዓመት የፈጀውን የሮቢን ደሴት እስሩን ጀመረ፡፡ በጊዜው የደቡብ አፍሪካ መንግሥት ማንዴላን ለማሰር የበቃው ማንዴላ በነፃነቱ ኢትዮጵያ ምድር ላይ ከተለያዩ የአፍሪካ፣የላቲን፣የኤዢያና መካከለኛው ምስራቅ ለነፃነታቸው ከሚፋለሙ ድርጅቶች ጋር መገናኘታቸው ለሮዴዢያ መሪዎች በመድረሱ ነበር፡፡ እ.ኤ.አ 1990 ማንዴላ ከእስር ሲለቀቁም መጀመሪያ የጐበኙት ኢትዮጵያን ነበር፡፡ በጊዜውም ኢትዮጵያን ይመሩ የነበሩት ኮ/መንግሥቱ ኃ/ማርያም በብሔራዊ ቤተ መንግሥት በተደረገ ታላቅ ሥነ-ሥርዓት የአገራችንን የክብር ኒሻን ሸልመዋቸዋል፡፡

እዚህ ላይ ንጉሱም ሆኑ አገራችን ለአፍሪካ ነፃነት ብቻ ሳይሆን በስነ ልቦናም ሆነ በእውቀት ያስመሰከሩበትን የማንዴላን አስተያየት አንስቼ ማለፍ እፈልጋለሁ፡፡ በጊዜው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ይበር የነበረው የኬኔት ካውንዲ አገር ዛንቢያ ድረስ ነበር፡፡ ይህም የሆነው ከዛንቢያ በታች ያሉ አገራት በሙሉ በቅኝ ገዢዎች ተይዘው ስለነበር ነው፡፡ ማንዴላም ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ የያዛቸው አውሮፕላን እስከ ዛንቢያ ድረስ ነበር ያደረሳቸው፡፡ ዛንቢያ ከደረሱ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት አየር መንገዳችን ውስጥ ይገባሉ፡፡ እንደ ገቡ ግን ባዩትና ቅኝ ገዢዎች በአእምሮዋቸው የረጩት መርዝ የሚያዩትን እንዲያምኑ አላደርግ ብሎ ጥርጣሬ ውስጥ ከተታቸው፡፡ የሚያዩት ነገር ግን እውነት ነበር፡፡ አውሮፕላኑ የሚበረው በጥቁር አብራሪ እና ጥቁር አስተናጋጅ ሴቶች ነበሩ፡፡ ይህንን እውነት ማንዴላ ከቀልባቸው ሲመለሱ የዘረኞቹን ሐሳብ ከፉኛ ኮንነዋል፡፡

በቀ/ኃ/ሥ የአገዛዝ ዘመንም ደቡብ አፍሪካ ከአህጉሪቷ እግር ኳስ ጀምሮ እስከ ዓለም አቀፍ ውድድሮች አሎምፒክን ጨምሮ እንዳትካፈል ከፍተኛ ትግል ያደረጉትና ውጤታቸውም ከግብ የደረሰላቸው ሌላኛው የአፍሪካ ስፖርት አባት ይድነቃቸው ተሰማ ነበሩ፡፡ እነዚህ ሁለቱ ብቻ ሣይሆኑ ሌሎችም በዲፕሎማቲኩ ዘርፍ የተሰማሩ ኢትዮጵያውያኖች ለአህጉሪቷ ነፃነት ያደረጉትን ትግል ለመጥቀስ እንዲህ በዋዛ የሚቻል አይደለም፡፡ የሚገርመው ግን እነዚህ ሁለት ቁንጮ የአፍሪካ ፖለቲካና ስፖርት ሞተሮች ነብይ በሃገሩ አይከበርም እንደሚባለው ሆነና ንጉሱ መገደል ብቻ ሣይሆን አሳዛኝ አቀባበርም ሲጠብቃቸው፤ሌላው ባለውለታ ቀብራቸው እንደ ተራ ዜጋ ተፈፅሟል፡፡

ሕንጾች ለቀ/ኃ/ሥ በነበራቸው ፍቅርና ክብር ሲኒማ አምፔር አጠገብ ከወገባቸው በላይ ምስላቸውን በነሃስ ሰርተው ቢያስቀምጡላቸውም አፍቃሪ ሶሻሊዝም የነበረው ስርዓት ሲመጣ አውልቆ ጥሎታል፡፡ ይድነቃቸውም ለአገራቸው፣ለአህጉራቸውና ለዓለም የሰሩት ሥራ ሁሉ ገደል ገብቶ ለኢትዮጵያ ያደረገው ነገር እስከ አሁን ባልገባኝ ደረጃ ለሩስያዊው አሌክሳንደር ፑሽኪን አደባባይ ሲሰየም ለእኚህ ባለ ውለታ ግን በተለይ በአሁኑ ጊዜ በከተማዋ ውስጥ ሞልቶ ከተትረፈረፈውና ባለሃብቶች በብራቸው ድርጅቶቻቸውን ከሚያስተዋውቁባቸው አደባባዮች መሃል አንድም በእሳቸው ስም አለመሰየሙ በእጅጉ የሚያስቆጭ ነው፡፡ ምንም እንኳን የይድነቃቸውን ታላቅ ሥራ አገራቸው ባትዘክርላቸውም ሌላዋ አፍሪካዊት አገር ሞሮኮ ዋና ከተማዋ ራባት ውስጥ የሚገኘውን የተለያዩ ስፖርት ማዘውተሪያ የሆነውን ስታዲዮሙዋን በስማቸው ሰይማላቸዋለች፡፡ ሞሮኮዎች ራሳቸው ሕጉን አርቅቀውና አዘጋጅተው ያስፀደቁትን ከ21 ዓመት በታች የሚዘጋጀውን የአፍሪካ ወጣቶች ዋንጫ ስያሜ እስከ አሁን ድረስ የይድነቃቸው ዋንጫ በሚል እየተካሄደ ይገኛል፡፡ ሜክሲኮ የሚገኘው ትልቁ የአዛቲክ ስታዲዮምም መግቢያው በር ላይ በሰሩት ሥራ ስማቸው ለመታሰቢያነት ተቀርፆ ከተቀመጠው አምስት ታላላቅ ሰዎች አንደኛው ይድነቃቸው ተሰማ ናቸው፡፡ ፊፋ ከፍተኛውን የአገልግሎት ሜዳሊያ የሸለማቸው ጥቁሮች ሁለት ሲሆኑ አንደኛው ፔሌ ሌላኛው ይድነቃቸው ናቸው፡፡ ሌላው ከሁሉ የሚያሳዝነው የይድነቃቸውን 10ኛ ሙት ዓመት ካፍ ኢትዮጵያ ውስጥ ለማካሄድ አስቦ በጊዜው ከሚመለከታቸው በቂ ምላሽና ትብብር በማጣቱ ሥነ-ሥርዓቱን ግብፅ አሌክሳንደሪያ ላይ በመውሰድ በርካታ በሺዎች የሚቆጠሩ የይድነቃቸው አድናቂዎች በተገኙበት ከማክበሩም በላይ ካፍና ፊፋ የላቀ ሽልማቶቻቸውን ለቤተሰቦቻቸው አበርክተውላቸዋል፡፡

# ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ

## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ (መድረክ)

**በአዲሱ የከተማ ቦታ ሊዝ አዋጅ ዙሪያ ከህዝብ ጋር መወያየት ስለሚፈልግ እሁድ የካቲት 4 ቀን 2004 ዓ.ም በአዲስ አበባ የውይይት መድረክ ስለተዘጋጀ ሁላችሁም ነዋሪዎች ተጋብዛችኋል።**

**ውይይቱ የሚካሄድበት ቦታ አዲስ አበባ በሚገኘው ቄራ በረት ገባ ብሎ በቀድሞ ቀበሌ 42 በአሁኑ ወረዳ 5 የመሰብሰቢያ አዳራሽ ከቀኑ 7፡00 ሰዓት ጀምሮ እንድትገኙ በአክብሮት ጥሪውን ያስተላልፋል።**

**ሁሉም ኢትዮጵያዊ የመብቱ ተጠቃሚ እንዲሆን መድረክ ከአዲስ አበባ በተጨማሪ በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ በክልሎችም ተመሳሳይ ውይይት እንደሚያደርግ ከወዲሁ ይገልፃል።**

**የኢትዮጵያ ሕዝብን የሥልጣን ባለቤት ለማድረግ በሚደረገው ትግል የግልዎን ድርሻ መወጣት ይፈልጋሉ?**
**እንግዲያውስ ለዚህ አላማ በፅናት ለሚታገለው አንድነት ፓርቲን በሞራል፣ በሀሳብና በገንዘብ ይርዱ።**

አንድነትን በገንዘብ መርዳት ለምትፈልጉ፣
አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ
የሂሳብ ቁጥር፡- 510
ንብ ባንክ፡ ዑራኤል ቅርንጫፍ ገቢ ያድርጉ።

ድረ-ገፅ: www.andinet.org
E-mail: andinet@andinet.org
or udjparty@gmail.com
Tel. 0111226288